# አዲስ ዘመን

እፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 213 ሚያዝያ 3 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# በኢድ አልፈጥር በዓል

## የታየው መደጋገፍና መተባበር የሁልጊዜ ተግባር ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል

## 1445ኛው ኢድ አልፈጥር በዓል በአዲስ አበባ በድምቀት ተከብሯል


**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡-በኢድ አልፈጥር በዓል የታየው መደጋገፍና መተባበር የሁልጊዜ ተግባር ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል ሲሉ የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ሼህ ሁሴን በሽር ገለጹ፡፡

1445ኛው ኢድ አልፈጥር በአዲስ አበባ ስታዲየም በትላንትናው ዕለት በድምቀት ተከብሯል፡፡

በዒዱ ሶላት ሥነ ሥርዓት ላይ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሐጂ ኢብራሂም ቱፋን ጨምሮ የአዲስ አበባ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሡልጣን አማን ኤባ፣ የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሽዴ፣ ኡስታዞች፣ ኢማሞችና የእምነቱ ተከታዮች ተገኝተው አክብረዋል።

በኢድ አልፈጥር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








## "ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን የታጠቁ ኃይሎች በሰጥቶ መቀበል መርሕ ለውይይት ዝግጁ ሲሆኑ ይገባል"

-አቶ ደስታ ዲንቃ

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን የታጠቁ ኃይሎች በሰጥቶ መቀበል መርሕ ለውይይት ዝግጁና ቁርጠኛ ሊሆኑ እንደሚገባ የኢትዮጵያ የፖለቲካ

"ዘላቂ ሠላምን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ እስከ አሁን ከ50 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተሰብስቧል

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

አዲስ አበባ-፡ ዘንድሮ ከለማው የበጋ መስኖ ስንዴ እስከ አሁን ከ50 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ታጭዶና ተወቅቶ ወደ ጎተራ መግባቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በበልግ ወቅት ወደ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር የሚደርስ መሬት ለማረስ መታቀዱን ተጠቁሟል፡፡

የሚኒስቴሩ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀው በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ ከዘንድሮው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እስከ መጋቢት 23 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በአንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር ማሳ ላይ የነበረ የስንዴ አዝመራ

ከበጋ መስኖ ስንዴ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ኢትዮጵያ

## የሱዳን ጦርነት በአፍሪካ ህብረት እንዲፈታ የጀመረችውን ሥራ አጠናክራ ልትቀጥል ይገባል

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ያላትን ታሪካዊ ተደማጭነቷ ተጠቅማ የሱዳን ጦርነት በአፍሪካ ኅብረት እንዲፈታ ኃላፊነቷን ልትወጣ እንደሚገባ የአፍሪካና እስያ ጉዳዮች ተመራማሪ አቶ ቅዱስ ገዛኸኝ አስታወቁ፡፡

የአፍሪካና እስያ ጉዳዮች ተመራማሪ አቶ ቅዱስ ገዛኸኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሱዳን ለውጭ ገበያ ታቀርባቸው የነበሩ የቁም እንስሳት፣ ወርቅና ድፍድፍ ነዳጅ በጦርነቱ ምክንያት ቆመዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሱዳን ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድቀት ውስጥ ናት፡፡ ይህ ከሱዳን አልፎ የቀጣናውን ኢኮኖሚውን እየጎዳው ነው፡፡

ኢትዮጵያ የሱዳን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# የኢድ አልፈጥር በዓል በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በድምቀት ተከበረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


አዲስ አበባ፡- ፲፬፻ 445ኛው የኢድ አልፈጥር በዓል በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በድምቀት ተከብሯል፡፡ በዓሉ ከተከበረባቸው አካባቢዎች መካከል ሐረር፣ ሀዋሳ፣ አሶሳ፣ አዳማ፣ ጅግጅጋ፣ መቀሌ፣ ባሕርዳር፣ ባሌ ሮቤ፣ ሰመራ፣ ጋምቤላ፣ ድሬዳዋ፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ ደሴ፣ ጂንካ፣ አርባምንጭና ደብረብርሃን ከተሞች ይገኙበታል።

በየአካባቢዎቹ ከማለዳው ፲፩ ተኩል ጀምሮ በርካታ የእስልምና እምነት ተከታዮች የተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥነ-ሥርዓቶችን በማከናወንና በስግደት የኢድ አልፈጥር በዓል በድምቀት አክብረዋል፡፡

በበዓሉ አከባበር ሥነ-ሥርዓት ዑላማዎች፣ ሼኮች፣ ኢማሞችና ሌሎችም የእምነቱ ተከታዮች ተሳትፈዋል፡፡

የእምነቱ ሥርዓትና አስተምህሮት በሚፈቅደው መሠረት በሐረር ጁምኣ መስጂድ ኢማም ሼህ ሙክታር ሐጂ ሙባረክ አማካይነት የሶላት ስግደት ሥነ ሥርዓት ተከናውኗል።

በወቅቱም ሼህ ሙክታር ሐጂ ሙባረክ "በዓሉን ስናከብር ምዕመናኑ አቅመ ደካሞችን፣ ወላጅ አልባ ሕፃናትና ደጋፊ የሌላቸው የተቸገሩ ወገኖቻችንን በመርዳትና በመንከባከብ ሊሆን ይገባል" ብለዋል።



ፎቶ ሀዲስ አብርሃ

ወጣቱም ሃይማኖቱ የሚያዘውን መልካም ተግባር በማከናወንና አንድነቱን በማጠናከር የጀመረውን አበረታች ሥራዎች ማጠናከር እንደሚገባውም አስገንዝበዋል፡፡

ዘንድሮ ሕዝበ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ የፆም ወቅትን አንድነቱን በሚያጎለብት መልኩ አብሮነቱን ማሳየቱን የተናገሩት ደግሞ የእምነቱ ተከታይ አሕመድ ዩሱፍ ናቸው።

በፆሙ ወቅት በጋራ የጀመሩትን የመረዳዳትና የመደጋገፍ እንዲሁም የተቸገሩ ወገኖችን የመደገፍ ተግባር በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

በረመዳን ወር የነበረው አንድነትና መልካም ሥራ ከረመዳን በኋላም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት የሲዳማ ክልል እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ አብዱሽኩር አብዱቃድር አሳሰቡ።

፲፬፻ 445ኛው የኢድ አል-ፈጥር በዓል በሀዋሳ ከተማ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን በመፈጸም በድምቀት ተከብሯል። የሲዳማ ክልል እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ አብዱሽኩር አብዱቃድር በዚህ ወቅት እንደገለጹት፤ ሕዝበ ሙስሊሙ በዓሉን በአብሮነት፣ በመደጋገፍ እና በመቻቻል ማክበር አለበት።

ያለፈውን የረመዳን ወር በፆምና በፀሎት ከፈጣሪ ጋር በመገናኘት እና አቅመ ደካሞችንም በመደገፍ ማሳለፉንም አውስተዋል።

በተለይም በረመዳን የፆም ወቅት ያሳየውን የአንድነትና የመረዳዳት ባሕል በዘወትር እንቅስቃሴውም ማጠናከር እንዳለበት ሼህ አብዱሽኩር አሳስበዋል።

የኢድ አልፈጥር በዓል ሲከበር ያለው የሌለውን በመርዳት፣ በመተጋገዝ እንዲሁም በአንድነት ማክበር እንደሚገባም የበዓሉ ታዳሚዎች ገልጸዋል።



ፎቶ ሀዲስ አብርሃ

# ዩኒቨርሲቲው ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ሕንጻዎችን እያስገነባ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የሕንጻዎችና መሠረተ ልማቶች ግንባታ እያካሄደ መሆኑን የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ፡፡

የወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ግንባታ ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ተስፋሁን ገብሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ግንባታዎች እያከናወነ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜም 25 የተለያዩ ሕንፃዎችና መሠረተ ልማቶች እየተገነቡ ናቸው፡፡

ዩኒቨርሲቲው በተያዘው በጀት ዓመት ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የተለያዩ ሕንጻዎችንና መሠረተ ልማቶችን እየገነባ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ የሕንጻ ግንባታዎቹ በተለይም የመማር ማስተማሩን ሂደት ምቹ ለማድረግ፣ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅና የተማሪ ቅበላ አቅምን ለመጨመር የሚረዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ግንባታው የአስተዳደር፣ የተማሪዎች አገልግሎት ሕንጻዎች፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የተማሪዎች ዶርሚተሪዎች፣ ቤተሙከራዎች (ላቦራቶሪዎችን) ጨምሮ አይሲቲ ታወሮች እና ሌሎች መሠረተ ልማቶችን ያካተተ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የቤተ ሙከራው ግንባታው ፲፩ ቤተ ሙከራዎችን አንድ ላይ አጣምሮ የያዘ ነው ያሉት ሥራ አስኪያጁ፤ ይህም ዩኒቨርሲቲው ለተግባር ዩኒቨርሲቲነት የሚያደርገውን ጉዞ የሚያፋጥን መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት በግንባታው ዘርፍ ለመሠረተ ልማቶች ትኩረት ተሰጥቶ ሲሠራ መቆየቱን በመግለጽ፤ ጎን ለጎን የማኅበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች መሠራታቸውንም አውስተዋል፡፡

ባለፉት ስድስት ወራት ሦስት ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለማኅበረሰብ አገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ተስፋሁን፤ የማኅበረሰብ አገልግሎት የግቢውንና የአካባቢውን ማኅበረሰብ አገልግሎት ያጠቃለለ ነው ብለዋል፡፡

የግቢው ማኅበረሰብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ደረጃውን የጠበቀ የሕፃናት ማቆያ መገንባቱን ጠቅሰው፤ ግንባታው በ26 ሚሊዮን ብር ወጪ መከናወኑን ተናግረዋል፡፡

ለዩኒቨርሲቲው የአካባቢ ማኅበረሰብ አገልግሎት የሚውሉ ሁለት የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክቶች ተገንብተው ለአገልግሎት መብቃታቸውን ገልጸው፤ ግንባታቸው ከተጠናቀቁት ፕሮጀክቶች በተጨማሪም በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ መኖራቸውን አመልክተዋል፡፡

በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን በየተያዘላቸው ጊዜ ለማጠናቀቅ እየተሠራ እንደሚገኝም ተናግረዋል፡፡

የግንባታ ግብዓቶች ገበያ አለመረጋጋትና ሌሎች ችግሮች የግንባታ መጓተቶችን ሊፈጥሩ እንደሚችል በስጋትነት አስቀምጠዋል ፡፡

# ሞሪንጋ ለመቀንጨር ችግር ሁነኛ መፍትሔ እንደሆነ ተገለጸ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ሞሪንጋ ወይም ሺፈራው ለሕጻናት የመቀንጨር ችግር ሁነኛ መፍትሔ እንደሆነ ተነገረ፡፡

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የምግብ ሳይንስና ሥነ ምግብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አልጋነሽ ቶላ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሞሪንጋ የመቀንጨር ችግርን መከላከል የሚያስችል የንጥረ ነገር ይዘት ያለው ቅጠል ነው፡፡

በሀገራችን እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ 38 ከመቶ ያህል ሕጻናት የመቀንጨር ችግር እንደሚገጥማቸው ያነሱት ዶ/ሯ፣ ሞሪንጋ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ሁነኛ መፍትሔ እንደሆነ ነው የተናገሩት፡፡

በአይረን፣ ዚንክ፣ ፕሮቲን፣ ፖታሺየም፣ ካልሺየምና ሌሎችም ንጥረ ነገሮች የበለጸገው ሞሪንጋ የንጥረ ነገር ይዘቱ የሥነ ምግብ ችግርን ለመቅረፍ የሚያስችል ነውም ብለዋል፡፡

አልጋነሽ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በዓለም አቀፍ የእርሻና ምግብ ድርጅት ድጋፍና በኢንስቲትዩቱ አስተባባሪነት ሞሪንጋን ለተለያዩ ምግቦች ለማዋል የሚጠቅም ፕሮጀክት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በደቡባዊ የሀገራችን ክፍል ሞሪንጋ ሐለኮ በሚል መጠሪያ እንደሚታወቅ የጠቀሱት አልጋነሽ (ዶ/ር) ፣ ቅጠሉን በተለያዩ ምግቦች ውስጥ በመጨመር የመጠቀም ልምድ መኖሩንም ተናግረዋል፡፡

በከተሞች አካባቢ ግን ከሻይ ቅጠል ውጪ ለምግብነት ከመጠቀም አኳያ ልምድ አለመኖሩንም አንስተዋል፡፡

በፕሮጀክቱ የተመራው ምርምር ይህን ሁኔታ በመቀየር በከተሞች አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ ሞሪንጋን ከተለመዱ ምግቦች ጋር እንዲጠቀመው የሚያስችል ነው፡፡

በምርምሩ ሞሪንጋን በስንዴ ዳቦ፣ በቡላ ገንፎ፣ ኩኪስና አይስክሬም ውስጥ ጨምሮ መጠቀም እንደሚቻልም ተመላክቷል፡፡

ትምህርት ቤቶች ላይም በምገባ ፕሮግራምም ላይ ለምግብነት ከሚውሉ የተማሪ ምገባ ፕሮግራም ውስጥ ቢገባ በልጆች እድገት ላይ በጎ ተጽዕኖ ይኖረዋል የሚል አስተያየትም ሰጥተዋል፡፡

ሞሪንጋ ከሰው ልጆች ባሻገር፣ ለእንስሳት መኖም መዋል እንደሚችል የተናገሩት አልጋነሽ (ዶ/ር)፣ በተለይም የወተት ላሞች ሞሪንጋን ቢመገቡ የወተትን የንጥረ ነገር ይዘት ለመጨመር ያግዛል ነው ያሉት፡፡

እርሳቸው እንደገለጹት፣ ኢንስቲትዩቱ ሞሪንጋን የማስተዋወቁና የማስፋፋቱን ሥራ አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

የገበያ ትስስርን በመፍጠር ረገድም ተቋሙ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ጥረቶችን እያደረገ እንደሚገኝም አስታውቀዋል፡፡

በኢንስቲትዩቱ የምግብና ሥነ ምግብ ምርምር ክፍል ከፍተኛ ተመራማሪና የሞሪንጋ ፕሮጀክት አስተባባሪ ሰሎሞን



**አልጋነሽ ቶላ (ዶ/ር)**



**ሶሎሞን አባተ (ዶ/ር)**

አባተ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ሞሪንጋ እንደ ስኳር ደም ግፊትና መሰል ድምፅ አልባ በሽታዎች ለመከላከል እንደሚረዳ ይናገራሉ፡፡

ቀደም ሲል ሞሪንጋን በከተሞች ላይ ለማስተዋወቅ ሰፊ ሥራ መሠራቱንና ጥሩ ግንዛቤ እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

ነገር ግን፣ ቅጠሉን ከሌሎች ባዕድ ነገሮችና ቅጠላ ቅጠሎች ጋር ቀላቅሎ የመሸጥ ሁኔታ ሲበራከት የኅብረተሰቡም ፍላጎትና ገበያው ሊቀዛቀዝ ችሏል ብለዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ፣ ከዓለም አቀፉ የእርሻና የሥነ ምግብ ድርጅት ጋር በመተባበር ሞሪንጋ የሚያበቅሉ ሴቶችን በማደራጀት ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን የገቢ ማግኛ መንገድ እንዲሆናቸው በማሰብ የማሠልጠንና የማስተዋወቅ ሠራ እየሠራ ይገኛል፡፡

ከዚህ በፊት ከተለመደው በሻይ መልክ ከሚጠጣው በተጨማሪ የለመድናቸው ምግቦች ላይ የንጥረ ነገር ይዘቱን እንደያዘ ለምግብነት እንዲውል ጥረት እያደረግ ነው ያሉት ሶሎሞን (ዶ/ር)፤ ፕሮጀክቱ በእስካሁኑ ሂደት ብዙ ርቀት መጓዙን አመልክተዋል፡፡

በከተማ አካባቢ ያለውን የሞሪንጋ አጠቃቀም ለማሳደግ ተጨማሪ የምርምር፣ የማስተዋወቅና የማስፋት ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉም ነው ሰሎሞን (ዶ/ር) ያስታወቁት፡፡

በብዛት በቆላማ አካባቢዎች ላይ የሚበቅለው ሞሪንጋ በዓለም ላይ "ተዓምረኛው ቅጠል" በሚል በስፋት የሚታወቅና በተለያየ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ የዛፍ አይነት ነው፡፡

# ደስታ ሮቦት መጪው ትውልድ የተሻለ የቴክኖሎጂ እሳቤ እንዲያዳብር የምታስችል ናት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- "ደስታ" የሚል ስያሜ የተሰጣት ሮቦት በተለይ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ቋንቋዎች የተቃኘች መሆኗ መጪው ትውልድ የተሻለ የቴክኖሎጂ እሳቤ እንዲያዳብር የምታስችል ናት ሲሉ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት "ደስታ" የሚል ስያሜ የተሰጣት ሮቦት በሳይንስ ሙዚየም ትናንት ለዕይታ አቅርቧል።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) በዕለቱ እንደገለጹት፤ ደስታ ሮቦት በሀገር ወስጥ መቃኘቷ መጪው ትውልድ የተሻለ የቴክኖሎጂ እሳቤ እንዲያዳብር የምታስችል ናት፡፡

ሮቦቷ ሀገሪቷ በሰው ሠራሽ አስተውሎት ዘርፍ እየሠራች ያለችው ሥራ በተግባር የተገለጸባት ናት ያሉት ዶክተር እዮብ፤ ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂው ዓለም የደረሰበት ለመድረስ የሰው ሠራሽ አስተውሎትን ማሳደግ ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

ኢዮብ (ዶ/ር)፤ ቴክኖሎጂ ጥሩም መጥፎም ጎኖች አሉት ያሉ ሲሆን፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎት አዲስ እንደመሆኑ ጉዳቱና ጥቅሙ በማመዛዘን በከፍተኛ ጥንካሬ መምራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

በዚህ ረገድ ሀገሪቱ ቴክኖሎጂ ይዞት የሚመጣው ዕድል በመጠቀም የሚያስከትለው ጉዳት የሚያስቀር የፖሊሲ እሳቤ እየተከተለች ትገኛለች ነው ያሉት፡፡




እንደ ኢዮብ (ዶ/ር)ገለጻ፤ ሀገር በቀል ኢኮኖሚ ለማሳደግ ትኩረት ከሰጠባቸው ዘርፎች መካከል ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አንዱ ነው፡፡ ይህም በተለያዩ ዘርፎች ተጨማሪ አቅም እየፈጠረ እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

ሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሰው ልጅ የማሰብ አቅም በከፍተኛ ደረጃ የሚጨምር ነው ያሉት እዮብ (ዶ/ር)፤ እንደ ከዚህ በፊት ቴክኖሎጂዎች ዘመን ካለፈባቸው በኋላ መላመድ ሳይሆን ቀድሞ መጠቀም በሚል እሳቤ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት የኮሙኒዩኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ዘውዴ በበኩላቸው፤ በተለይ ሮቦቷ በሀገር ውስጥ ቋንቋ መናገር መቻሏ መጪው ትውልድ ቴክኖሎጂን የበለጠ እንዲላመድ ያስችለዋል ብለዋል።

አቶ ተስፋዬ ፤ ኢንስቲትዩቱ ሀገሪቱ በቴክኖሎጂው ረገድ ዓለም የደረሰችበት ለማድረስ ትኩረት ተደርጓል ያሉ ሲሆን ሮቦቷ በሀገረ ውስጥና በውጭ ሀገር ከሚገኙ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መዘጋጀቷን ተናግረዋል።

በኢንስቲትዩቱ የተለያዩ ችግር ፈቺ ቴክኖሎጂዎችን እየተሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ ከእነዚህ መካከል የሮቦት ቴክኖሎጂ ዘርፍ አንዱ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ደስታ ሮቦት ከተመልካች ለሚቀርብላት ጥያቄም በሀገር ውስጥና በውጭ ቋንቋዎች ምላሽ የምትሰጥ ሲሆን ኢንስቲትዩቱና ከiCog Labs በጋራ በመሆን በሀገር ውስጥና በውጭ ባለሙያዎች ማዘጋጀታቸውን ተገልጿል።

የአርቲፊሻል ቴክኖሎጂ የደረሰበትን ደረጃ ለማሳየት እንደሚረዳና የነገው ትውልድ ተረካቢ ሕፃናት ለሚሠሩት የፈጠራ ሥራዎች አጋዥ እንደሚሆን የተገለጸ ሲሆን በቅርቡ የሙዚቃ ኮንሰርት ታዘጋጃለች ተብሏል፡፡

በደስታ ሮቦት የፕሮግራሚንግ እና የቋንቋ ሥርዓት ላይ ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸውም ተጠቁሟል፡፡

በ5ጂ ኔትዎርክ ቴክኖሎጂ አማካኝነት የተገናኘችው ሮቦቷ ሰው ከሚመስል የፊት ገጽታ ባሻገር የሰዎችን መሠረታዊ እንቅስቃሴዎች ማከናወን እንደምትችል ታውቋል፡፡

# በመዲናዋ ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ 505 ቦታዎች በጥናት ተለይተዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ 505 ቦታዎች በጥናት ተለይተው ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እየተሠራ መሆኑን የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ በበልግ ዝናብ የጎርፍ አደጋ እንዳይከሰት የቅድመ መከላከል ሥራ እየተሠራ መሆኑም ተመላክቷል፡፡

የአዲስ አበባ እሳትና አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዘርፍ ምክትል ኮሚሽነር ይክፈለው ወልደመስቀል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመዲናዋ ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን በጥናት በመለየት የቅድመ መከላከል ሥራ እየተሠራ ነው፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ በሁሉም ክፍለ ከተማ 221 ለእሳት፣ 218 ለጎርፍ፣ 27 ለትራፊክ አደጋ እና 17 ለመሬት መንሸራተት አደጋ ተጋላጭ የሆኑ በድምሩ 505 ቦታዎች በጥናት መለየታቸውን አስታውቀዋል፡፡

በተጋላጭነት ደረጃ 341ዱ ከፍተኛ፣ 147ቱ መካከለኛ 17ቱ ደግሞ ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸው፤ አደጋዎችን ቀድሞ ለመከላከልና ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

እንደ ምክትል ኮሚሽነሩ ገለጻ፣ በተለዩት ቦታዎች እንደ ችግሩ ስፋት ቅድሚያ በመስጠት የጥናት ውጤቱን ወደ ተግባር ለመቀየር በትኩረት እየተሠራ ይገኛል፡፡ በከተማዋ እየተከናወነ ባለው የኮሪደር ልማት አማካኝነት የመንገድ ማስፋፊያ መሠራቱ፣ በላስቲክ ቤቶች የሚኖሩ ዜጎችን ወደ ተሻለ ቦታ መዛወራቸው እንዲሁም በመንገዶች ላይ የውኃ ማፋሰሻ ቱቦዎች እንደ አዲስ መሠራታቸው አደጋን ለመከላከል ከፍተኛ ጠቃሜታ ይኖረዋል ብለዋል፡፡

የተለያዩ አደጋዎች ሲያጋጥሙ ቦታው ድረስ በመሄድ አደጋን የመከላከል ሥራ የሚሠሩ በማዕከልና በቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የተቋቋመ ቡድንና ተሽከርካሪ መኖሩን አመላክተዋል፡፡ በተጨማሪም እሳትና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ሲያጋጥሙ ምላሽ የሚሰጥ ሲሆን፤ አደጋዎች ሲያጋጥሙ በ939 ወይም 0111555300 ላይ በመደወል አፋጣኝ መፍትሔ ማግኘት እንደሚችሉ አስገንዝበዋል፡፡

የጎርፍ አደጋን በሚመለከት በ2015 በጀት ዓመት ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ ከሆኑ 284 ቦታዎች መካከል 168ቱ የከፍተኛ ደረጃ ተጋለጭ እንደነበሩ አስታውሰው፤


ይክፈለው ወልደመስቀል

ኮሚሽኑ ከመንገዶች ባለሥልጣን፣ ከውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ ከፅዳት አስተዳደር፣ ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንን ሌሎች ባለድርሻ ተቋማት ጋር በመተባበር ለከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ከነበሩት ውስጥ ለ105ቱ ቦታዎች መፍትሔ መስጠት መቻሉን አብራርተዋል፡፡

አሁን ላይ ከባለፈው ዓመት መፍትሔ ሳያገኙ የተዛወሩና በተያዘው በጀት ዓመት የተለዩ ለከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ 135 ቦታዎች መኖራቸውን ገልጸው፤ ለነዚህ ቦታዎች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት የድጋፍ ግንብ የመሥራት፣ የውሃ መፋሰሻ መስመሮችን የማፅዳትና ሌሎች የቅድመ መከላከል ሥራዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

የፍሳሽ ማስወገጃ በበቂ ሁኔታ አለመኖሩ፣ የፍሳሽ ማስወገጃዎች በግንባታ ተረፈ ምርትና በተለያዩ ቆሻሻዎች መዘጋታቸው በአዲስ አበባ ለጎርፍ አደጋ ምክንያት መሆናቸውን አመልክተው፤ በወንዝና የውሃ መፋሰሻ መስመሮች ላይ የተለያዩ ቆሻሻዎችን በመጣል ለጎርፍ አደጋ መከሰት ምክንያት እየሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አስጠንቅቀዋል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች መኖሪያቸውን ወንዝ አካባቢ የመሠረቱ ዜጎች ለአደጋው የመጋለጥ እድላቸው ሰፊ በመሆኑ ከመንግሥትና ከክፍለ ከተማው የሚሰጠውን የመፍትሔ ሃሳብ በመቀበል ተባባሪ ሊሆኑ እንደሚገባም ጨምረው ገልጸዋል፡፡


ፎቶ ዳኜ አበራ

አቶ ግፋወሰን ደሲሳ

# ኤጀንሲው ከአገልግሎት ክፍያ 4 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ሰበሰበ

## -በ190 ሚሊዮን ብር ሕንፃዎቹን ሲያድስ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- የበጀት ዓመቱ ከተጀመረ ወዲህ ለደንበኞች ከሚሰጠው አገልግሎት 4ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡ እስከ ሰኔ 2016 ማብቂያ ድረስ ሕንፃዎቹን ለማደስም 190 ሚሊዮን ብር ወጪ አደርጋለሁ ብሏል፡፡

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ግፋወሰን ደሲሳ በተለይም ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፤ በከተማዋ ሁለተኛ ገቢ የሚያስገባው የአዲስ አበባ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በ2015 በጀት ዓመት 4 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ገቢ መሰብሰቡን አስታውሰው፤ በዚህ በጀት ዓመት ስድስት ቢሊዮን ለመሰብሰብ አቅዶ እየሠራ ነው፡፡ ከአገልግሎት አንፃርም በዓመት 133ሺ ተገልጋዮችን በሲስተም እያስተናገደ ነው፡፡ ይህም የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን በፍጥነት በመመለስ ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ከክፍያ አንፃር ወቅቱን የዋጀ የክፍያ ሥርዓት መተግበር ግድ ይላል ያሉት አቶ ግፋወሰን፤ ለማኅበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ፋይዳ ያላቸውን ተግባራት የሚከናወኑት በተሰበሰበው ገቢ ልክ ነው፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው ጊዜውን የዋጀ የአገልግሎት ክፍያ ሥርዓት እንደሚከተልም አመልክተዋል፡፡

ኤጀንሲ ዘመናዊ የካዳስተር ሥርዓት ለመገንባት እየተጋ መሆኑን የገለፁት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ለአሠራር ምቹ እንዲሆን ብሎም ባለሙያዎችና ደንበኞች ምቹ ምሕዳር ላይ እንዲገለገሉ ኤጀንሲው ሕንፃዎቹን በዚህ ዓመት ያድሳል፡፡

በአስሩም ክፍለ ከተሞች ላይ ያሉን ሕንፃዎች የተገነቡት ከ13 ዓመት በፊት መሆኑን ያስታወሱት አቶ ግፋወሰን፤ በእነዚህ ዓመታት ጥገና አልተደረገላቸውም፡፡ «አሁን ባለው ሁኔታ ሕንፃዎቹ መታደስ ስላለባቸው ለከተማ አስተዳደሩ 190 ሚሊዮን ብር ለዕድሳት እንዲፈቀድልን ጠይቀናል» ብለዋል፡፡

የቅድመ ጥናት ሥራዎችም ተጠናቀዋል፡፡ የፋይናንስ ቢሮው ጨረታው አውጥቶ በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ተፈቅዶልን ወደ ሥራ እየገባን ነው» ብለዋል፡፡ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ገለልተኛ አካላት በየሳይቱ ሄደው ጥናት ማካሄዳቸውን እና ለዕድሳቱም 190 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል፡፡

ሕንፃዎቹ ዕድሳት ተደርጎላቸው ወደ ሥራ እንድንገባ የከተማ አስተዳደሩም ድጋፍ እያደረገልን ነው ያሉት አቶ ግፋወሰን፤ ይህን የማስፈፀም ጉዳይ ደግሞ የእኛ፣ የዲዛይንና ግንባታ ባለሥልጣን እና የፋይናንስ ቢሮ ነው፡፡ ዕድሳቱ እስከ ሰኔ 2016 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ ነው የተናገሩት፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የዕቅድና በጀት ዳይሬክተር ተወካይ ወይዘሮ ቅድስት መከተ በበኩላቸው፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከአገልግሎት ክፍያ 4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 4ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን ተናግረዋል፡፡

የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ ተብሎ በአዋጅ 22/2002 ዓ.ም የተቀቋቋመ ሲሆን፤ የአዲስ አበባ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የሚለውን ስያሜ ደግሞ በአዋጅ 45/2007 ማግኘቱ ታውቋል፡፡

# ምርትና ምርታማነትን የሚያሳድጉ 50 ቴክኖሎጂዎች የማፍለቅ ሥራ እየተሠራ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ በዓመት 50 የሚደርሱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማፍለቅ ታቅዶ ተጨባጭ ሥራ እየተሠራ ነው ሲል የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አስታወቀ::

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ዳሬክተር ፈቶ ኢስሞ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ በዓመት 50 የሚደርሱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማፍለቅ ታቅዶ በተሠራው ሥራ ተጨባጭ የምርምር ውጤቶች እየተገኙ ነው::

ኢንስቲትዩቱ ምርትና ምርታማነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ እየሠራ ባለው የምርምር ሥራ በዓመት 50 ቴክኖሎጂዎችን ያፈልቃል፤ አንድ የቴክኖሎጂን ለማፍለቅ ከአስር እስከ ከሃያ ዓመት በላይ ሊወስድበት ይችላል ብለዋል::

የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሀገሪቱን የግብርና ምርትና ምርታማነት የሚያሳድጉ የተለያዩ ጥናቶችን በመሥራት ማኅበረሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ እየተሠራ ባለው የምርምር ሥራ ከአፍሪካ ቀዳሚ ነው ሲሉ ተናግረዋል::

ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅ፣ የማባዛትና ወደ ማኅበረሰቡ ተደራሽ የማድረግ ሥራ የተጀመረው ከዛሬ 60 ዓመት በፊት መሆኑን አውስተው፤ ቴክኖሎጂን በምርምር ማፍለቅ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁኑ ዓመት ድረስ 3 ሺህ ቴክኖሎጂዎች በምርምር መገኘታቸውን ተናግረዋል::

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ የተገኙት 3 ሺህ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ወደ ማኅበረሰቡ ተደራሽ ተደርገው ጥቅም ላይ በመዋላቸው የሀገርን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ባለው ሂደቱ ውስጥ ትልቅ ውጤት አስገኝተዋል::

የሀገርን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የግብርና የምርምር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው፤ በምርምር ቴክኖሎጂን ለማፍለቅ፤ ለማላመድና ለማኅበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ በትኩረት እየሠራን ነው፤ ይህም ምርታማነትን እያሳደገ ነው ሲሉ ገልጸዋል::

የሀገሪቱ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆነውንና ከ70 በመቶ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል እየፈጠረ የሚገኘውን ግብርና ለማዘመንና ለማሳደግ በ12 ዘርፎች ላይ ማለትም በቴክኖሎጂ፣ በሰብል፣ በተፈጥሮ ሀብት፣ በእንስሳትና በሌሎች መስኮች ላይ የተለያዩ ምርምሮች እየተሠሩ ይገኛሉ ሲሉ አብራርተዋል::

ተቋሙ የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ እየሠራው ባለው ቴክኖሎጂን የማፍለቅ ሥራ ሀገሪቱ የዛሬ 30 ዓመት ታገኘው የነበረው ምርት በእጥፍ እንዲያድግ አድርጓል ብለዋል::

ኢንስቲትዩቱ ቴክኖሎጂን የማፍለቅ ሥራ ሲሠራ ከማኅበረሰቡ ጋር በመናበብና በመነጋገር ነው፤ በግብርናው ላይ የሚታዩ ችግሮች ከማኅበረሰቡ ወደ ተቋሙ ይመጣሉ፤ ተቋሙ ችግሮችን ተቀብሎ ለመፍታት ቴክኖሎጂን የማፍለቅ ሥራ ይሠራል፤ የሚሠራውም የምርምር ሥራ የማኅረሰቡን ችግር የሚፈታና ምርታማነትን የሚያሳድግ መሆኑን አመልክተዋል::

---

## በኢድ አልፈጥር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ ሼህ ሁሴን በሽር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት:: ሕዝበ ሙስሊሙ የረመዳን ወር ከሌሎች ጊዜያት በተለየ መልኩ የተቸገሩትን በመርዳት አሳልፏል:: የረመዳን ወርና በኢድ አልፈጥር በዓል የታየውን መደጋገፍና መተባበርም የሁልጊዜ ተግባር ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል::

በርካቶች በረመዳን ወር የተቸገሩትን በገንዘብና የሞራል ድጋፍን ሲያደርጉ ቆይተዋል ያሉት ሼህ ሁሴን፤ አሁንም በዓሉን ከተቸገሩት፣ የሚለበስና የሚቀመስ ከሌላቸው ጋር ተካፍሎ ማሳለፍ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል::

ኢድ አልፈጥር ሲከበር በምስጋና፣ በተግባር በመረዳዳት፣ የጋራ እሴቶችን በሚንፀባረቁበት መልኩ ሊሆን እንደሚገባው አስገንዝበው፤ ኢድ አልፈጥር አንዱ ከሌላው የሚገናኝበት፣ የሚተዋወቅበትና ለነገ አለኝታነቱ የሚገልጽበት በዓል መሆኑን ገልጸዋል::

መላው ሕዝበ ሙስሊም በሀገር የሰላም አጀንዳ ላይም የበኩሉን አስተዋፅዖ ሲያደርግ ቆይቷል ያሉት ሼህ ሁሴን፤ የጋራ በሆኑት ሀገራዊ የሠላም፣ ልማትና ሌሎች አጀንዳዎች እጅ ለእጅ በመያያዝ ማስቀጥልና መሳተፍ እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል::

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የማኅበራዊ ጉዳይ አማካሪ ኡስታዝ አሕመዲን ጀበል በበኩላቸው፤ በረመዳን ጾም የታየው የመረዳዳት፣ የመተዛዘን መልካም ሥራዎች ሊቀጥሉ ይገባል::

ኢድ አልፈጥር ሙስሊሞች ከሚያከብሩት ታላላቅ በዓላት መካከል አንዱ ነው ያሉት ኡስታዝ አሕመዲን፤ በዓሉን ከቤተሰብ ጋር ያለው ለሌለው አካፍሎ ይከበራል ብለዋል::

የረመዳን ወር በርካታ የበረከት ሥራዎች ሲሠሩበት የነበረ ወር መሆኑን አውስተው፤ በተለይም የፆም፣ የስግደትና የምጽዋት ሥራዎች በስፋት መሠራታቸውን ገልጸዋል::

በረመዳን የተጀመሩ መልካም ሥራዎች በተለያየ መልኩ ይቀጥላሉ:: ረመዳን ተፈታ ተብሎ የሚቋጭ አለመሆኑን የገለጹት አማካሪው፣ በተመሳሳይ መልኩ መልካም ተግባራት ይቀጥላሉ ብለዋል::

የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሳቢር ይርጉ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ያሉበት በመሆኑ ሀገርን ለማስቀጠል ተባብሮ መሥራት ያስፈልጋል::

ዘንድሮው የኢድ ሰላት በርካታ ሙስሊሞች የታደሙበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢድ አልፈጥር ሲከበር እያንዳንዱ ሰው በሚያስተዳድራቸውን ቤተሰብ ልክ ለተቸገሩ ወገኖች ስጦታ እንደሚሰጥ ገልጸዋል::

ኢዱ ሲከበር የተቸገሩ ሰዎች ከሌሎች ጋር ተደስተው እንዲያከብሩ ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ሳቢር፤ ረመዳን የታየው መደጋገፍ፣ መተባበር፣ ያለው ለሌለው መስጠት ተግባር ከረመዳን በኋላም ባሕል ሊሆን ይገባል ብለዋል::

እስላም የሠላም ብቻ ሳይሆን የአብሮነትም ተምሳሌት መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች ያሉበት በመሆኑ ሀገርን ለማስቀጠል ተባብሮ መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል::

ሁሉም የራሱን እሴት ጠብቆ እምነቱ የሚያዘውን አክብሮና የሌላውንም እምነት እውቅና ሰጥቶ መኖር ተገቢ መሆኑን በመግለጽ፤ ሀገሪቱን በመተባበር ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ማድረስ እንደሚቻል ገልጸዋል::

## "ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን የታጠቁ ኃይሎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አስታወቀ:: ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችም መንግሥት በሀገሪቱ ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን ለሚያደርገው ጥረት ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚገባ አመልክተዋል::

የጋራ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ አቶ ደስታ ዲንቃ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሠላም የጋራ እሴትና ዋስትና መሆኑን በመረዳት ከመንግሥት ጀምሮ እያንዳንዱ ዜጋ ሰላም ፈላጊ መሆን አለበት::

መንግሥት በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ለሠላም መስፈን ቅድሚያ በመስጠት የሠላም መድረኮችን በማመቻቸት በመሣሪያ የሚፋለሙ ኃይሎችን ወደ ሠላም ለማምጣት ቁርጠኛና ዝግጁ መሆን እንዳለበት አስታውቀዋል::

የታጠቁ ኃይሎች የሰጥቶ መቀበል መርሕን በማወቅና በመተግበር ጥያቄዎችን በውይይትና በድርድር እንዲመለሱ ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል::

አሁን ላለውና ለተተኪው ትውልድ ዘላቂ ሠላም የሰፈነባት ሀገር ለማስረከብ እና ታሪካዊና ነባራዊ የፖለቲካ ቁርሾዎችን ለመፍታት ብርቱ ጥረት ማድረግን እንደሚጠይቅ ገልጸው፤ መንግስት የታጠቁ ኃይሎችን ጥያቄ በማዳመጥና በውይይት ሠላምን ማስፈን ይገባል ነው ያሉት::

የፖለቲካ ፓርቲዎች ከገዢው ፓርቲ ጋር በመተባበር በሀገሪቱ ያሉትን ልዩነቶች በሕግ አግባብና በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ሊሠሩ እንደሚገባ ገልጸው፤ ፓርቲዎቹ መንግሥት ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር፣ ለፖለቲካ ምሕዳሩ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እና በሀገሪቱ ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን የሚያደርገውን ጥረት መደገፍ እንዳለባቸው አብራርተዋል::

የታጠቁ ኃይሎችም ጥያቄቸው የሚመለሰው በውይይትና በድርድር መሆኑን በመረዳት ለሠላም ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው አስገንዝበዋል::

እንደ አቶ ደስታ ገለጻ፣ የታጠቁ ኃይሎች ጥያቄያቸው የሚመለሰው በጦርነት ሳይሆን በውይይትና በድርድር መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል:: ትጥቅ ያነገቱ አካላትን ጨምሮ፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የሲቪክ ማኅበራት፣ የብዙኃን መገናኛዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ታዋቂ ሰዎች እና ሁሉም ዜጎች በየአካባቢያቸው ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍን የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ብለዋል::

የጋራ ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሠላምን ለማስፈን እቅድ በማውጣት በፖለቲካ ፓርቲዎችና በመንግሥት መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ምቹ ሁኔታን የመፍጠርና ሌሎች ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን አቶ ደስታ አስረድተዋል::

የጋራ ምክር ቤቱ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች ያሉትን ግጭቶች በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት መንግሥትንና ተፋላሚ ኃይሎችን የማነጋገር ሥራ እየሠራ መሆኑን አንስተው፤ ከፖለቲካ ፓርቲዎች መብትና ጥያቄ ጋር ተያይዞ የታሰሩ ሰዎችን የማስፈታት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕጋዊ መንገድ ተመዝግበው እንዲሠሩና ለሠላም ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ፣ ግጭት በተነሳባቸው አካባቢዎች ሠላም የማስፈንና ሌሎች በርካታ ሥራዎችን ማከናወን እንደተቻለ ገልጸዋል::

መንግሥት የጋራ ምክር ቤቱ የ69 የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚወክል መሆኑን ተረድቶ ድጋፍ አለማድረጉ፣ የታጠቁ ወገኖች ሠላምን አለመፈለጋቸውና ጥያቄቸውን በጉልበት ለማስመለስ መፈለጋቸው፣ በቂ በጀትና የሰው ኃይል አለመኖሩ ምክር ቤቱ ሀገራዊ ተልዕኮውን እንዳይወጣ ተግዳሮት እንደሆነበት ጠቅሰዋል::

## ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ እስከ አሁን ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መሰብሰብ ተችሏል:: ከዚህም ከ50 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ስንዴ ወደ ጎተራ እንዲገባ ተደርጓል::

የአዝመራ ስብሰባው በእቅዱ መሠረት እየተፈጸመ መሆኑን አቶ ከበደ ጠቅሰው፣ በአንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የሚገኘውን የስንዴ አዝመራ ለመሰብሰብም የተጠናከረ ሥራ እየተከናወነ መሆኑንም አስታውቀዋል::

ዘንድሮ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ በሁሉም ክልሎች እየተካሄደ መሆኑን ጠቅሰው፣ እስከ አሁን በአብዛኛው አዝመራው እየተሰበሰበ ያለው ከቆላማው አካባቢ መሆኑን ገልጸዋል::

የቆላማ አካባቢው የመስኖ ስንዴ ልማት አዝመራ ቶሎ የመድረስ ባሕሪ እንዳለው ተናግረው፣ እስከ አሁን በአብዛኛው የዚህ አካባቢ አዝመራ እየተሰበሰበ መሆኑን ጠቁመዋል::

በቦረና፣ በጉጂ፣ በሐረርጌ፣ በምሥራቅ ሸዋ፣ ወዘተ. አካባቢዎች የአዝመራ ስብሰባው በተጠናከረ መልኩ እየተፈጸመ መሆኑን ገልጸዋል::

በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች አዝመራው ያልደረሰበት ሁኔታ እንዳለም ጠቅሰው፣ አዝመራው በደረሰባቸው ደጋና ወይና ደጋ አካባቢዎችም አሁን እየጣለ ካለው ዝናብ ጋር ተያይዞ ትንሽ ሊዘገይ ቢችልም፣ የአዝመራ ስብሰባው ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል::

ዘንድሮ ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሚጠበቀውን 120 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ምርት የማግኘት እቅድ እናሳካለን ብለን እየሠራን ነው ብለዋል::

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የአዝመራ አሰባሰቡ በጥሩ ደረጃ የሚገኝ ሲሆን፣ አዝመራው በባሕላዊ መንገድና ኮምባይነር እየተሰበሰበ ይገኛል:: ለአዝመራ ስብሰባው ቴክኖሎጂ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክቷል::

በአጠቃላይ ምርት እየተሰበሰበ ያለበት መንገድ በባሕላዊና በኮምባይነር መሳ ለመሳ በሚባል ደረጃ መሆኑን ጠቅሰው፣ በኦሮሚያ ክልል አዝመራው በስፋት እየተሰበሰበ ያለው በኮምባይነር መሆኑን አስታውቀዋል::

የመስኖ ልማቱ በስፋት እየተካሄደ ያለው በኦሮሚያ ክልል መሆኑን የገለጹት አቶ ከበደ፣ በክልሉ ወደ ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር ማሳ በስንዴ ዘር መሸፈኑን አመልክተዋል::

ከዓመት ዓመት የግብርና ቴክኖሎጂን የመጠቀሙ ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱን ጠቅሰው፣ ከዚህም ግብርናን ማዘመን የሚለውን በተግባር እንደሚያሳይ ተናግረዋል::

በኦሮሚያ፣ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ፣ በደቡብና በመሳሰሉት አካባቢዎች ኮምባይነር ለመጠቀም ምቹ ሁኔታዎች ከመኖራቸው በተጨማሪ የምርት ብክነትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂው በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉን ገልጸዋል::

እስከ አሁን ባለው የአዝመራ ስብሰባ እየተሳተፈ ያለው አርሶ አደሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ አርሶ አደሩ በጋራ በተለይ በኩታ ገጠም እርሻዎች ተቀናጅቶ አዝመራ እየሰበሰበ መሆኑን አመልክተዋል::

በኩታ ገጠም አካባቢዎች በኮምባይነር፣ በሌሎቹ አካባቢዎች ደግሞ በደቦና በመሳሰሉት በተቀናጀ መልኩ እየተሰበሰበ መሆኑን አስታውቀዋል:: ይህም ቅንጅት በቀጣይም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ በአዝመራ ስብሰባው የባለድርሻ አካላት ሚና ከፍተኛ ነው:: የሚመለከታቸው የልማት አጋሮች፣ የከተማና የወረዳ አስተዳደሮችና ማኅበረሰቡ ለምርትና ምርታማነት እድገት ያላቸው አስተዋፅዖ ከፍተኛ እንደመሆኑ ለአዝመራ ስብሰባው ተቀናጅተው ድጋፍ ማድረጋቸው ወሳኝ ይሆናል::

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በ2016 የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሦስት ሚሊዮን ሄክታር ማሳ በዘር በመሸፈን 120 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑ ይታወቃል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከአዝመራ ስብሰባው ጎን ለጎን የበልግ ማሳ ዝግጅቱና ማሳን በዘር የመሸፈኑ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠሉን ሥራ አስፈጻሚው አስታውቀዋል:: ጥር የካቲትና መጋቢት ወራት ለበልግ ሥራው ርብርብ የሚደረግበት መሆኑን አቶ ከበደ ጠቅሰው፣ አሁን እየጣለ ያለው ዝናብ ለዚህ የበልግ እርሻ ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል::

በዘንድሮው የበልግ ወቅት ወደ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር የሚደርስ መሬት ለማረስና ወደ 80 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት መታቀዱን አስታውቀዋል:: እስከ አሁን ባለው አፈጻጸም ከ800 ሺ. ሄክታር በላይ መሬት በዘር መሸፈኑንም ገልጸዋል::

## ኢትዮጵያ የሱዳን ጦርነት በአፍሪካ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኢትዮጵያ ያላትን ታሪካዊ ተደማጭነቷን ተጠቅማ የሱዳን ጦርነት በአፍሪካ ኅብረት እንዲፈታ ኃላፊነቷን ልትወጣ ይገባል ብለዋል::

ጦርነቱ በቀጣናው ከፍተኛ የሆነ የስደተኛ ጫና አምጥቷል:: ይህም የደኅንነት ስጋቶችን ይፈጥራል ያሉት አቶ ቅዱስ፤ አካባቢው የአሸባሪዎችና ከሕገ ወጥ የመሣሪያ ዝውውር ማዕከል እንዳይሆን ኢትዮጵያ ያላትን ታሪካዊ ተደማጭነቷ ተጠቅማ የሱዳንን ጦርነት በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር ችግሩ እንዲፈታ ኃላፊነቷን ልትወጣ እንደሚገባ ገልጸዋል::

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፤ የሱዳን ጦርነት ትኩረት ተነፍጎታል፤ ነገር ግን ቀጣናውን ወደማይወጣው ቀውስ ውስጥ እንዳይገባ ችግሩን በውይይት መፍታት ያስፈልጋል:: ለዚህ ደግሞ ሁሉም ሀገር በግሉ የሚፈታው ችግር ስለሌለው የአፍሪካ ኅብረትና የኢጋድ ተፅዕኖ ፈጣሪነት በማጠናከር በውይይት መፍታት ይገባል:::

ኢትዮጵያ እንደ አፍሪካ ኅብረት መቀመጫነቷና ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ እንደምታምን ሀገር ግጭቱ እንዲፈታ ጥረት ማድረግ እንዳለባት አመልክተው፤ በዓለም አቀፍና በአፍሪካ ደረጃ ያላትን ተፅዕኖ ተጠቅማ ትኩረት የተነፈገውን ጦርነት ዓለም ትኩረት እንዲሰጠው ማድረግ ይኖርበታል ብለዋል::

አሁንም ትልቅ ቀጣናዊ ችግር እየፈጠረ መሆኑን በማሰብ መፍትሔ የሚሰጥበትን መድረክ የማመቻቸት ግዴታ እንዳለባት ተናግረዋል::

ጦርነቱ የሁለት ተፋላሚዎች ብቻ ሳይሆን ከበስተጀርባው ብዙ እጅ ያለበት በመሆኑ ቀላል አይደለም ያሉት አቶ ቅዱስ፤ ችግሩ ካልተፈታ ቀጣናው የሽብርተኞች መናኸሪያ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው:: የአፍሪካ ቀንድ ትልቅ የሕገ-ወጥ የመሣሪያ ሽያጭ መናኸሪያ ሊሆን ይችላል:: ጎረቤት ሀገራት የችግሩን አሳሳቢነት ተገንዝበው በኢጋድ ጥላ ስር ይህም ካልተሳካ በአፍሪካ ኅብረት ስር መፍትሔ ሊሰጠው እንደሚገባ ተመራማሪው ገልጸዋል::

እስካሁን አፍሪካ ኅብረት ካለው የአሕጉራዊ ስም አንጻር የሠራው ሥራ አለ ማለት አይቻልም የሚሉት ተመራማሪው፤ በአሁኑ ጊዜ የሱዳን ግጭት «የተረሳው ጦርነት» እየተባለ ነው:: ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች የሱዳንን ቀውስ የዩክሬን- ሩሲያ እና የእስራኤልና የጋዛን ያህል ሽፋን የለውም:: ይህ የሚያሳየው ዓለም እንደረሳው አስገንዝበዋል::

ጦርነቱ እንደ አፍሪካ በርካታ ሕልሞችን ይጎዳል ያሉት ተመራማሪው፤ ቀጣናውን በንግድና በኢኮኖሚ ለማስተሳሰር የሚደረገውን ጥረትም ትልቅ ፈተና እንደሆነ ጠቁመዋል::

የሱዳን ኢኮኖሚያዊ ድቀት መልሶ ኢትዮጵያን የሚጎዳ በመሆኑ ጦርነቱ በፍጥነት መፍትሔ እንደሚያሻው ገልጸዋል::

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፃምና የበዓል ሰሞን አብሮነትና መተሳሰብ፣ በሀገር ሠላምና ልማት ጉዳይ ሳይም ሲደገም ይገባል!

ሃይማኖት፣ እንደ ማኅበረሰብም፣ እንደ ግለሰብም ከፍ ያለ የመተሳሰብ፣ መደጋገፍና የአብሮነት እሴቶችን የሚያጎናጽፍ መንፈሳዊ ኃይል አለው:: ይሄ መንፈሳዊ ኃይል ደግሞ በግለሰቦች አልያም በማኅበረሰቦች መካከል የሚኖርን የእርስ በእርስ መስተጋብር ቀናና ሠላማዊ የሚያደርግ ነው::

ይሄው ሃይማኖታዊ ልዕልናም ነው በተለይም በሃይማኖታዊ በዓላት ወቅት በሰው ልጆች መካከል ከፍ ያለ የመተሳሰብና መደጋገፍ እሴትን እንዲገለጥ የሚያደርገው:: ያሳለፍነው ወርሐ መጋቢትም፣ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በዚህ መልኩ የሚገለጡ አያሌ ተግባራት የታዩበት፤ በተለይም በእስልምናም ሆነ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በጋራ የጾሙበት ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከፍ ያለ መንፈሳዊ ተግባራት ሲከናወኑበት ቆይተዋል::

የየሃይማኖቶቹ አስተምህሮቶች በሚፈቅዱትና በሚያዝዙት መጠንም አማኙ ሲተጋ፤ ለሰው ልጅ ያለውን ፍቅርና ክብርም ሲገልጥ ቆይቷል:: ይሄ እንደተጠበቀ ሆኖ ደግሞ፣ ትናንት መቋጫውን ባደረገው የታላቁ ሮመዳን ወር በእለተ ኢድ አልፈጥር፣ በሕዝበ ሙስሊሙም ሆነ በሌላው ኢትዮጵያዊ ዘንድ የነበረው መንፈስ ልዩ ነበር::

ሕዝበ ሙስሊሙ በጋራ ኢድን ሰግዶ በጋራ በዓሉን ከማሳለፍ ባለፈ፤ አንዱ ከሌላው ሲያደርግ የነበረው የመተሳሰብና አብሮነት ሁነት የኢትዮጵያውያንን የመተሳሰብ ልዕልና የገለጠ ሆኗል:: ሕዝበ ሙስሊሙ ብቻም ሳይሆን፣ የሌሎች እምነቶች ተከታዮች ጭምር በየጉርብትናው የነበረው ማኅበራዊ መስተጋብር፣ ለበዓሉ ድምቀትም፤ ለኢትዮጵያውያን የአብሮነት እሴትም ዘላቂነት ከፍ ብሎ የሚናገር ተግባር ነበር::

ዜጎቿ በየሃይማኖታዊ በዓላት ወቅት ያላቸው ይሄን መሰሉ የመልካምነት ተግባር ደግሞ 99 በመቶ ሕዝቧ አማኝ (ሃይማኖተኛ) ነው ለሚባልላት ኢትዮጵያ ቀጣይ የአብሮነት መንገዷን በመልካም እንዲገለጥ የሚያስችል ነው::

ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ ግን፤ ሃይማኖት እና ሃይማኖተኛ በመልካም ምግባር ሊተሳሰሩ የሚገባቸው በሃይማኖታዊ ወራት አልያም በዓላት ወቅት ብቻ ነውን? የሚለው ዐቢይ ጉዳይ ነው:: ምክንያቱም ዛሬ ላይ የሚታዩ የሠላም መደፍረሶች፤ መፈናቀልና የኑሮ ጫናዎች እየተፈጠሩ ያሉት በእኛው ሃይማኖተኛ ነን በምንል፤ በእኛው ፆምና ኃይማኖታዊ በዓላትን እየጠበቅን መልካም በምንሆን ሃይማኖተኞች ነው::

ይሁን እንጂ አንድ ሃይማኖተኛ፣ ሃይማኖታዊ አስተምሕሮው የሚያዝዘው ቀን እና ወር መርጦ፣ ጊዜ ለይቶ መልካም አልያም ክፉ እንዲሆን አይደለም:: ይልቁንም በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ የሰው ልጆች እርስ በእርሳቸው እንዲዋደዱ፣ እንዲረዳዱ፣ እንዲተሳሰቡ፣ አንዳቸው ለአንዳቸው አለኝታ እንዲሆኑ፣ በሠላምና በፍቅር አብረው እንዲኖሩ ነው::

አንድ አማኝ ደግሞ፣ በትክክል የእምነቱን መንገድ የሚከተል፤ ትዕዛዙንም ለመፈጸም ራሱን ያስገዛ ከሆነ፣ እነዚህን ነገሮች ገንዘቡ ሊያደርግ የተገባ ነው:: ከሰው ልጆች ጋር ፍቅርና ኅብረትን ሊያጸና እንጂ ፀብና መለያየትን ሊያነግስ አይገባውም:: ለሰው ልጆች መልካም ነገርን ከማሰብና ከማድረግ የዘለለ፣ በሰው ልጆች ላይ ክፋትንና ጥቃትን ለማድረስ ማሰብም ሆነ መንቀሳቀስ አይገባውም::

አንድ ሃይማኖተኛ፣ ለሰው ልጆች ሠላምና አብሮነት ብቻ ሳይሆን፤ ለሰው ልጆች ሠላማዊና ምቹ የኑሮ ከባቢ እንዲፈጠር አብዝቶ ይተጋል:: የሰው ልጆች ሠላማዊ ኑሮን፣ የተመቻቸ ከባቢን ማግኘት የሚችሉት ደግሞ፣ የሚኖሩባት ሀገር ሠላሟ የተጠበቀ፣ ልማቷም የተሳለጠ መሆን ሲችል ነው::

በመሆኑም የትኛውም ሃይማኖተኛ፣ በፈጣሪው አምሳል ለተፈጠረ የሰው ልጅ መልካም ነገርን ሲያስብ፤ የሚኖርበትን ከባቢ ሠላማዊም፣ ምቹም በማድረግ ሂደት ውስጥ ድርሻዬ ምንድን ነው ብሎ ራሱን መጠየቅ፤ በዛው ልክም ለዚህ መልካምነት መትጋት ይጠበቅበታል::

በዚህ ረገድ ባለፈው ወር በፆም እና ትናንትንም በኢድ አልፈጥር ዕለት የታዩ የመልካምነት፣ የመተሳሰብ፣ የመደጋገፍ፣ የመረዳዳትና የአብሮነት ሁነቶች፤ በጊዜ እና በሁኔታ ሳይታጠሩ በቀጣይነት መገለጥ ይኖርባቸዋል:: እነዚህ መገለጦች ደግሞ ለሰው ልጆች ካለን መልካም እሳቤ ጋር የተቆራኙ ሊሆን ያስፈልጋል::

ምክንያቱም መልካም ተግባር የሚመነጨው ከልብ ሀሳብ ነው:: የልባችን ሀሳብ ሠላም ሲሆን፣ ስለ ሠላም እንተጋለን፤ የልባችን ሀሳብ ፍቅር ሲሆን፣ ስለ ፍቅር እንተጋለን፤ የልባችን ሀሳብ የዜጎች እና የሀገር መበልጸግ ሲሆን፣ ስለ ሀገርና ሕዝብ ብልጽግና እንተጋለን:: በመሆኑም በሃይማኖታዊ በዓላት ወቅት የታዩና የሚታዩ መልካም ተግባራት፤ ከበዓላት ዓውድ ባሻገር ባለው ዘላቂ የሰው ልጆች ሠላም፤ የሀገርም ልማት ላይ እንዲገለጡ ሁሌም አብረውን የሚኖሩና የሚገለጡ ሀብቶቻችን ልናደርጋቸው ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው::በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## ረመዳን፤ እስልምና እና እሴቶቹ

ግርማ መንግሥቴ

ታሪክ እንደሚያስረዳው፣ ነብዩ መሐመድ የእስልምና እምነት በመካና አካባቢው በሚሰበክበት ዘመን በአንዳንድ ቀንደኛ ነጋዴዎች፣ ባለሥልጣናት እና መሰል አካላት ተቃውሞ ሲደርስበት እምነቱ በትክክል የገባቸው ተከታዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ በመላካቸው ምክንያት እስልምና ኢትዮጵያዊና የኢትዮጵያውያን እምነት ሆኗል። መልካም እሴቶቹ ሁሉ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን እሴቶች ናቸው ማለት ነው።

ባለፈው ዓመት ተሾመ ብርሃኑ ከማል የተባሉ ጸሐፊ እንዳሰፈሩት የእስልምና እምነት በዓለም የተሰራጨው በሦስት ዋና ዋና ወቅቶች ሲሆን፤ የመጀመሪያው ከ632-800 ባለው ዘመን ነው:: በዚህ ዘመን እስልምና በኢትዮጵያ፣ በፋርስ፣ በሶሪያ፣ በሰሜንና በምሥራቅ አፍሪካ፣ በስፓይንና በሲሲሊ ተቀባይነት አግኝቷል:: ከዚህ የምንረዳው ከሌሎች ታሪካዊ ዳራዎች በተጨማሪ ኢትዮጵያ እስልምናን ከተቀበሉት አገራት አንዷ ብቻ ሳትሆን ቀዳሚዋም መሆኗን ነው።

ከመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች ሁሉ ከብዙ ሺህ ዓመታት ጀምሮ በፖለቲካና በኢኮኖሚ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን በጠበቀ ማኅበራዊ ግንኙነት የምትታወቀው ኢትዮጵያ፣ ለእስልምና ሃይማኖት ቅርብ እንድትሆን ካደረጉ ምክንያቶች መካከል መሰል መስተግባሮች ከዋነኞቹ ተርታ የሚዘረዘሩ ስለመሆናቸው የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

ከላይ የጠቀስናቸው ጸሐፊም «ኢትዮጵያ በጥንታዊነታቸው ከሚታወቁ የንጉሠ ነገሥት ግዛቶች አንዷ ስትሆን ሥልጣኔዋ ከግብፅ ሥልጣኔ ጋር የተያያዘ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ንጉሥ ሰለሞን የተባለ የሔብሩ ንጉሥና ንግሥተ ሳባ የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ሁለቱን አገሮች አስተሳስረዋል የሚል ታሪክ አለ::

በ3ኛው ክፍለ ዘመን የግሪኩ ቅኝ ገዥ ግብፅን በቅኝ ግዛትነት ይዞ በነበረበት ጊዜ ኪነጥበቡን ወደ ኢትዮጵያም አምጥቶ እንደነበር ይታወቃል:: በዚህ ጊዜ የአይሁዶች ሃይማኖት ለረዥም ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ ተንሰራፍቶ የነበረ ቢሆንም እንኳን ከ330 ጀምሮ ክርስትና ገብቷል:: ምንም እንኳን ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ይህን ያህል ዓመታት ቢወስድበትም በዓረቢያና በኢትዮጵያ መካከል በነበረው ጂኦ-ፖለቲካዊ ቀርቤታ እስልምና ወደ ኢትዮጵያ የገባው በራሱ በሳዑዲ ዓረቢያ እንደተጀመረ በራሳቸው በነቢዩ መሐመድ ዕድሜ ነው::" በማለት ያሰፈሩት ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነውና ወደ ዛሬው ረመዳን በዓል እንለፍ።

ከአምስቱ የእስልምና ማዕዘናት ውስጥ አንዱ የሆነውና ሃያ ዘጠኝ ወይም ሠላሳ ቀናትን የሚዘልቀው ረመዳን በሂጅራ አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር ሲሆን፤ በሙስሊሞች ዘንድ የፆምና ጸሎት ወር ነው:: ጥናቶች እንደሚያሳዩት ረመዳን የሚጀምረው በየዓመቱ ከ10 እስከ 12 ቀናት ቀደም ብሎ ሲሆን፤ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ኢስላማዊው የዘመን አቆጣጠር በጨረቃ የሒጅራ አቆጣጠር ስለተመሠረተ ነው:: ወሮቹ 29 እና 30 ቀናት የሚረዝሙ ናቸው።

ከእምነቱ አስተምሕሮ መረዳት እንደሚቻለው፣ ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከምትጠልቅ ድረስ መፆም ለአቅመ አዳም እና ሄዋን ለደረሱ ሙስሊሞች ፋርድ (ግዴታ) ነው። አልጋ ላይ የዋሉ በሽተኞች፣ መንገደኞች፣ አረጋውያን፣ ጡት አጥቢ እናቶች፣ የስኳር በሽተኞች፣ ወይም የወር አበባ ያላቸው እንስቶች ሲቀሩ ሁሉም ይፆማል።

ከሱቢሀ (ፈጅር) አዛን ቀደም ብሎ በሌሊት (ንጋት) ላይ የሚበላው ምግብ (የቅድመ-ጎሀ ምግብ) ሱሁር እና ምሽት ከመግሪብ አዛን በኋላ የሚፈታበት (የሚፈጠርበት) ምግብ (ፀሐይ ስትጠልቅ ፆም የሚፈታበት ምግብ) ኢፍጣር ይባላል። ይህ እንግዲህ ላለፈው አንድ ወር የዘለቀና በዛሬው እለት የተፈታ ፆም ነው።

ከእምነቱ ተከታይ ወገኖቻችን መረዳት እንደቻልነው፣ የፆም መንፈሳዊ ሽልማቶች (ሰዋብ) በረመዳን ውስጥ እንደሚባዙ ይታመናል። በዚህ መሠረት፣ ሙስሊሞች ከምግብ እና መጠጥ ብቻ ሳይሆን፣ ከትምባሆ ምርቶች፣ ከባለቤታቸው ጋር ፆታዊ ግንኙነት፣ እንዲሁም ከአጠቃላይ መጥፎ ባሕሪያት በመቆጠብ፤ ሰላት እና ቁርዓን መቅራትን በማዘወተር ከንጋት እስከ ፀሐይ መጥለቅ የሚዘልቀውን የፆም ወር ያሳልፋሉ። ይህንን እዚህ መጥቀስ ያስፈለገበት ምክንያት የፆም ወሩ በዚህ መልክ ማለፉን በጨረፍታ ለመጠቆም ሲሆን፤ ቀጥለን የእስልምና እሴቶችን እንመልከት።

ብዙውን ጊዜ ሙስሊሞች በጸሎት፣ በሰላት እና በሰደቃ (ምጽዋት) እንዲሁም ሥነ ምግባራቸውን ለማሻሻል በመጣር ፆሙን ያሳልፋሉ። ይህም በሃዲስ "ረመዳን ሲደርስ የገነት በሮች ይከፈታሉ፤ የሲኦል (ገሃነም) በሮች ይዘጋሉ እና ሰይጣናት ይታሰራሉ።" የሚለውን መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ በሃይማኖቱ ታሪክ ጸሐፍት በተደጋጋሚ ሲጠቀስ ይታያል። እንደ ኢትዮጵያ ባሉና እስልምናና ክርስትና ብዙም ተለያይተው በማይታዩበት ሀገርም ይህ የእለት ተእለት የእምነቱ ተከታዮች ተግባር መሆኑ ይታወቃል። እስላማዊ እሴቶችን በተመለከተም እንደዛው።

የመቻቻል፤ የመረዳዳት፣ አብሮነትና የመከባበር ባሕል የእስልምና ሃይማኖት እሴቶች መሆናቸው ተደጋግሞ የተነገረ ነው። መረዳዳት፣ መከባበርና የታመመን መጠየቅ በእስልምና ኃይማኖት ሕግ የውዴታ ግዴታ ነው። አልፎ አልፎ በሚታዩ የአክራሪነት አስተሳሰቦች በሚፈጠሩ ግጭቶች አንዱ የሌላውን መመኘትና መቀማት በቅዱስ ቁርዓን ፍፁም የተከለከለና የሚወገዝ ነው::

በባለፈው ዓመት የበዓሉ አከባበር ሥነሥርዓት ላይ የጉጂ ዞን ሸሪያ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሼክ ከድር አብዱረህማን "አክራሪነትና ጽንፈኝነት የኃይማኖቱን አስተምሮ የሚጥስ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ነው" ማለታቸው የሚታወስ ነው። "በሃይማኖቱ የተፈቀደና የታዘዘው መቻቻል፣ መረዳዳት፣ አቅመ ደካሞችን መርዳትና አብሮነት ጥንትም የነበረ አሁንም ያለ ወደፊትም የሚኖር የተከበረና የተመረጠ ባሕል" መሆኑንም ነው የገለፁት።

ይህ በሚመለከታቸው በቀጥታ ይገለፅ ከሚል ነው እንጂ ሁላችንም የምናውቀው ከመሆኑ አኳያ ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑን ከመግለፅ ያለፈ እዚህ የምንጨምረው ነገር አይኖርም። በትናንትናው እለት፣ እስልምና የሰላም፣ የፍቅርና የወዳጅነት እምነት እንደመሆኑ ምእመኑ በያሉበት በእነዚሁ እሴቶቻቸው ላይ ተመሥርተው ረመዳንን ያከበሩ ስለመሆናቸው በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል።

ሁለቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች፣ ክርስትና እና እስልምና የተቀደሱና የተባረኩ ወሮች የሚሏቸውን የፆም ወሮቻቸውን (‹‹ዓቢይ ፆም›› እና ‹‹ረመዳን››) በተመሳሳይ ጊዜ በፀሐይ ከመጋቢት 2 ቀን 2016 ዓ.ም (የጨረቃ መጋቢት 1 ቀን 2024/ ዓመተ 2024 የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የፀሐይና የጨረቃ ጥምር ቀመር ሲሆን፤ ከአውሮጳው ጋር አይገናኝም) እና በጨረቃ ከረመዳን 1 ቀን 1445 ዓመተ ሒጅራ ጀምሮ መያዛቸው ይታወቃል። ይህም በወቅቱ በብዙዎች አግራሞትን የጫረ ሲሆን፤ ለበርካታ የሁለቱም ሃይማኖቶች ምእመናን ውስጣዊ ደስታን የፈጠረ፤ ወንድማማችነትን፤ እንዲሁም የሺዎች ዘመናትን አብሮነትን ያንፀባረቀ ሆኖ ማለፉ ይታወቃል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞጂ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ከሩዋንዳ የዘር እልቂት በስተጀርባ

የእርቅ፣ የይቅርታ፣ የፍቅር ተምሳሌት፣ አባት፣ ረቡኒ/ አስተማሪ/ የሆኑት የደቡብ አፍሪካ የፀረ አፓርታይድ ትግል መሪና የነፃዋ ደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው ጥቁር ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላ/ማዲባ/ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1995 ለንባብ በበቃው" Long Walk to Freedom" በተሰኘው ድንቅ ግለ ታሪክ መፅሐፋቸው፤" ሁሉም ሰው ጥላቻን ተምሮ እንጂ ከእናቱ ማህፀን ይዞት አልተወለደም፡፡ ጥላቻን የተማረ አዕምሮ ደግሞ ፍቅርንና እርቅን መማር አይከብደውም" ብለዋል፡፡

በሩዋንዳ በጥላቻ ታውረው የገዛ ዜጎቻቸውን የጨፈጨፉ፤ ስድስት ሚሊዮን አይሁዶች በግፍ የፈጀው ናዚ ሆነ፤ በሀገራችን የተንሰራፋው ጥላቻም ሆነ በየዕለቱ የምናየውን ሰቆቃ የሚፈጽሙት ከእናታቸው ማሕጸን ይዘውት የተወለዱት ሳይሆን ለዓመታት ተቋማዊና መዋቅራዊ ሆኖ የተጋቱት ጥላቻ ውጤት ነው። ማናችንም ብንሆን ጥላቻን ተጋትነው እንጂ ከእናታችን ማሕፀን ይዘነው አልተወለድንም ፡፡

ከእናታችን ማሕፀን ይዘነው ያልተወለድነውን ግን በአንድም ሆነ በሌላ መልክ የተማርነውን ጥላቻ፣ ልዩነትና ቂም በቀል፤ ከአዕምሮአችን ለመሰረዝ፣ ለማጥፋት እንደ ኔልሰን ማንዴላ ካሉ ባለግዙፍ ተክለ ሰብዕና ባለፀጋዎች መማር እንችላለን፡፡ አዎ! ከእነ ማሕተመ ጋንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ ተዝቆ የማያልቅ የይቅርታ መዝገብም መማር ይቻላል፡፡ ለዛውም ጥላቻን ከመማር ይልቅ ፍቅርንና ይቅርባይነትን መማር ይቀላል፡፡ ምክንያቱም ፍቅር ይቅር ባይነት አምላካዊ ሲሆን ጥላቻ ደግሞ ሰይጣናዊ ነው ፡፡

የሰው ልጅ አምላኩ በአምሳሉ የፈጠረው ስለሆነ አዕምሮው ለፍቅር፣ ለይቅርታ ይቀርባል፡፡ ያደላል፡፡ ከማዲባ ወይም የቀድሞው የነፃነት ታጋይና መሪ ማንዴላ ይቅርባይነት ያረጋገጥነው ይሄንኑ ነው፡፡ መቼም ስለ ፍቅር፣ ይቅርባይነት በተነሳ ቁጥር ከፈጣሪ ቀጥሎ ስሙ የሚወሳው ማንዴላ ነው፡፡ ከፍ ብዬ በጠቀስሁት መጽሐፉ ስለ ይቅርባይነት ከፍታና ኃያልነት ፤" ይቅርባይነት ነፍስን አርነት ያወጣል፡፡ ፍርሀትን ያስወግዳል፡፡" ሲል እማኝነቱን፣ ምስክርነቱን ገልጿል ፡፡

ወንድሞች ይቅር በመባባል ነፍሳችንን ከባርነት ነፃ እናውጣ፡፡ በይቅርባይነት ቀይዶ አላላውስ ካለን የፍርሃት ቆፈን እንላቀቅ ፡፡ ወገኖቼ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደልኋችሁ፤ በዚህ ጋዜጣ በምጽፋቸው መጣጥፎች የተቀየማችሁ ብትኖሩ ከእግራችሁ ስር ወድቄ ይቅር እንድትሉኝ እለምናለሁ፡፡ እንዲሁም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የበደላችሁኝንም ከልብ ይቅር ብያለሁ፡፡ ለመንደርደሪያ ያህል ይሄን ካልሁ፤ ሰሞነኛውን የሩዋንዳ የዘር ፍጅት ወይም ጄኖሳይድ 30ኛ ዓመት ሰበብ በማድረግ ብንማርበት በሚል እስያኤል ዘ ኢትኤል፣ "የሩዋንዳ ቆይታዬና የተማርኩት፤" በሚል ያስነበበንን መጣጥፍ ላጋራችሁ ወደድሁ።

ሩዋንዳ ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ውስጥ አንዷ ናት፤ ልክ እንደ ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሀገር ስትሆን አብዛኛውን መልከዓ ምድሯ ተራራማ ቦታ ሲሆን "የሺህ ኮረብቶች ምድር" በመባል ትታወቃለች፡፡ ከአፍሪካ ታላላቅ ሐይቆች አንዱ በሆነው ከምድር ወገብ በስተደቡብ እና ከኪቩ ሐይቅ በስተምሥራቅ የምትገኝ በመካከለኛው አፍሪካ ያለች ትንሽ ወደብ የለሽ፣ ኮረብታማ አገር ነች። እኔ ከተወለድኩበት ታላቁ የስምጥ ሸለቆ የምዕራብ ጫፍ ላይ የምትገኝ በሰሜን ከዑጋንዳ፣ በምስራቅ ከታንዛኒያ፣ በደቡብ ከብሩንዲ፣ በምዕራብ ከዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ (ኪንሻሳ) እና ከኪቩ ሐይቅ ትዋሰናለች።

አገሪቷ 26,338 ኪ.ሜ$^2$ ስፋት ያላት ሲሆን ከሌሎች ሀገሮች አንጻር ስትነጻጸር መቄዶንያ (ሪፐብሊክ) ታክላለች፣ ወይም ደግሞ ከአሜሪካ የሜሪላንድ ግዛት

## ዓለም አቀፍ

**ማኅበረሰቡም ዘርን ያነጣጠሩ ግድያዎችን ሲያይ ዝም ከማለት ብዙ አደጋ ሳይደርስ አፋጣኝ እርምጃዎችንና ጫናዎችን በማድረግ፣ በተለያዩ ጊዜ እንደተፈጠሩት የዘር ፍጅቶች "Never Again" ወይም "በጭራሽ አይደገምም" እያለ ከአይሁዶች እስከ ሩዋንዳ ተመሳሳይ መፈክር ማሰማት ብቻ ሳይሆን በተግባር እንዳይፈጸም ማድረግ ይጠበቅበታል**

በመጠኑ አነስ ያለች ነች፡፡ እ.ኤ.አ 2016 በተገኘ መረጃ መሠረት 11.5 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሲሆን (የሩዋንዳ የሕዝብ ብዛት ከሰሐራ በስተደቡብ ካሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ትልቁ ነው፡፡) ዋና ከተማዋ እና ትልቁ ከተማዋ ኪጋሊ የምትባል ሲሆን ወደ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ ነዋሪዎች ይገኙበታል፡፡ አብዛኛው ሕዝብ የሚናገረው ቋንቋዎች መካከል ኪንያሩዋንዳ (የሩዋንዳ ኦፊሴላዊ ቋንቋ)፣ እንግሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ፣ ስዋሂሊ በብዛት ይነገርባታል፡፡

በ1890ዎቹ ጀርመን ሩዋንዳን በቅኝ ግዛት ስር አደረገቻት፡፡ እ.ኤ.አ. በ1916 ፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ፣ ጀርመን በእሷ ቅኝ ግዛት ስር የነበረችውን ሩዋንዳን ቤልጂየም በቅኝ እንድትገዛት ፈቀደችላት። በመቀጠልም ቤልጂየም ለአገዛዝ እንዲመቻት እያንዳንዱን ሰው ሁቱ (84%)፣ ቱትሲ(15%)፣ ትዋ(1%) በማለት በመከፋፈል ለሁሉም ዜጎች የብሔር መታወቂያ ካርዶችን አዘጋጅታ ለሕዝቡ ሰጥታለች።

በመቀጠልም ቤልጂየሞች ቱትሲዎችን ሁሉንም የመንግሥት የኃላፊነት ቦታዎች እንዲይዙ እና በሁቱዎች ላይ የበላይ ሆነው እንዲገዙ ወሰኑ፤ ይህም በሁለቱ ቡድኖች (ብሔረሰቦች) መካከል ከፍተኛ ውጥረት ፈጠረ። ቱትሲዎች ከሁቱዎች ተለይተው የተመረጡበት ምክንያት ተብሎ የሚታሰበት ቤልጂይማውያኑ ቱትሲዎቹን በረዥሙ እና ከታላቁ የሰውነት ቅርጻቸው የበለጠ "አውሮፓውያን" እንደሚመስሉ ያምኑ ስለነበረ ነው።

ይህ ዘዴ በአውሮፓ ሀገራት በያዙት ሀገራት ላይ ልዩነት በመፍጠር ሕዝቡን በመከፋፈል ለረዥም ጊዜ ለመግዛትና ሀገሪቱን በራሳቸው ሰው ከመምራት ይልቅ፣ በእነዚህ ምስለኔ የሀገሪቱ ዜጎች ማስተዳደሩ መልካም መሆኑን ስለተረዱና አዋጭ መሆኑን ስለተገነዘቡ ነው፡፡ በዚህም የቱትሲ ዘውዳዊ ሥርዓተ መንግሥት በማቋቋም በሁቱዎች ላይ የበላይ ሆነው እንዲያስተዳድሩ አድርጓዋል፡፡

ከጊዜ በኋላ ግን ቱትሲዎች ከቤልጅየም ነፃ ለመውጣት እንቅስቃሴ በመጀመራቸው ቤልጅየሞች በዚህ በመናደድ ሁቱዎችን በቱትሲዎች ላይ እንዲነሱባቸው የጥላቻ ዘመቻ ጀምሩ፡፡ ቱትሲዎች እስከ ኅዳር 1959 የሁቱ አመጽ እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ መንግሥትን መምራት ቀጠሉ። ሁቱዎች በፍጥነት ቱትሲዎችን እና የቤልጂየምን አገዛዝ በመገርሰስ በሺዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎችን ገድለው፤ የቀሩትን ደግሞ ወደ ጎረቤት ሀገሮች እንዲሰደዱ አደረጓቸው።

እ.ኤ.አ. ሐምሌ 1 ቀን 1962 ቤልጂየም ለሩዋንዳ በይፋ ነፃነቷን ሰጠች፤ ይህም አመጹ እንዲቆም አድርጓል። በዚያን ጊዜ ሁቱዎች የመንግሥት ሥልጣን ተቆጣጥረው ነበሩ፡፡ እ.ኤ.አ. በ1959 ከነፃነት 3 ዓመታት በፊት ቀደም ብሎ፣ አብላጫው ብሔረሰብ ሁቱ ገዢውን የቱትሲ ንጉሥ አስወገዱ። በሚቀጥሉት በርካታ ዓመታት በሺዎች የሚቆጠሩ ቱትሲዎች ተገድለዋል። በነበረው የእርስ በእርስ ግጭት ከ150,000 ሺ. እስከ 300,000 ሺ. የሚጠጉ ቱትሲዎች ወደ ጎረቤት ሀገራት ተሰደዋል።

እ.ኤ.አ. ጥቅምት 26 ቀን 1962 የሁቱ ተወላጅ ግሬጎየር ካይባንዳ የሩዋንዳ ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ። ሁቱዎች በሩዋንዳ ላይ ሥልጣን ከመያዛቸው ቱትሲዎችን ማፈናቀላቸውንና መበቀላቸውን ቀጠሉ። እንደ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በ1960ዎቹ አጋማሽ ከመጀመሪያዎቹ ቱትሲዎች ግማሹ ከሩዋንዳ ውጭ ይኖሩ እንደነበር ይገመታል። ከዚህ እንደምንረዳው ከከፍተኛ እልቂት ከተፈጸመበት ጊዜ አስቀድሞ ብዛት ያለው ግድያዎችና ማፈናቀሎች እንደነበረ መረዳት ግድ ይለዋል፡፡

የእነዚህ ግዞተኞች ልጆች የሩዋንዳ አርበኞች ግንባር (RPF) የተባለውን አማፂ ቡድን አቋቁመው በ1990 የእርስ በርስ ጦርነት ጀመሩ። ጦርነቱ ከበርካታ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ውጣ ውረዶች ጋር፣ በኤፕሪል 1994 ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ቱትሲዎች እና ለዘብተኛ ሁቱዎችን የዘር ማጥፋት ዘመቻውን ያባባሰው። ከእነዚህ ሁሉ ታሪክ በፊት ግን በሩዋንዳ ሦስቱም ማኅበረሰቦች በመጋባት፣ በመዋለድና በጋራ በመኖር ባሕላቸውን ጠብቀው ይኖሩ ነበር፡፡ ሀገር ሁሉም ብሔረሰቦች አብረው በጋራ ጠላቶቻቸው በጋራ በመመከትና በደህናው ጊዜ እርስ በእርስ በመጋባት፣ ግጭቶች ሲኖሩ በባሕላዊ ግጭት አፈታት ችግራቸውን በመፍታት በትብብርና ተደጋግፈው ይኖሩ ነበር፡፡

ይህ ሁኔታው ቢለያይም በሌሎች ሀገሮችም ያለ የሚኖር የማኅበረሰብ አኗኗር ዘይቤና ትስስር ነው፡፡ ሰዎች በቡድን ሲኖሩ የተወሰኑት መሪዎች ሌሎቹ ደግሞ ተመሪዎች ይሆናሉ፡፡ ነገር ግን ማኅበረሰቡ እነዚህ መሪዎች ከየትኛውም የማኅበረሰብ ክፍል ቢመጡ ማኅበረሰቡ ዋና ሀሳቡ በአግባቡ እየመሩ ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ እንጂ ሌላ ሀሳብ የላቸውም፡፡ ከዚህ ውጭ ያለው ሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ በጣም ጠንካራ ሲሆን በተለይም በሁቱና ቱትሲዎች መካከል ያለው ግንኙነት በጣም ጠንካራ ነው፡፡ አብሮ መጨፈር፣ መብላትና መጠጣት፣ የባሕል ለባሕል ልውውጥ ማድረግ ነበር፣ ክፋትና መጥፎ አስተሳሰብ ሳይዘራ በፊት በፍቅርና በመተጋገዝ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡

ነገር ግን በሁለቱ ብሔረሰቦች መካከል በደንብ እንዲከፋፈሉ አንዱን ብሔረሰብ በመጥቀም ሌላውን በማግለል ቅራኔ እንዲሰፋ ያደርጋሉ፡፡ አንድን ብሔረሰብ አባላት ወደ ሥልጣን በማምጣት ሌላው ብሔረሰብ የተገፋ እንዲመስለው በማድረግ ጥላቻንና በቀልን እንዲቆጥሩ ጊዜና ሁኔታ እስኪፈጠር እንዲጠብቁ ያደርጋል፡፡ ይህ ሁኔታ በሩዋንዳ የታየ ሲሆን በተለይም ቤልጅየሞች ቱትሲዎችን ወደ ሥልጣኑና ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ሁቱዎች የተገፋ እንዲመስላቸው አድርገዋል፡፡

በሩዋንዳ ባየሁት ሁኔታ በቱትሲዎችና ሁቱዎች መካከል ይህ ነው የሚባል ሰፋ ልዩነት ያላቸው ሕዝቦች አይደሉም፡፡ ለምሳሌ ለዚህ ማሳያ የሚሆነው የሚጠቀሙት መግባቢያ ቋንቋ አንድ አይነት ነው፡፡ እንግዲህ አስቡት እንደ ኢትዮጵያ ባለሀገር የተለያዩ ቋንቋዎችና ባህሎች ባለበት ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡

በሩዋንዳ ፕሬዚዳንት ጁቬናል ሀይኮሚን በ1973 በመፈንቅለ መንግሥት ወደሥልጣን ሲመጣ አዲስ አዋጅ አወጣ፤ ይኸውም ሀገሪቱ ላይ ያለው የሥልጣን ቦታዎች ሀገሪቷ ላይ ያለው የብሔር ስብጥር ሚዛን የጠበቀ መሆን እንዳለበትና ተማሪዎችም ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲመደቡ ከፍተኛው ቦታ አብዛኛውን ቁጥር ላላቸው ሁቱዎች ሲሆን ቀሪው ትንሽ ቁጥር ደግሞ ቱትሲዎችና ትዋ ብሔረሰቦች እንዲሆን አደረገ፡፡

ለዚህ ምክንያቱ ሁቱዎች በቁጥር ትልቁ ስለሆኑ ከፍተኛው የመንግሥት ሥልጣን ቦታዎችን መያዝ ያለባቸው እነሱ እንደሆኑ የሚደነግግ አዋጅ ነበር፡፡ በሩዋንዳ ኢ-መደበኛ አደረጃጀት ቡድን ወይም ኢንተርሀሙይ የተባለ ቡድን በማቋቋም በቱትሲ ማኅበረሰብ ላይ ጥቃት እንዲፈጽሙ አደራጅተዋቸው እና በመሣሪያ ድጋፍ አድርገው ለብዙኃን ዜጎች ሞት ምክንያት ዋና ተዋናይ ሆነዋል፡፡

የሩዋንዳው አይነት ድርጊት ሚችን ብቻ ሳይሆን ገዳይንም የጎዳው ስለሆነ ከዚህ ትምህርት ወስደን በቂ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ ዓለም አቀፍ ማኅበረሰቡም ዘርን ያነጣጠሩ ግድያዎችን ሲያይ ዝም ከማለት ብዙ አደጋ ሳይደርስ አፋጣኝ እርምጃዎችንና ጫናዎችን በማድረግ፣ በተለያዩ ጊዜ እንደተፈጠሩት የዘር ፍጅቶች "Never Again" ወይም "በጭራሽ አይደገምም" እያለ ከአይሁዶች እስከ ሩዋንዳ ተመሳሳይ መፈክር ማሰማት ብቻ ሳይሆን በተግባር እንዳይፈጸም ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

ለዚህም በዓለም አቀፍ ያለው የዲፕሎማሲና የዓለም አቀፍ ግንኙነት መሣሪያዎችንና መርሆችን ማዕከል ያደረጉ እርምጃዎችን በእንደዚህ አይነት መንግሥታት ላይ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፤ ነገሮች ከመዘግየታቸውና እልቂት ከመፈጠሩ በፊት አስፈላጊውን እርምጃ በመውሰድ እንደዚህ ያሉ እልቂቶችን እንዳይፈጸሙ ማድረግ አለበት፡፡

**ሻሎም ! አሜን።**

# ወቅታዊ

# አሳሳቢ የሆነው የድሬዳዋ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት

ስምስም መንግሥቱ

የምሥራቅዋ ንግሥት እየተባለች የምትወደሰው ድሬዳዋ ከኢትዮጵያ ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች አንዷ መሆኗ ይታወቃል። ከባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት መጀመር ታሪክ ጋርም ተያይዞ ስሟ ይነሳል። እስከ ጅቡቲ የተዘረጋው የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ሲጀምር በከተማዋ ውስጥ የተቋቋመው የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት የከተማዋን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ሁኔታ ያነቃቃ እንደነበር አይዘነጋም። ይህም የንግድ እንቅስቃሴ ማዕከል እንድትሆን አስችሏታል።

በንግድ እንቅስቃሴ መታወቋ ደግሞ ከተለያየ የኢትዮጵያ ክፍል ወደ ከተማዋ የሚሄደው ሰው እንዲጨምር አድርጓል። ከድሬዋ እየሸመቱ ወደአካባቢያቸው ወስደው የሚሸጡ ሰዎች ጥቂት አልነበሩም።

ድሬደዋ አስተዳደር እንዲህ በተለያየ ታሪክ እንደምትታወቀው ሁሉ፤ በከተማዋ በከፍተኛ ሁኔታ የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር እንዳለባትም አብዝቶ ይነሳል። በቧንቧ መስመር ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳትም ከፍተኛ ወጪ በማስከተል ተጨማሪ ተግዳሮት ሆኗል። አካባቢው ላይ እየተስተዋለ ያለውን ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትም ሆነ፣ ከፍተኛ ወጪ እያስከተለ ያለው በቧንቧ መስመር ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመፍታት ምን እየተሰራ ነው? ስንል ጥያቄ አቅርበናል።

በዚሁ ዙሪያ በድሬደዋ አስተዳደር የውሃ አቅርቦትና ስርጭት ዳይሬክተር ኢንጂነር ረመዳን ሙሳ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተውናል፤ መልካም ንባብ።

**አዲስዘመን፤ የድሬደዋ አስተዳደር የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር እንዴት ይገለጻል? አሁን ላይ ያለው የውሃ ሽፋን ምን ያህል ነው?**

**ኢንጂነር ረመዳን፤** የውሃ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ ነው። የተፋሰስ ልማት ሥራ በተጠናከረ ሁኔታ ካልተሰራ ችግሩ እየተባባሰ መሄዱ አይቀርም። ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ሁለት መቶና ሶስት መቶ ሜትር ተቆፍሮ ውሃ ይገኝ ነበር። አሁን ላይ እስከ አምስት መቶ ሜትር ድረስ ጥልቀት መቆፈር ይጠበቃል። ይሄ በጣም አሳሳቢ ነው።

በአሁኑ ጊዜ ለሐረር ውሃ እየቀረበ ያለው ከድሬደዋ አስተዳደር ነው። ሐረርን የገጠማት ችግር ድሬደዋ አስተዳደርን እንዳይገጥማት ምን ማድረግ አለብን የሚለው መታሰብ አለበት። እየታየ ያለውን ችግር ታሳቢ ያደረገ የጥናት ሥራዎች ተጀምረዋል። አሁን ላይ ሥራዎች እየተሰሩ ያሉት ያሉንን የውሃ መገኛዎችን በአግባቡ በመያዝ ተደራሽነቱንም ፍትሀዊ ለማድረግ ነው ጥረት እየተደረገ ያለው።

ለውሃ እጥረቱ ሌላው ተግዳሮት እየሆነ ያለው፤ ካልሼም ባይካርቦኔት ወይንም ጨው ነው። ይሄ ጨው የውሃ መተላለፊያዎችን ቧንቧ በመዝጋት ጉዳት እያስከተለ ነው። በዚህ የተነሳ ውሃ ማዳረስ የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል። መስመሮቹ በጨው ስለሚበሉ አንዳንዴ መስመሩ ተሰብሮ በመፍሰስ ብክነት ያጋጥማል። እንዲህ ያለው ችግር ሲያጋጥም ሐረር ላይም እጥረቱ በተመሳሳይ ይከሰታል። ምንጫችን አንድ በመሆኑ ችግሩ ይሰፋል። የጨው ክምችቱ እየጨመረ ሲሄድ በስርጭቱ ላይ የአንድ ቀን ልዩነት እንዲፈጠር ያደርጋል።

ችግሩ በቀላሉ የሚነገር አይደለም። ከውሃ እጥረቱ በላይ በጨው ምክንያት የሚስተጓጎለው እየበለጠ ችግር እየሆነ ነው። በጨው ምክንያት አስተዳደሩ ለከፍተኛ ወጭ እየተዳረገ ነው። በየዓመቱ ቢያንስ ወደ 20ኪሎ ሜትር የውሃ ማስተላለፊያ መሥመር ይቀየራል።

በአጠቃላይ ተቋሙ እየሰጠ ባለው ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የተጠቃሚውን ፍላጎት አሟልቷል ብሎ አያምንም። በተቀመጠው ዲዛይን ሙሉ ለሙሉ እያቀረብን አይደለም። ክፍተት አለ። ከንግድ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ወደ ከተማዋ የሚመጣው ሰው ቁጥር ከፍተኛ ነው። የሰው ፍሰቱም ያለውን ውሃ ስለሚሻማ ለእጥረቱ የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው። አቅርቦትና ፍላጎትን ለማጣጣም ባይቻልም አሁን ላይ እንደመፍትሄ ተወስዶ እየተሰራ ያለው በፈረቃ አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ ነው።




አሁን ባለው መረጃ የድርጅቱ ደንበኞች ወደ 49ሺ ይሆናሉ። አገልግሎቱም ተደራሽ እየሆነ ያለው ለዘጠኝ የከተማ ቀበሌና በመካከል ላይ ለሚያልፉ የገጠር ቀበሌዎች ነው። እነዚህ ከተቋሙ ጋር ውል ገብተው ወርሃዊ ክፍያ እየከፈሉ የሚጠቀሙና ተቋሙም በደንበኝነት የያዛቸው እንጂ አገልግሎቱን ከሚያገኙት በመግዛትና በተለያየ መንገድ የሚጠቀመው ተገልጋይ ቁጥር ከፍተኛ ነው። በቤተሰብ በአማካይ በሚወሰድ ስሌት እንኳን እስከ 300ሺ ሰው አገልግሎት እንደሚፈልግ ይገመታል።

ከባለፈው ዓመት ጀምሮ ያለውን መረጃ ብንወስድ እንኳን ከነፃ ንግድ ቀጣና እና ከተለያዩ ነገሮች ጋር ተያይዞ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰው ወደ ድሬደዋ ፈልሷል። እነዚህ ሁሉ የተጠቃሚውን ቁጥር የሚጨምሩ በመሆናቸው ትክክለኛውን መረጃ ለመስጠት ያስቸግራል።

በከተማዋ የሚገኙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችም የራሳቸውን ጉድጓድ በመቆፈር የሚጠቀሙ ቢሆኑም፤ ከቀጥታ መስመር አገልግሎት ይፈልጋሉ። የከተማ አስተዳደሩ ኢንዱስትሪ መንደር ለሚባሉት ግን ተደራሽ እየሆነ ያለው በሥራ ላይ ባለው ፕሮጀክት ነው።

የድሬደዋ አስተዳደርን ከሌሎች አካባቢዎች ለየት የሚያደርገው፤ የከተማና የገጠር ወረዳዎች አሏት። ይህ ተቋም በአብዛኛው አገልግሎት እየሰጠ ያለው ከተማ ውስጥ ቢሆንም ውሃ በሚገኝባቸው የገጠር አካባቢዎችም ተደራሽ ያደርጋል። አገልግሎቱ የሚሰጥባቸውን አካባቢዎች በጥናት በመለየት ክለሳ ለማድረግ ሥራ ተጀምሯል።

**አዲስዘመን፤ -ታዲያ ችሩን ለማስወገድ ምን ታስባል ?**

**ኢንጂነር ረመዳን፤-** በተለይ የጨው ክምችቱ እያስከተለ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር እየሰራን ነው። በአካባቢያችን ያሉት ዩኒቨርሲቲዎች ድሬደዋና ሐረማያ ናቸው። እነርሱም በግላቸው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደተጠበቀ ሆኖ በቅንጅት ሆነን የምንሰራቸው ሥራዎችም አሉ።

አንዳንዴ ግን ችግሮችን የምንፈታበት መንገድ ከአቅም በላይ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ አለ። የጥናት ሥራ ከሆነ በዚህ በኩል ችግር የለም። በተለያየ ጊዜ ጥናት ተደርጓል። ለምሳሌ ጨውን ለማከም ጥናት ሊካሄድ

**ከውሃ እጥረቱ በላይ በጨው ምክንያት የሚስተጓጎለው እየበለጠ ችግር እየሆነ ነው:: በጨው ምክንያት አስተዳደሩ ለከፍተኛ ወጭ እየተዳረገ ነው:: በየዓመቱ ቢያንስ ወደ 20ኪሎ ሜትር የውሃ ማስተላለፊያ መሥመር ይቀየራል**

ይችላል። ወደ ትግበራ ለመቀየር ደግሞ ከፍተኛ መጠን ያለው በጀት ይፈልጋል። ይሄን ለማሟላት ደግሞ አቅም ይጠይቃል።

ችግሮች ከታወቁ መፍትሄ ስለማይጠፋ ችግሩ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኝ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋርም ሆነ ከአንዳንድ ባለድርሻ አካላት ጋር ሥራዎችን መሥራት አልተቋረጠም። በአማካሪ ድርጅቶች የጥናት ሥራም ጎን ለጎን ማካሄድ ያስፈለገውም መፍትሄ ለማምጣት ነው። ድሬደዋ ለሚቀጥሉት ዓመታት ውሃ ከየት ነው የምታገኘው? ከተገኘስ በኋላ ምንድነው የምናደርገው ? የሚለውን ነው ጥናቱ የሚዳስሰው።

**አዲስ ዘመን፤ -አሁን ላይ በቀን ምን ያህል ሜትሪክ ኩዩብ ንጹ የመጠጥ ውሃ ለተጠቃሚው እየቀረበ ነው?**

**ኢንጂነር ረመዳን፤-** በርግጥ አንዳንዴ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት መቆራረጥ በራሱ የሚያሳድረው ተጽእኖም አለ። አቅርቦቱን በመመዝገብ ነው የጀመርነው። በሶስት ሳይቶች (አቅጣጫዎች) ላይ ለመከታተል በተደረገው ጥረት በቀን ከሰባት ሺ እስከ ስምንት ሺ እንዲሁም ከአምስት ሺ እስከ ስድስት ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ የማምረት አቅም ያላቸው ዞኖች መኖራቸው ተረጋግጧል።

እነዚህ በክትትል የተረጋገጡ ናቸው። ሌሎች ታሳቢ ያልተደረጉ ጉድጓዶች ግን አሉ። የእሳት አደጋን ለመከላከል የሚውል የውሃ መጠንን ጭምር ማወቅ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ የተሟላ መረጃ ከተሰበሰበ በኋላ በቀን ምን ያህል ሜትሪክ ውሃ መንጭቶ ጥቅም ላይ እንደሚውል ማወቅ ይቻላል። በወር ውስጥ ግን እስከ አንድ ሚሊየን ሜትር ኪዩቢክ ውሃ ይመረታል። ታሳቢ ያልተደረጉት ሲጨመሩ ግን ቁጥሩ ከፍ ይላል።

**አዲስ ዘመን፤ ከመሠረተ ልማት አቅራቢ ተቋማት ጋር በመናበብ ያለመሥራት እንደ ችግር ይነሳል፤ ይህን ችግር ለማስወገድ ምን እየሰራችሁ ነው ?**

**ኢንጂነር ረመዳን፤** በቅንጅት እየተናበቡ መሥራት ለመሠረተ ልማት ሥራ ወሳኝ ነው። በቅንጅት ሲሰራ የሀብት ብክነትን ያስቀራል። ይህን ታሳቢ በማድረግ በአዳዲስ ፕሮጀክት ሥራዎች ላይ ለመተግበር ጥረት ተደርጓል። በነባር ፕሮጀክቶች ላይ ግን አሁንም መቅረፍ አልተቻለም። የውሃ መስመር በተዘረጋበት ላይ የአስፓልት ሥራ ይሰራል። የኮብል ስቶን ንጣፍ የሌላቸው አካባቢዎች ላይ አዲስ ሥራ ይሰራል። እነዚህ አካባቢዎች የውሃ መሥመር የተዘረጋባቸው ስለሆኑ የውሃ መስመር ፍንዳታ ሲያጋጥም እንደ ገና መጠገን ወይም አዲስ መስራት ያስፈልጋል።

ይሄ ከፍተኛ የሆነ የሀብት ብክነት ያስከትላል። አሁን ላይ ግን መሠረተ ልማቱን የሚያከናውኑ ተቋማት ለባለ ድርሻ አካላት ቀድሞ በማሳወቅ ችግሩን ለመቀነስ ጥረት እየተደረገ ነው።

ቀድሞ እንዲያውቁት ሳይደረግ ወደ ሥራ አይገባም። ሁሉም በዘፈቀደ የየራሱን ሥራ ለመሥራት አይነሳም። ይሄ ትልቅ መሻሻል ነው። እንደ አስተዳደርም መሠረተ ልማትን የሚያቀናጅ እንዲሁም ሁሉም ዓመታዊ እቅዳቸውን በፎርማ የሚያሳውቁበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቷል። የተዘረጋውን የአሰራር ሥርዓት አጠናክሮ መቀጠል ከተቻለ ችግሮች ቀስ በቀስ እየተቀረፉና ትክክለኛውንም መሥመር እየያዙ ይሄዳሉ።

አሁን ላይ በውሃ መሠረተ ልማት በብዛት እየተቆፈረ ያለው ከካልሼም ባይካርቦኔት ወይንም ከጨው ጋር በተያያዘ ችግር ነው። ምክንያቱም ጥገና ካልተደረገ የውሃ ብከነት ይከሰታል። ተጠቃሚዎችም ተገቢውን አገልግሎት አያገኙም።


**አዲስ ዘመን፤ ማኅበረሰቡ ለመጠጥና ለተለያየ አገልግሎት ተመሳሳይ የሆነ ውሃ ከመጠቀም ቢቆጠብ ብክነትን መቀነስና በበቂ ሁኔታም ማግኘት እንደሚቻል የውሃ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ምክረሀሳብ ይሰጣሉ። እዚህ ላይ የተሰራ ሥራ ካለ እንዲሁም በአካባቢ ጥበቃ ሥራ ላይ የተከናወነ ተግባር ካለ ቢገልጹልን ?**

**ኢንጂነር ረመዳን፤** ከብክነት አንጻር ሁለት ነገሮችን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

# አሳሳቢ የሆነው...



ከገጽ 7 የዞረ

ማየት ይቻላል። አንዱ ሕዝቡ አውቆ የሚያባክነው ነው። ሌላው ከእውቀት ማነስ የሚፈጠረው ነው። ለመጠጥ ሊውል የሚችል ውሃ ለመኪና እጥበትና ለተለያዩ አገልግሎቶች ሲውል ይስተዋላል።እነዚህን ክፍተቶች በመልሶ መጠቀም መፍታት ይቻላል። መልሰን ጥቅም ላይ ልናውላቸው የሚችሉ ሀብቶችን በቸልታ እያለፍናቸው በመሆኑ ነው እንዲህ ያሉ ክፍተቶች የተፈጠሩት።

በተለያየ ምክንያት በሚያጋጥም ብልሽት አላግባብ ውሃ ሲፈስ አይቶ የማለፍ ሁኔታም ሌላው ችግር ነው። ይሄ ተቆርቋሪነት አለመኖርን ያሳያል። ለሚመለከተው አካል መረጃ ሰጥቶ ብክነትን መታደግ ሲቻል በምንቸገረኝና በቸልተኝነት ይታለፋል። ዞሮ ዞሮ ግን ጉዳቱ የተገልጋዩ ነው። የውሃ እጥረቱን የበለጠ እንደሚያባብሰው መገንዘብ ያስፈልጋል።

አንድ ሰው በቀን እስከ 80ሊትር ውሃ መጠቀም እንዳለበት የውሃ ፖሊሲ ይገልጻል። አሁን ባለው መወቅታዊ መረጃ ግን አንድ ሰው መጠቀም ካለበት የውሃ መጠን በላይ እየተጠቀመ ነው። ይሄም አኗኗሩ ያመጣው ለውጥና የከተማ ማደግ ነው። የመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም በመቀየሩ ቆሻሻውን ለማውረድ ውሃ ይለቀቃል። የሚለቀቀው የውሃ መጠን ደግሞ ከፍተኛ ነው።

ከደንበኞች ጋር በዓመት ሁለቴ የምንገናኝበትን ፎረም አዘጋጅተናል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ግንኙነቱ ወደ ሶስቴ ሊሆን ይችላል። ደንበኞች በአሰራር ላይ ሀሳብ አስተያየት እንዲሰጡ የሥራ አፈጻፀምና እቅድ ይቀርባል። በተጨማሪም ከእነርሱ የሚጠበቀውን ግዴታና ኃላፊነት የማስገንዘብና የተሟላ መረጃ እንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ ይሰራል።

የአካባቢ ጥበቃ ሥራን በተመለከተ፤ ምንም አያጠያይቅም የዛፍ ችግኞችን በመትከል የአካባቢ ሥነምህዳርን መጠበቅ ያስፈልጋል። መሥሪያቤታችን ከአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በጥምረት ሆኖ እየሰራ ይገኛል። በየዓመቱ በሚከናወነው የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሃግብር የዛፍ ችግኝ መትከያ ቦታዎች እየተመረጡ እንዲተከል ይደረጋል።

የአካባቢ ጥበቃ ሥራም እንደ አጠቃላይ የውሃ መሠረተ ልማትን ለማሻሻል ተብሎ እየተደረገ ካለው የጥናት ሥራ ጋር ተካትቶ ይከናወናል። በጥናቱ እንዲመለስ ማድረግ ያስፈለገው የአካባቢ ጥበቃ ሥራው በተለየ ቦታ ላይ ትኩረት እንዲያገኝ ነው። ምክንያቱም የውሃ መገኛ ምንጩ ከድሬደዋ ከተማ ውጭ ቁልቢ አካባቢ ወይንም ሌላ አካባቢ ሊሆን ስለሚችል ነው።

**አዲስዘመን፤ የውሃ ቆጣሪ ወይንም መሥመር ማግኘት አንዱ የመልካም አስተዳደር ችግር ሆኖ ይነሳል። ይህ ሁኔታ እናንተም አጋጥሟችሁ ከሆነ እንዴት እየፈታችሁት ነው?**

**ኢንጂነር ረመዳን፤** አዲስ ደንበኞች ጥያቄ ስላቀረቡ ብቻ አይስተናገዱም። ቀድመው የሚታዩ ነገሮች አሉ። አንዱ የተቋሙ የአቅም ሁኔታ ነው። ሌላው ደግሞ የቦታ ምቹነት ነው። ከኛ ሪዘርቫየር በላይ ወይንም ተደራሽ በማንሆንበት አካባቢ ጥያቄ ይቀርባል። ይሄን ጥያቄ ብናስተናግድና ደንበኛው ውሃ ማግኘት ባይችል መልሶ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ማንሳቱ አይቀርም። ስለዚህ የቦታ ምቹነት ወሳኝ ነው። ለሚያቀርቡት ጥያቄ መልስ ሳያገኙ የቀሩትም በአብዛኛው ምቹ ባልሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው።

ተቋሙ በሚችለው አቅም አዳዲስ ደንበኞችን እያስተናገደ ይገኛል። ይሁን እንጂ ከተቋሙ አቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲኖሩ ደንበኞች ረዘም ላለ ጊዜ ሊጠብቁ ይችላሉ። የውሃ ቆጣሪ በግዥ ከውጭ ስለሚመጣ የግዥ አፈፃፀሙ ረዝም ያለ ጊዜ ይወስዳል።

እኛ በየዓመቱ ሶስት ሺ ደንበኞችን ለመቀበል ነው ያቀድነው። ሆኖም ግን የውሃ ቆጣሪው የግዥ መዘግየት በእቅዳችን መሠረት እንዳንፈጽም እያደረገን ነው። በተቻለ መጠን ግን እንዲገዛ የታዘዘው ግዥው ተፈጽሞ እንደደረሰን የደንበኞችን ጥያቄ እንመልሳለን። በያዝነው በጀት ዓመት በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ 700 የሚሆኑ አዲስ ደንበኞችን ማስተናገድ ተችሏል። የተያዘው እቅድና አፈፃፀም የተመጣጠነ አይደለም።

ይህ ሊሆን የቻለው የውሃ ቆጣሪ አቅርቦት በበቂ ሁኔታ ባለመኖሩ ነው። ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የመጣው የደንበኞች ፍላጎትም ጫናው እንዲጨምር አድርጓል። የውሃ ቆጣሪ አቅርቦት ችግር ለመቅረፍ እንደመፍትሄ እየተወሰደ ያለው በሀገር ውስጥ ተመርቶ እንዲቀርብ በማድረግ ነው። መስሪያቤታችንም ይህንን በቦርድ አስወስኗል።

**አዲስዘመን፤- አዳዲስ የፕሮጀክት ግንባታዎች ካሉና ለፕሮጀክት ግንባታው የተያዘውን ወጪ፣ መጠኑንም ጨምረው ቢገልጹልን ?**

**ኢንጂነር ረመዳን፤-** ከዚህ ቀደም ከዓለም ባንክ በተገኘ ገንዘብ የተሰራው የውሃ ፕሮጀክት ለነዋሪውም ሆነ ለከተማ አስተዳደሩ ትልቅ እፎይታ የሰጠ መሆኑ ይታወሳል። ከዚህ ፕሮጀክት የተረፈ ወይንም ቀሪ ሥራ ደግሞ የከተማ አስተዳደሩ ቀጥሎበታል። በራስ አቅም መሰራት አለበት ብሎ በመነሳሳት ነው እየሰራ የሚገኘው።

ፕሮጀክቱ ወደ 18 ወራት የሚፈጅ ፕሮጀክት ሲሆን፤ በሚቀጥለው በጀት ዓመት እንደሚጠናቀቅ ይጠበቃል። በገንዘብም ወደ አንድ ነጥብ ስድሰት ቢሊየን ብር የሚፈጅ ፕሮጀክት ነው። የዚህ ፕሮጀክት ሥራ ኢንደስትሪ ፓርኮችንም ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፤ አጠቃላይ የከተማ አስተዳደሩን የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር ይፈታል የሚል እምነት የተጣለበት ነው።

አፈጻፀሙም አበረታች ነው። ከዚህ በኋላ ያለው ሥራ የመሥመር ዝርጋታ በመሆኑ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ይጠናቀቃል የሚል እምነት ነው ያለው። የፕሮጀክት ሥራው ከከተማ አስተዳደሩ ወጣ ባለ የገጠር ቀበሌ ውስጥ ነው እየተከናወነ ያለው።

**አዲስ ዘመን፤ ከቆሻሻ ፍሳሽ አወጋገድ ጋር ተያይዞ ስላለው አገልግሎት፤አክለውም በሥራ ሂደት በጥንካሬና በክፍተት የሚጠቀሱትን ያንሱልንና በዚሁ ብናጠቃልል**

**ኢንጂነር ረመዳን፤** የውሃ፣ የቆሻሻ ፍሳሽ አገልግሎቶች ሁለቱም ትላልቅ ተቋማት ናቸው። ንጹህ የመጠጥ ውሃ ደንበኛው ጥያቄ እስኪያቀርብልን ድረስ ጠብቀን የምንሰራው ስራ አይደለም። ሁልጊዜ የኅብረተሰቡን ውሃ ፍላጎት ለማሟላት ጥረት ማድረግን ይጠይቃል። የሚያስተኛ ስራ አይደለም።

የቆሻሻ አወጋገዱም የራሱ የሆኑ ችግሮች ያሉበት ነው።ከቆሻሻ ፍሳሽ ጋር ተያይዞ የሚያጋጥመን ችግር፤ አንዳንድ መፀዳጃ ቤቶች ሴፍቲ ታንክ ወይንም የቆሻሻ ማስወገጃ የሌላቸው አሉ። የአንዳንዶቹ ደግሞ የመድረቅ ሁኔታ ያጋጥማቸዋል። ይሄ ቆሻሻ ፍሳሹን ለማስወገድ ፈተና ነው የሚሆነው። የቆሻሻ መምጠጫ ወይንም ፓምፕ ላይ ጉዳት ያስከትላል።

በሌላም በኩል በአሰራር ላይም ክፍተቶች አሉ። የመምጠጫዎች የመሳብ አቅም በአግባቡ ሳይፈተሽ ለሥራ ሲወጣ አገልግሎቱ የተሟላ የማይሆንበት ሁኔታ አለ። ይሄም በተቋሙ አገልግሎት ላይ ችግር እያስከተለ በመሆኑ መታየት እንዳለበት ግንዛቤ ተይዟል። አንዳንዴ ደግሞ ጥያቄዎች ሲበዙ አገልግሎቱ የተቀላጠፈ የማይሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል።

በዚህ በኩል ወደፊት ይስተካከላል ብለን የምንጠብቀው በዓለም ባንክ የተያዘው የፕሮጀክት እቅድ ነው። የዓለም ባንክ ከሳንቴሽን ጋር ተያይዞ የሚሰራው ፕሮጀክት ልክ እንደ ንጹህ መጠጥ ውሃ ፍሳሽ ቆሻሻም በመስመር እንዲወገድ ማስቻል ነው። የፕሮጀከት ሥራው ጥናት ተጠናቅቆ የጨረታ ሂደት ላይ ነው የሚገኘው። ሥራው በተያዘለት እቅድ ተጠናቅቆ ተግባራዊ ሲሆን፤ ንጹህ መጠጥ ውሃን ለማሰራጨት ግዴታ እንደሆነው ሁሉ የፍሳሽ ቆሻሻንም ለማስወገድ የሚሰጠው አገልግሎት ግዴታ ይሆናል ማለት ነው።

አንድ ቦታ አገልግሎቱ ቢቋረጥ ለምን ተቋረጠ ብሎ መፍትሄ መስጠት አለበት። የንጹህ መጠጥ ውሃ አሰራር ሂደትን ተከትሎ ይከናወናል። ምክንያቱም አንድ ሰው ውሃ ሲጠቀም 60 እና 70 በመቶ ቆሻሻ ፍሳሽ ሆኖ ነው የሚወገደው። ስለዚህ ነው ትኩረት የተሰጠው። የግንባታ ሥራው በቅርቡ ይጀመራል።

በጥንካሬና በክፍተት እንደተቋም የማነሳው፤ በተለይ በጥንካሬ በኩል ተቋማችን እረፍት የሌለው ነው ማለት ይቻላል። ሰራተኞቻችን የእረፍት ቀን ሳይሉ ከሳምንት እስከ ሳምንት 24 ሰአት ሥራ ላይ ናቸው። ምክንያቱም ያለ ውሃ ምንም ነገር መሥራት ስለማይቻል።

በክፍተትና በተግዳሮት የማነሳው፤ ካልሺም ባይካርቦኔት ወጥንም የጨዋማነት ሁኔታ ትልቁ የተቋሙ ፈተና ነው ማለት ይቻላል። ተቋሙ ገቢ በማያገኝበት ነገር ላይ ነው እየሰራ ያለው። ጨው በሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ ወጭ እያወጣ ነው። በኅብረተሰቡ ዘንድ ደግሞ ውሃን ሀብት አድርጎ ያለማየትና በብልሽትና በተለያየ ምክንያት ውሃ ሲፈስ በዝምታ ማለፉ እንደ ክፍተት የማነሳው ነው።

የድሬደዋ አስተዳደር የንጹ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለይቶ የውሃ አቅርቦት ሽፋንን ለማሳደግ እየተደረጉ ያሉ ጥረቶችን በማገዝ ቁርጠኛ መሆኑን በተለያዩ ድጋፎቹ ማረጋገጥ ይቻላል። ውሃ ህይወት በመሆኑ የከተማ አስተዳደሩ በተለያየ መንገድ እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ ይቀጥላል የሚል እምነት አለኝ።

በሌላ በኩል በግልም ሆነ በድርጅት ደረጃ በውሃ ዘርፍ ላይ እውቀቱ ላላቸውና ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙ አካላት የድሬዳዋን ውሃ አቅርቦት ችግር ለማቃለል የቻሉትን ሁሉ እገዛ እንዲያደርጉ እገዛ ማድረግ እፈልጋለሁ። እንዲህ ያለው ሀብት ያላቸው በአቅም ግንባታና በተለያየ መልኩ ተቋማዊ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል እገዛ ቢያደርጉልን ለውጥ ለማምጣት እያደረግን ያለውን እንቅስቃሴ የበለጠ ያጠናክርልናል ብዬ አምናለሁ።

**አዲስዘመን፤ ስለነበረን ቆይታ እጅግ በጣም እናመሰግናለን።**

**ኢንጂነር ረመዳን፤** እኔም አመሰግናለሁ።

**እኛ በየዓመቱ ሶስት ሺ ደንበኞችን ለመቀበል ነው ያቀድነው፡፡ ሆኖም ግን የውሃ ቆጣሪው የግዥ መዘግየት በእቅዳችን መሠረት እንዳንፈጽም እያደረገን ነው**

# ኢንቨስትመንት

# የወተት ሃብት ኢንቨስትመንቱ አርዓያነት ያለው ተሞክሮ

**ማሕሌት አብዱል**

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን አብዛኛው ዜጋዋ በግብርና ሥራ ላይ የሚተዳደር እና ኢኮኖሚዋም በግብርና ላይ የተመሠረተ ቢሆንም፣ የአመራረት ሂደቱ ኋላቀር፣ በአነስተኛ መሬት ላይ የሚካሄድ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ዘርፉ ለሃገር እድገት የሚገባውን ያህል ሳያደርግ መቆየቱ ይጠቀሳል፡፡ ለግብርና ልማት ምቹ የአየር ሁኔታና ሥነ-ምህዳር ያላት ሃገር ብትሆንም የዘርፉ አመራረት ከአነስተኛ አቅም ወጥቶ በግዙፍ ኢንቨስትመንት ሳይደገፍ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

እርግጥ በተለይም የለውጡ መንግሥት መምጣቱን ተከትሎ የእያንዳንዱን አርሶ አደርና አርብቶ አደር ምርትና ምርታማነት ሊያሳድጉ የሚችሉ እንዲሁም የግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፉን አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች እንዲሁም የአሠራር ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ ይህም በተጨባጭም የአርሶ አደሩን ሕይወት የሚለውጡ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እያስገኘ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር ጥቂት የማይባሉ ባለሃብቶችንም እየሳበ ይገኛል፡፡ ለኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ተቋቁመው ሃገራቸውንና ሕዝባቸውን በኢኮኖሚ ለማሳደግ ቆርጠው የተነሱ ባለሃብቶችም በዘርፉ እየተፈጠሩ ይገኛሉ፡፡

ከእነዚህ ባለሃብቶች መካከል አቶ አድማሱ አርፍጮ አንዱ ናቸው፡፡ ግለሰቡ ትውልዳቸውም ሆነ እድገታቸው በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከንባታ ዞን ዳምቦያ ወረዳ በምትገኘውና ሄጎ በምትባለው የገጠር ቀበሌ ነው፡፡ እድገታቸው እንደ አብዛኛው የአርሶ አደር ልጅ አነስተኛ ገቢ ካለው ቤተሰብ ውስጥ ሲሆን፣ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በአካባቢያቸው ለወጣቶች የሚሆን የሥራ ዕድልም ሆነ የልማት እንቅስቃሴ ባለመኖሩ ራሳቸውንም ሆነ ቤተሰባቸውን ከችግር ለማውጣት ሲሉ ለስደት መዳረጋቸውን አቶ አድማሱ ይናገራሉ፡፡

‹‹ማንም ሰው ቢሆን ተመችቶት ከሃገሩ አይወጣም፤ እንደአጋጣሚ ሆኖ ወቅቱ ጥሩ ስለነበር ተሳካልኝ እንጂ እስከሞት የሚደርስ አደጋ ሰለባ ልሆን የምችልበት አጋጣሚ ሰፊ ነበር›› ሲሉ የስደት ሕይወታቸውን አስታውሰው፤ በተለይም ደቡብ አፍሪካ ለመድረስ ሲሉ ያለፉባቸውን ፈታኝ ሁኔታዎች ከባድ እንደነበሩ ይጠቅሳሉ፡፡ ለ20 ዓመታት በቆዩባት ደቡብ አፍሪካ እንደማንኛውም ስደተኛ ከዝቅተኛ ሥራ ጀምሮ ሥራ ሳይመርጡ በመሥራታቸው በጥቂት ዓመታት ጥሪት ቋጥረው የግላቸውን የንግድ ሥራ መጀመራቸውን ያመለክታሉ፡፡

ሥራ ወዳድና አዲስ ነገር ለመቀበል ሁሌም ዝግጁ መሆናቸውን የሚናገሩት አቶ አድማሱ፣ በሂደት ባፈሩት ሀብት በዚያው በስደት ሃገር በሆቴል ኢንቨስትመንት ዘርፍና በንግድ ሥራ ከፍተኛ ደረጃ ከደረሱ ኢትዮጵያውያን አንዱ መሆን ችለዋል፡፡ ሆኖም የሚሠሩት ለባዕድ ሃገር መሆኑና ይህች ሃገር ደግሞ በኢኮኖሚ ደረጃ የላቀች ከመሆኑ ጋር ተያይዞ  በአንፃሩ ደግሞ ሳይማር ያስተማራቸው ሕዝብ በድህነት እየማቀቀ መሆኑን ሲያስቡ ቁጭት ያድርባቸው እንደነበር ይጠቅሳሉ፡፡

‹‹ሃገርና ሕዝብ የእኔን ድጋፍ በጠየቀ ቁጥር ያቅሜን ከማድረግ ወደኋላ ቀርቼ አላውቅም፤ ዓባይ ግድብ እንኳን ሲጀመር በደቡብ አፍሪካ የሚኖረውን ኢትዮጵያውያንን አስተባብሬ 25 ሚሊዮን ብር አሰባስቤ ድጋፍ እንዲደረግ ሠርቻለሁ›› ይላሉ፡፡ ይሁንና ይህ ብቻውን እርካታ አልሰጣቸውምና ወደ ሀገራቸው በመምጣት ከተወለዱበት ቀዬ ዘልቀው ዛሬም በድህነትና በመሠረተ ልማት እጦት እየተሰቃየ ያለውን ማኅበረሰብ አማከሩ፡፡ የማኅበረሰቡ የመጀመሪያ ጥያቄ በአካባቢያቸው በአያያዝ ጉድለት የተጎዳውን የእርሻ መሬት የሚመልስ ሥራ እንዲሠሩ ነበር፡፡ ቀድሞውንም ችግኝ መትከልና የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ሥራ የልጅነት ሕልማቸው ነበርና በእዚህ ላይ አላንገራገሩም፡፡ ከኅብረተሰቡ ባገኙት 10 ሄክታር መሬት እንዲሁም አምስት ሄክታር መሬት ለአርሶ አደር ካሣ ከፍለው በድምሩ በ15 ሄክታር ልማቱን ጀመሩ፡፡

በቅድሚያም ከፍተኛ በጀት በመመደብና ባለሙያዎችን በመቅጠር የተራቆተውንና የተጎዳውን መሬት ማገገም የሚያስችሉ ተግባራትን አከናወኑ፤ በመቀጠልም ከደቡብ አፍሪካ ድረስ የተለያዩ ዝርያ ያላቸውን ችግኞች በማስመጣት ተከሉ፡፡ የደን ልማቱ ሥራ እየጎመራ ሲመጣ ደግሞ ጎን ለጎን ሕዝቡን የሚጠቅሙ ተጨማሪ የልማት ሥራ መሥራት አለብኝ ብለው አሰቡ፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳሉም አካባቢው ለወተት ሃብት ልማት ምቹ መሆኑን ተገነዘቡ፡፡ የዓለም የወተት ቀን ሲከበር በተመለከቱት መሠረት የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ከብቶች ለልማቱ ወሳኝ መሆናቸውን ተረዱ፡፡ በሌላ በኩል ባለሙት ጫካ ውስጥ ያለው የግጦሽ ሣር ጋር ተዳምሮ  እሳቸውም በወተት ሃብት ልማት ቢሠማሩ ውጤታማ ሊሆኑ እንደሚችሉ አመኑ፡፡



በጥምር ግብርና ኢንቨስትመንቱ በቀን 300 ሊትር ወተት እየተመረተ ነው

ጊዜ ሳያጠፉም አስር ሚሊዮን ብር በመመደብና የተሻሻሉ ዝርያ ያላቸውን ጊደሮች በመሰብሰብ የከንዓን ጥምር ግብርና ኢንቨስትመንትን መሠረቱ፡፡ ከአካባቢው ያገኟቸውን ጊደሮች ከእስራኤል ምርጥ ኮርማዎች ጋር በማዳቀል የከብቶቻቸውን መጠን ከፍ አደረጉ፡፡ አሁን ላይ 65 የሚደርሱ ከብቶች በጥምር ግብርና ኢንቨስትመንቱ ያሉ ሲሆን፣ በተጓዳኝም 300 ዶሮዎችን እያረቡ ይገኛሉ፡፡ በ100 ዘመናዊ ቀፎችም የንብ ማነብ ሥራ ጀምረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በጥምር ግብርና ኢንቨስትመንቱ በቀን 300 ሊትር ወተት ይታለባል፤ ወተቱንም በአካባቢው የሚገኙ አቅመ ደካማ ሴቶች ተደራጅተው በቅናሽ ዋጋ ወስደው ለገበያ እንዲውሉ አድርገዋል፡፡ ባለሃብቱ በተጓዳኝም ማኅበረሰቡም ሆነ ወረዳው የተሻሻለ ዝርያ ያላቸው ኮርማዎች ዘረ-መል በነፃ በመስጠት የአካባቢው የወተት ሃብት ምርታማነት እንዲጎለብት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

ከኢንቨስትመንቱ ባሻገር ለዘመናት በጨለማ ይኖር ለነበረው የመንደራቸው ሕዝብ በራሳቸው ወጪ ትራንስፎርመር አስተክለው የመብራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም ክረምት በመጣ ቁጥር ፍዳውን ያይ የነበረው የሄጎ ቀበሌ ነዋሪ በኢንቨስተሩ ቀናነት አምስት ኪሎ ሜትር የውስጥ ለውስጥ መንገድ ተሠርቶለት እፎይ ብሏል፡፡ በአጠቃላይ የኢንቨስትመንት ሥራዎች 60 በላይ ዜጎች ቋሚ እንዲሁም ከ250 ለማያንሱ ሰዎች ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠር ችለዋል፡፡

‹‹ትልቁ ዓላማዬ የአካባቢውን ማኅበረሰብ መጥቀም ነው›› የሚሉት ኢንቨስተር አድማሱ፣ በተለይም የአርሶ አደሩን ኢኮኖሚ ማሳደግ በሚያስችሉ የልማት ሥራዎች ላይ መዋለ ንዋያቸውን በማውጣትና ምርቶቻቸውንም ወደ ውጭ በመላክ ለሃገርም የውጭ ምንዛሪ ግኝት ምንጭ ለመሆን ራዕይ ሰንቀው እየሠሩ መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡ አቶ አድማሱ ‹‹ወደ ኢንቨስትመንቱ ስንገባ 10 ሚሊዮን ብር ነው የነበረን፤ አሁን ኢንቨስትመንቱ ወደ 100 ሚሊዮን ከፍ ብሏል›› ይላሉ፡፡ ይህንንም ካፒታል በእጥፍ በማሳደግ ለግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ እድገት ወሳኝ ሚና ለመጫወት አቅደው እየሠሩ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡

‹‹የተሻሻለ ከብት ዝርያ ልማቱ በአካባቢው በሙሉ በደንብ ሲስፋፋ ማሽን በመትከል አሁን የምንሰጠውን ወተት መልሰን ከማኅበረሰቡ በመሰብሰብና በማቀነባበር



አቶ አድማሱ አርፍጮ

ምርቶቻችንን እስከ ውጭ ድረስ የመላክ እቅድ ይዘናል›› ሲሉም ያብራራሉ፡፡ ይህም ለበርካታ የአካባቢው ሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ ዕድል ይፈጥራል የሚል ትልም አላቸው፡፡

ይህ ራዕያቸው እንዲሳካ ግን በተለይ እንደ መብራት፣ ውሃና መንገድ ያሉ መሠረተ ልማቶች በመንግሥት በኩል እንዲሟሉም ጠይቀዋል፡፡ ‹‹የመብራትና የውሃ ችግር ሥራችንን ለማስፋፋት ፈተና ሆኖብናል፤ በድርጅታችን ሙሉ ወጪ ያስገነባውም የውስጥ ለውስጥ መንገድ በዋናው መንገድ ሥራ ሰበብ እየፈረሰና መልሶም እየተጠገነ ባለመሆኑ መስተጓጎል ፈጥሮብናል›› ሲሉም ኢንቨስተር አድማሱ ያብራራሉ፡፡ ያም ቢሆን ግን ለገጠማቸው ተግዳሮት እጅ ሳይሰጡ የሚችሉትን በራሳቸው አቅም እያሟሉ የኢንቨስትመንት ሥራቸውን ማስፋፋታቸውን እንደሚቀጥሉም ነው የሚያመለክቱት፡፡

ልክ እንደእሳቸው ሁሉ ከተለያዩ ሃገራት መጥተው ሃገራቸው ላይ መዋለ ንዋያቸውን አፍስሰው ልማት የጀመሩ ጥቂት የማይባሉ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን አንዳንድ ቦታዎች ላይ በሚስተዋለው አለመረጋጋትና በቢሮክራሲ የታጠረ የመንግሥት አሠራር ተስፋ ቆርጠው ወደመጡበት ሃገር መመለሳቸውንም አይሸሽጉም፡፡ ‹‹በሃገር ተስፋ አይቆረጥም፤ ደግሞም አሁን ያለው ችግር መፈታቱ፤ ሃገርም ሠላም መሆኗ አይቀርም፤ ያን ጊዜ ደግሞ አሁን ያለው ምቹ ዕድል እንደልብ ላይገኝ ስለሚችል ሸሽተው የሄዱ ባለሃብቶች ወደፊት እንዳይቆጫቸው ተመልሰው ሕዝባቸውና ሃገራቸውን ሊያገለግሉ ይገባል›› ሲሉም ምክረ ሀሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

ከሌሎች ኢንቨስትመንቶች ይልቅ በግብርና ኢንቨስትመንት ላይ መሠማራት የተለያዩ ተግዳሮቶች ያጋጥማሉ ሲሉም ጠቅሰው፤ ፈተናውን ሁሉ ተቋቁሞ ሕዝቡን ማገልገል የግድ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ‹‹ምክንያቱም የተወለድነው ከዚያ ማኅበረሰብ በመሆኑ የዚህን ሕዝብ ችግር መካፈል አለብን፡፡ ደግሞም የእኛ ተንደላቆ መኖር ብቻውን በቂ አይደለም›› ይላሉ፡፡

በመሆኑም እያንዳንዱ ዲያስፖራ ሌላ ሃገር ሲኖር ያገኘውን ልምድ በመቀመር ሕዝቡን የሚጠቅሙ ልማቶች ላይ መሳተፍ እንዳለበትም ያስገነዝባሉ፡፡ ‹‹ችግሮችን በማየት ሀገር ጥሎ መሄድ መፍትሔ አይሆንም፡፡ ችግሮችን ተቀብሎ ነገሮች ይቀየራሉ ብሎ ተስፋ ሰንቆ መንግሥትንም እየደገፉ መሥራት አለበት›› ሲሉ ያብራራሉ፡፡

‹‹አሁን ላይ እኔ ትርፍ አልጠብቀም፤ ዛሬም ድረስ ኢንቨስት እያደረኩ ነው ያለሁት፡፡ ሥራው ዋጋ ቢያስከፍለኝም ነገ ውጤት እንደሚያመጣ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡›› ሲሉ ጠቅሰው፣ ኅብረተሰቤን ማገልገል በራሱ ትልቅ ነገር እንደሆነም ይናገራሉ፡፡ ሌሎችም የእሳቸውን ተሞክሮ እንዲቀስሙ ይመክራሉ፡፡ በተለይም በኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገራት የተሻለ ምቹ የአየር ንብረትና ሥነምሕዳር እንዳለ ጠቅሰው፣ ዜጎች በግብርና ኢንቨስትመንት ሥራ ላይ ቢሠማሩ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አመልክተዋል፡፡

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ  ተክሌ ኃይለማርያም(ዶ/ር) እንደሚሉት፤ ባለሃብቱ ለ20 ዓመታት በውጭ ሃገር ያገኙትን ሃብት በሀገራቸው ሥራ ላይ በማዋል ከፍተኛ አደጋ ውስጥ የነበረውን የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት በመታደግ ረገድ ያከናወኑት ሥራ ለግብርናው ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ወሳኝ ሚና አበርክቷል፤ እያበረከተም ይገኛል፡፡ በዚህ ሥራቸው ተመናምኖ የነበረው ደን አሁን ተመልሷል፤ የአካባቢው ልምላሜና እርጥበትም አንሰራርቷል፡፡ አካባቢው የእንስሳት ሃብት በስፋት የሚገኝበት እንደመሆኑ ለከብት መኖ የሚውሉ የሣር ዝርያዎች በስፋት በመብቀላቸው ኅብረተሰቡ ለመኖ ግዢ ያወጣ የነበረውን ከፍተኛ ወጪ ማስቀረት አስችሏል፡፡

በጥምር ግብርና ኢንቨስትመንቱ በየቀኑ የሚታለበው ወተት ደካማና ደጋፊ የሌላቸው የአካባቢው እናቶች በቅናሽ ዋጋ የሚያገኙበት ሥርዓት በመበጀቱ ሲያሻቸው አትርፈው ለመሸጥ፤ አሊያም ቂቤና አይብ በማድረግ ለቤተሰባቸውና ለተጨማሪ የገቢ ምንጭ እንዲያገኙ ማድረጉ በርካቶች ከድህነት እንዲወጡ የበኩሉን አስተዋፅዖ እያበረከተ መሆኑን ተክሌ (ዶ/ር) ያመለክታሉ፡፡

‹‹ድርጅቱ ከሁሉም በላይ የተሻሻለ ዝርያ ያላቸውን ኮርማዎች ዘረ̈መል በነፃ የሚያሰራጭ መሆኑ ለከንባታ ማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን እንደሃገርም በቀንድ ከብት ሃብት የላቀ ተጠቃሚ እንድንሆን ያደርጋል›› ይላሉ፡፡ የሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት በአካባቢው ያለውን የመሠረተ ልማት ችግር በመፍታት ድጋፍ እንዲያደርጉ እሳቸውም ጠይቀዋል፡፡

ጎሜ

# መንግስት የመኖሪያ ቤት ኪራይ

# አዋጅን በነካበት እጁ....

**ምሕረት ሞገስ**

ሶስቱ ጓደኛሞች ምንም እንኳ ከአስር ዓመታት ያላነሱ ጊዜያትን አብረው ቢያሳልፉም፤ የኑሮ ደረጃቸው በእጅጉ የተለያየ ነው። አንደኛው ምክንያት ቤት ነው። ገብረየስ በደህና ጊዜ የጋራ መኖሪያ ቤት ደርሶታል። ተሰማ ደግሞ በቅርቡ የ40/60 የጋራ መኖሪያ ቤት ዕድለኛ ሆኖ ከኪራይ ቤት ወጥቶ በቤቱ ለመኖር በቅቷል። ዘውዴ ግን አሁንም በኪራይ ቤት እየተንገላታ ነው። ዘውዴን የቤት ኪራይ ዋጋ ቁልቁል እንደካሮት ሲቀብረው አዲስ ቤት ያገኘው ተሰማ ደግሞ ተመችቶት ዓለሙን መቅጨት ጀምሯል።

ሶስቱም ከተገናኙ ሰነባብተዋል። መቆየታቸውን ምክንያት በማድረግ ከሌላ ጊዜው ለየት ያለ ቦታ መሔድ ፈልገዋል። ቀድመው በመነጋገራቸው ጋባዡ ተሰማ መንግስቴ የሚያውቀው መጠጥ ቤት በከፍተኛ ወጪ ሊጋብዛቸው መፈለጉን አስታወቀ። ዘውዴ መታፈሪያ እና ገብረየስ ገብረማሪያም ለመጋበዝ በመጓጓታቸው ይሁን ወይም ከተገናኙ በመቆየታቸው ገና ሳይመሽ አስር ሰዓት ቀድመው ማምሻ ግሮሰሪ እየተጨዋወቱ ተሰማን ሲጠብቁት ዘውዴ የተለመደ ምሬቱን መናገር ጀመረ።

‹‹ከአከራዮቼ ጋር በዚህ ወር ቤቱን እንደምለቅላቸው ተስማምቼ ነበር። በየሶስት ወሩ 50 በመቶ እየጨመሩብኝ ሲያማርሩኝ ለሶስት ወር አልጨምርም፤ ከዛም እለቅላችኋለሁ ብያቸው ነበር። የተከራየሁትን ቤት ለመልቀቅ ሳስብ ደግሞ የሚገኘው ቤት ከነበርኩበት የወረደ ዋጋው ደግሞ ቀድሞ ከምከፍለው በእጥፍ የሚጨምር ነው። በተጨማሪ ደላሎቹ ቀድሞ የስድስት ወር ክፈል ብለው ያስገድዳሉ። ለእነርሱ የሚከፈለው የ10 በመቶ ክፍያ በስድስት ወር ሲባዛ የአንድ ወር የቤት ኪራይ የሚያህል ነው። በእኔ ደሞዝ እንኳን ልጆች ይዞ ለብቻም ለመኖር አዳጋች ሆኗል። ብቻዬን ብኖር ጎዳና ላይም እተኛ ነበር። አሁን አሁንማ ልጆቼን አስቤ እንጂ አንዳንዴ መሞት ያምረኛል›› በማለት ሰሞኑን ሲያስጨንቀው የነበረውን ለገብረየስ ተነፈሰ።

ገብረየስ በበኩሉ ‹‹ ዛሬ እኮ በዘመኑ አለኝ የሚል ሰው የሚጠጣውን መጠጥ ለመጠጣት እና በሰፊው ለመዝናናት በተቀናጣው መጠጥ ቤት ለመገናኘት የምንችልበት ቀን ነው። ቢያንስ ዛሬ አትማረር።›› አለው። ይህንን እየተነጋገሩ፤ የገብረየስ ስልክ ጠራ። ደዋዩ ተሰማ ነበር። ቦሌ አካባቢ የሚገኘውን የመጠጥ ቤት ስም ጠርቶ ‹‹ከተገናኛችሁ ሲመሻሽ ጠያይቃችሁ ኑ።›› አለ። ገብረየስ በተሰማ ሃሳብ አልተስማማም፤ ‹‹ ግብዣው ከልብህ ከሆነ መጥተህ ውሰደን፤ የጠራኸው መዝናኛ ቤትን አናውቀውም። ያለአንተ ቦሌ ደርሰን መዝናናት አይሆንልንም።›› አለው።

ተሰማ ‹‹ ሳቀና እሺ እንደውም ቅርብ ነኝ፤ መጥቼ እወስዳችኋላሁ።›› አለ። ገብረየስ ፈገግ ብሎ፤ ‹‹ይቀልዳል እንዴ? በምናችን እንዴት ብለን ልንደርስ ነው?›› ሲል፤ ዘውዴ በራሱ ሃሳብ ተጠምዷልና ገብረየስ የሚለውን አልሰማም። ዘውዴ ፍዝዝ ብሎ ፊት ለፊቱ ያለውን ድራፍት ሲጎነጭ፤ ገብረየስ አዘነለት። ‹‹ እኔ የምልህ የዛሬው ግብዣ ይቅር እና የአንድ ወር የቤት ኪራይ ይክፈልልህ።›› ሲለው፤ ዘውዴ በጣም ተበሳጨ። ‹‹ ይህን ያህል ዓመት ተምሬ፤ ከሁለት አስርት ዓመታት ለሚበልጡ ዘመናት ሕዝብን እና መንግስትን አገልግዬ ቢያንስ ያለጭንቀት በልቼ ከነልጆቼ የማርፍበት ማጣቴ ያሳዝናል። አልፎ ተርፎ ልመና ውስጥ ከምገባ ሞቴን እመርጣለሁ።›› አለው።

ገብረየስ፤ ‹‹ ዛሬ ደጋግመህ ስለሞት የምትናገረው ምን ሆነህ ነው? ሞትማ ለማንም አይቀርም። ነገር ግን ራሱ ሲመጣ እንጂ በግድ ልሙት ብሎ ከፈጣሪ ጋር መከራከር ውጤት አያመጣም። ሁሉም ያልፋል። ምናልባት አንተም የቤት ባለቤት የምትሆንበት ቀን ይመጣል። በዛ ላይ አዲሱ የመኖሪያ ቤት አዋጅ ወጥቷል። እርሱን በደንብ አንብብ እና ከአከራዮችህ ጋር ተደራደር።›› ሲለው ተሰማ ደረሰ።

‹‹ደግሞ የምን ድርድር ነው›› ሲል ጥያቄ አቀረበ። ‹‹የዘውዴ የቤት ችግር ከስሩ የሚፈነቀለው መቼ እንደሆነ ይናፍቃል።›› ሲል ገብረየስ ምላሽ ሰጠ። ‹‹ እኛ ደህና፤ የቤት ችግር ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ አይደለም። የትም አገር መካከለኛው እና ከፍተኛው እንጂ የዝቅተኛ ደረጃ ነዋሪው የቤት ችግር የሕይወት ዘመኑ የታሪክ አካል ነው። በእርግጥ የእኛ አገሩ ችግር ከባድ ቢሆንም በሂደት መሻሻሉ አይቀርም። እንደሰሞኑ ለተከራይም ለአከራይም የሚያመቹ አዋጆች ከወጡ በቀጣይም ችግሩ የሚቃለልበት ሁኔታ ትኩረት ከተሰጠው አትጠራጠር ችግርህ መቃለሉ አይቀርም።›› አለው።

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹በእርግጥ ለእናንተ ለማስረዳት ከባድ ነው። ምክንያቱም የችግሩ ስፋት እና ጥልቀት አይገባችሁም። አሁን ላይ አዲስ አበባ ውስጥ የቤት ባለቤት አለመሆን ድህነት ብቻ ሳይሆን ለውርደት የሚዳርግ ከባድ ችግር ነው። እጅግ ሞራል የሚነካ ራስን የሚፈታተን ታግሎ አሸናፊ ለመሆን የማይቻልበት ትልቅ ፈተና ነው።›› ሲል ተሰማ ፈገግ አለ።

ተሰማ፤ ‹‹ በዘመንህ በጣም ብዙ ፈተናዎች አሉብህ። ፈተናዎቹን ለማለፍ የምትችለው አንተ ነህ። የሌሎች አካሎች ማለትም መንግስትን የመሳሰሉ አካላት ሲደግፉህ ዕድሉን መጠቀም አለብህ። አሁን አንተ የምትኖረው ተከራይተህ ነው። የቤት ኪራይ ዋጋ ያለአግባብ እንዳይጨመርብህ መንግስት አዋጅ አውጇል። መንግስት ካልፈቀደ መጨመርም ሆነ ማባረር አይችሉም። ከዚህ በኋላ የሚጨመርብህ መንግስት ባስቀመጠው መሠረት ብቻ ነው። ልቀቅ የምትባለውም በአዋጁ መሠረት ቤቱ ላይ ዋጋውን የሚቀንስ ጉዳት ስታስከትል፣ ቤቱን ከተከራየህበት ማለትም ከመኖሪያነት ውጪ ለሌላ ዓላማ ካዋልክ ወይም ቤቱ ከተሸጠ እና የቤት ኪራይ በአግባቡ የምትከፍል ካልሆነ ነው።

አንተ ቤቱን በአግባቡ ያዝ፤ የሚጠበቅብህን የቤት ኪራይ ገንዘብ በአግባቡ ክፈል፤ ከዛ ውጪ ውጣ ብትባል ለማህበረሰባዊ ፍርድ ቤት፣ ለፖሊስ ጣቢያ ወይም ሌላ መሃል ላይ ሆኖ ችግሩን ሊፈታ ለሚችል አካል አሳውቅ። በተረፈ ማንም ቢሆን ሊያስወጣህ አይችልም። ስለዚህ ጭንቀት አያስፈልግም።›› አለው።

ዘውዴ ፈገግ ብሎ፤ ‹‹ ወይ መሬት ያለ ሰው!›› አለው። ተሰማ በበኩሉ ‹‹ መሬት ላይ እንደማልኖር አየር ላይ ተንጠልጥዬ ወደቅኩ አልወደቅኩ እያልኩ እንደምሳቀቅ ታውቃለህ። ነገር ግን ብወድቅም አልሳቀቅም። ነገር የሚከብደው ባከበድከው ልክ ነው። ቀለል ስታደርገው ራሱ ይቀላል። በአዋጁ ደስ ልትሰኝ ይገባል።›› አለው።

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹ በእርግጥ አዋጁ ደስ ይላል። ነገር ግን አንተ በምትኖርበት የጋራ መኖሪያ ቤት ወለል ላይ ብዙ ቤት ተዘግቶ ሰው እንደማይኖርበት ነግረኸኝ ነበር። ወይም ለምን እዛ አይከራይም?›› አለው። ‹‹ በእኛ አካባቢ ባሉ መኖሪያ ቤቶች ትልልቅ ፎቆች ውስጥ በትንሹ ከ40 ያላነሱ ቤቶች ሳይከራዩ በራቸው ዝግ ነው። የኤሌክትሪክ አገልግሎትም ሆነ ውሃ ገብቷል። የሚገርመው አንዳንዶቹ ቤቶች በደንብ ፀድተው የተሰሩ ናቸው። ነገር ግን የቤቶቹ ባለቤቶች ይሁኑ ደላሎቹ የሚጠሩት ዋጋ በጣም የተጋነነ ነው። በዚህ ምክንያት ከእያንዳንዱ ሕንፃ በአማካኝ 40 ቤት በአጠቃላይ ከ13 ሕንጻ ምን ያህል ቤት ሳይከራይ ቁጭ ብሏል ብሎ ለማስላት ቀላል ነው። በእርግጥ ለአከራዮቹ ተራ ነገር ሊሆን ይችላል። በዛች አካባቢ ያለውን የቤት ፍላጎት ለማስታገስ የሚጫወተው ሚና ቀላል አይሆንም። አዋጁ የጋራ መኖሪያ ቤት ያለነዋሪ መቀመጥ የለበትም ብሎ ቢያስገድድ መልካም ነበር።›› ሲል ያለውን ሃሳብ ገለፀ።

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹ ለነገሩ ያ ብቻ አይደለም። አሁንም በስፋት ግንባታቸው ተጀምሮ ያልተጠናቀቁ የጋራ መኖሪያ ቤቶች አሉ። ሌሎች ደግሞ ዕጣ ከወጣባቸው አምስት ዓመታትን ቢያሳልፉም እስከ አሁን ኤሌክትሪክ እና ውሃ ያልገባባቸው ለነዋሪዎች ምቹ ያልሆኑ ሕንፃዎች አሉ። እነዚህን መሠረተ ልማቶች የማሟላት ግዴታ ያለባቸውን ተቋማት ምክር ቤትም ሆነ ሌላ ተቆጣጣሪ አካል አስጨንቆ እንዲሰሩ እና የከተማዋ የመኖሪያ ቤት ችግር እንዲቃለል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ለነዋሪ የተላለፉ ግን ደግሞ የተዘጉ የማይከራዩ ቤቶች እንዲከራዩ ያለበለዚያ ወደ መንግስት እንደሚመለሱ እና ዕድሉን ላላገኙ የከተማዋ ነዋሪዎች እንደሚተላለፉ ቢገለፅ ሁሉም ያከራይ ነበር። የሚከራይ ቤት ሲበዛ ደግሞ ዋጋውም ይረጋጋል።›› አለ።

**ለነዋሪ የተላለፉ ግን ደግሞ የተዘጉ የማይከራዩ ቤቶች እንዲከራዩ ያለበለዚያ ወደ መንግስት እንደሚመለሱ እና ዕድሉን ላላገኙ የከተማዋ ነዋሪዎች እንደሚተላለፉ ቢገለፅ ሁሉም ያከራይ ነበር:: የሚከራይ ቤት ሲበዛ ደግሞ ዋጋውም ይረጋጋል**

ዘውዴ በበኩሉ፤ ‹‹ችግሩ አንድም ተገቢውን ሕግ አለማውጣት ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ የወጣውን ሕግ አለማስተግበር ነው። ችግሩ የሰፋ በመሆኑ ተከራዮች አከራዮች የሚሉትን በሙሉ ለመፈፀም ዝግጁ ናቸው። አከራዮች ደግሞ ሕግን ለመተግበር ፈቃደኞች አይደሉም። የከተማ አስተዳደሩ አከራዮች ዋጋ እንዳትጨምሩ ቢልም፤ አከራዮችም ዋጋ ሲጨምሩ ተከራዮችም ጨምሩ የተባሉትን ሲከፍሉ ኖረዋል። ችግሩ የሚቃለለው በአዋጅ ሳይሆን እጥረቱን በሚያቃልል መልኩ ቤቶችን በብዛት መስራት ሲቻል ነው። የቤት ኪራይ ችግር ከሥሩ ይፈነቀላል የሚል እምነት የለኝም።

በየትኛውም ዓለም የመኖሪያ ቤት እጥረት አለ። ነገር ግን የኢትዮጵያን በተለይ የአዲስ አበባን ያህል የቤት ችግር ያነቀው እና ያስጨነቀው ከተማ አለ ለማለት እቸገራለሁ። በእርግጥ ሰሞኑን ወደ አቃቂ ቃሊቲ ከገላን አቅራቢያ 60 ሺህ ቤት ሊገነባ መሆኑን ይፋ ተደርጓል። የመሠረት ድንጋይም ተቀምጧል። ነገር ግን አንተ እንዳልከው ሳይጠናቀቁ ተንጠልጥለው ያሉትን በፍጥነት ማጠናቀቅ፤ መሠረተ ልማት ያልተሟላላቸውን በአስቸኳይ እንዲሟላላቸው ማድረግ፤ ተመኑን በተመለከተም በፍጥነት ይፋ ማድረግ ይገባል። የወጣው አዋጅም እንዲተገበር እስከ ታች መግፋት ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ ቢያንስ የግል ቤት ባይኖረንም በኪራይ ቤት ተረጋግተን መኖር እንችላለን።›› ሲል መሠራት አለባቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ጉዳዮች ገለፀ።

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹ በእርግጥ ይህ አዋጅ በጣም ለመተግበር የሚመች አዋጅ ነው። አከራዩንም ሆነ ተከራዩን የሚጠቅም ነው። ተፈፃሚ ካልሆነ ያለውን ተጠያቂነትም አስቀምጧል። በተረፈ መንግስትም ተገቢውን ግብር እንዲሰበስብ ያግዛል። ስለዚህ የአሁኑ አዋጅ ማንንም የሚያስደስት እንጂ የሚያስከፋ አይደለም። በተለይ እንደአንተ አይነት በየጊዜው ጨምር እና ውጣ እየተባለ የሚንገላታ ተከራይ መደሰት አለበት። አሁን ሰዓቱ እየደረሰ ነው ወደ መዝናናታችን ብንሔድ ይሻላል።›› ብሎ ወደ አሽከርካሪው ደወለ።

ቦሌ ያ ብዙዎች ያደነቁት ቤት ደረሱ። መቀመጫው እንደማምሻ ግሮሰሪ ደረቅ ወንበር ሳይሆን የተቀናጣ ሶፋ ነው። ገና በጊዜ በመግባታቸው ብዙ ሰዎች እና ሰፊ መስተንግዶ አላገኙም። እየቆየ ቤቱ መሙላት ሲጀምር ግን መስተንግዶ ተቀላጠፈ። የሙዚቃ ባንድ ቆሞ ዘፋኞች በየተራ እየወጡ መዝፈን ጀመሩ። አስተናጋጆች ሳይጠሩ፤ ‹‹ ምን እናምጣ? ምን ይጨመር?›› እያሉ ተከተለተሉ። አሻሻጭ ሴቶች ተኮለኮሉ።

ለጠጪዎች ‹‹ ይህ መጠጥ እኮ ምርጥ ነው። ይህኛው ከዚህኛው ይሻላል። ያንን አምጡላቸው ይህንን ቀይሩላቸው።›› እያሉ በየጠረጴዛው የሚዞሩት አጫፋሪዎች፤ ምንም እንኳ ተኳኩለው መልካቸው ቢያምርም፤ ዘውዴ ግን ስጋ ያየ ጥንብ አንበሳ አድርጎ ሳላቸው። ዘፋኞቹ ደጋግመው ተቀራራቢ ዘፈን ይዘፍናሉ። መጠጡም ሆነ ዘፈኑ አጠቃላይ የቤቱ ሁኔታ ዘውዴ እና ገብረየስን አስገርሟቸዋል። ተሰማ ደግሞ ደስ ብሎት መጨፈር ጀመረ። ዘውዴ ከመደሰት ይልቅ አይ ዘመን እያለ የተቀዳለትን መጠጣቱን ቀጠለ።

# የዘመን ጥበብ

## ከሕሊና ጅረት




**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ኪነ ጥበብ ትናንትናም ሆነ ዛሬ ለጥበብ የሚሰጠውን አጥቶም ሆነ ነፍጎ አያውቅም። ሁሌም አዳዲስ ስጦታዎች እንደጎረፉ ናቸው። እናስ ኪነ ጥበብ ከሰሞኑ ምንስ አዲስ ነገር ይዞ ብቅ ብሎ ይሆን...ስጦታው ትልቅም ይሁን ትንሽ ያቺኑ ጭብጦ በቀኝ ይዘን፤ በደረቁ እንዳያንቀን በትንታም እንዳይኮረኩመን በግራ ደግሞ መማጊያ የሚሆኑንን ሀሳቦች እያነሳን ፉት እንላለን።

ከሰሞኑ ከኪነ ጥበብ መንደር ከተፍ ያለው አዲስ ጉዳይ በህሊና ታሽቶ፤ በህሊና የማንነትና የምንነት መዳፍ ሸንተረሩን እየሰራ የወጣ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ነው። ከህሊና የሚፈልቁ የማንነት ጅረቶችም፤ የዚህን ሸንተረር መስመሮችን እየተከተሉ እንደ አባይ ወንዝ ይፈሳሉ። በሌላ አቅጣጫም ከአንድ ስፍራ ሰክነው እንደ ጣና ሀይቅ ይንጣለላሉ። ይህን ተከታታይ ድራማም፤ ከዚህ ቀደም በ"አጼ ማንዴላ፤ ድንግሉ፤ ሚስቴን ዳርኳት፤ የፍቅር ጥግ፤ የፍቅር ሰው..." በእነዚህና በሌሎች ፊልሞች ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ለመድረስ የቻለው፤ የሳልቃን ፊልም ፕሮዳክሽን አሁን ደግሞ በይዘቱም ሆነ በአይነቱ የተለየ "ህሊና" የተሰኘ ተከታታይ ድራማ ይዤ ቀርቤያለሁ ሲል ከአጋሮቹ ጋር በይፋ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥቶበታል።

ፕሮዳክሽኑ እንደ ፊልም ላቅ ያለ ደረጃን የያዘ ቢሆንም በተከታታይ ድራማ ይህ የመጀመሪያ ሥራው ነው። ይህን ድራማ ለዚህ ለማድረስ ሁለት ዓመታት ፈጅቶበታል። እውቅ የፊልምና ድራማ ባለሙያዎችን እንዲሁም 2 መቶ ያህል ተዋናይናን ይዞ ወደፊት የሚገሰግሰው "ሕሊና" ምንስ ያሳየን ይሆን..

"ህሊና" የዋና ገጸ ባህሪዋ ስም ቢሆንም ግን ደግሞ ለስያሜ ያህል ብቻ የተቀመጠ አይደለም። የታሪኩ የመነሻ ገመድ እየተጠቀለለ ክቧን የሕይወት ዓለም የሚሠራበት ጠጣር ህብለሰረሰር ነው። ሁላችንም እንደየመልካችን አሻራ ማንነታችን የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፤ ይህን ማንነት የሚሠራው ደግሞ ህሊናችን ነው። የእሾህ ፍሬ የበተኑበት ህሊና ለከርሞ ስንዴ አብቅሎ አናገኘውም። ከፊት የሚታየው ማንነታችን የበቀለው ከውስጥ በተዘራው የህሊናችን ማሳ ላይ ነውና ድራማው ውስጥ የምንመለከታቸው እያንዳንዱ ትዕይንቶች በህሊና ገመድ የተጠፈሩና በተሻለ እይታ የምንረዳቸው ናቸው።

ይህቺ የድራማው ዋና ገጸ ባህሪ የራሷ ብቻም ሳትሆን የማህበረሰቡ ነጸብራቅ ሆና ትታያለች። ድራማው በሚያጠነጥኑበት መንገድ ላይ ህሊና ከወዲያና ከወዲህ ባለ የማንነት ባላ በሁለት ጫፍ ገመዱ ተወጥሮ፤ አንዴም ለመበጠስ ሲከር፤ አንዴም ሲላላ፤ ደግሞ መልሶ ሲወጠር እናያላን። በድራማው ውስጥ ያለችውን የህሊናን ማንነት በአይን አይተን በልብ ለመፍረድ የምንቸገርበትና የእርሷ ውጫዊ ማንነት በእኛ ውስጣዊ ህሊና ላይ የተመሠረተ ነው።

አንድ ጊዜም አብረን ስናለቅስላት ሌላ ጊዜም ልባችንን እርር! እያደረገች በቃላት ናዳ የምናወርድባት አይነት ልጅ ናት። በአስተዳደግና በድሮ ማንነቷ በዛሬና በአሁን እሷነቷ ውስጥ የሚፈጠሩት ግጭቶች እያየን የምናልፋቸው ሳይሆን እራሳችንን እያስተያየን የምንሄድባቸው ናቸው።

ጥሩ ህሊና ችግሮችን ሁሉ ወደ መፍትሄነት ይቀይራቸዋል፤ የደከረተ ህሊና ግን መልካም መፍትሄዎችንም ወደ ችግር ይለውጣቸዋል። በ"ህሊና" ውስጥ ህይወት ትነጋለች ደግሞ ትጨልማለች። አንደኛው ከፀሐይ ጋር አንዱም ከጨረቃ ሌላኛውም፤ ደመና ብርሃን፤ ጨለማ ሁሉም እየተፈራረቁ በህይወት መስኮት ሲገቡና ሲወጡ እንመለከታለን። ህሊና ውስጥ ህይወት እንዲህ ናት፤ እንደሚገባና እንደሚወጣው ሁሉ የእርሷም ማንነት ለአንዱ ጨለማ ለሌላኛው ብርሃን ናት።

የህይወት ዕጣ ፈንታዬ ነው ብላ የፍቅር ጉዞ የጀመረችበት መንገድ በቀጥታ ይዟት ወደ ጠላቷ ቤት ያደርሳታል። ከአንድ ቤት ከአንድ ቤተሰብ የህይወቷ ሁለት ማንነቶች ሲፋጠጡ ህሊና ማንን ትምሰል? የድራማው ጭብጥ በሌላኛው መስመሩ የሴት ልጅን ዘመናዊ ጥቃቶች ያሳየናል። ገንዘብ በፍቅር ላይ፤ ገንዘብ በህሊናና በማንነት ላይ እግሩን ሰቅሎ ቁልቁል በጫማው ሲረግጥ አይንና ልብ ተጨፍነው ይጨልማሉ። በተለይ ደግሞ አሁን አሁን በከተማችን አዲስ አበባ ላይ መልኩን ቀይሮ የመጣውን ዘመናዊ የጥቃት ልምድ እየሸለተ ውስጥ ውስጡን ያሳየናል።

ልብ ሲሰበር መንፈስም ይሰበራል፤ ህሊና ይደማል ይቆስላል ግን በምን ይሽራል? አንዳንዴም የገዛ ህሊና ይከዳል፤ አብዝተው የማንነት በረሃ ላይ ከተጓዙ ይደክመዋልና ከአንደኛው ክምር አሸዋ ላይ ገብቶ ይሰወራል። በዚህም በማንነት ከማህበረሰብ ሸሽቶ፤ በተወላገደ ጫማ የሚደረግን ጉዞ መዘዝና የመጨረሻውን መልኩን እናያለን። በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ነቅሶ ከማሳየት አንጻርም ድራማው ብዙ የታሰበበት ይመስላል።

በሀገራችን ኪነ ጥበብ ውስጥ የተከታታይ ድራማ ያለው እድሜ እጅግ ትንሽና የቅርብ ጊዜ ታሪክ ነው። ለጥበብ ከተበረከቱ ስጦታዎች መሃከልም ትኩስነቱ ያልበረደና በአዲስነት ቃናው እንዳለ ነው ለማለት እንችላለን። ጥቂት ዓመታትን ወደኋላ መለስ ስንል በኢትዮጵ የጥበብ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያ የነበረው የ"ገመና" ድራማ ከማናችንም ማህደረ ትውስታ ውስጥ የተፋቀ አይመስለኝም። እሁዳችንን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጣቢያ ከልባችን ጋር አጋምዶት፤ በፍቅር እየተመለከትነው፤ እየጣፈጠን አጣጥመነዋል።

ቀጥሎ ሁለተኛውን እርካብ "ሰው ለሰው" ድራማ ሰራው። አይናችን ፈጦ ልባችን እንደ ፊኛ እስኪወጠር ድረስ አብረን ከገጸባህሪያቱ ጋር እላይ ታች ብለንበታል። እያሉም ቀጥለው ዛሬ ላይ ብዙ ተባዝተዋል። መቼም በዛራና ቻንድራ እንኳን ቀልባችን ጠፍቶ ቀልብ ፍለጋ የወጣንበት አንድ ሰሞንም አለና እንዲህ በሀገራችን ድራማዎች ቢጠፋም መልካም እንጂ የሚቆጭ አይደለም። የግል የቴሌቪዥን ጣቢያዎችና ዓለም ዓቀፍ የሳተላይት ስርጭት ከዲኤስ ቲቪ ጋር ብቅ ማለታቸውን ተከትሎ ደግሞ የተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ፤ ገና ከውልደቱ የኪነ ጥበብ መንደር አብዮት ቀስቃሽ ሆኗል። እናም ዛሬ ላይ ጣቢያው በየአይነቱ፤ ድራማው በየፈርጁ ሆነና እንደየፍላጎታችን እየመረጥን እንኮመኩም ይሆናል እንጂ የተከታታይ ድራማ ፍቅራችን ላይ ንፋስ ገብቶበታል ለማለት አንችልም።

በዚህ ሁሉ የምናጤነው አንድ ነገር ቢኖር ተከታታይ ድራማዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው ተቀባይነትና ተወዳጅነት እጅግ ከፍ ያለ መሆኑን ነው። ለዚህ ደግሞ ልንጠቅሳቸው የምንችላቸው ምክንያቶች አሉ። የመጀመሪያው ነገር ከህጻናት እስከ አዛውንቱ፤ ከሊቅ እስከ ደቂቁ ስለሚታጨቁበት እያንዳንዱ ሰው እራሱን ከአንደኛው ስፍራ ላይ ያገኝበታል።

የሚተላለፉት ሰፊው ሕዝብ በሚከታተለው የቴሌቪዥን ጣቢያ እንደመሆኑ በድራማው ከሚነሱ ጭብጦቹ እያንዳንዱን ተመልካች ያገናዘቡ ናቸው። ርዕሰ ጉዳዮቹም ከማህበረሰቡ የወጡ፤ የማህበረሰቡ መስታየቶች ናቸው። በእያንዳንዱ ክፍል የሚፈጠሩት አዳዲስ ሴራዎች አሰልቺ እንዳይሆን ያደርጉታል። እያደር እንደ ወይን ለሚጣፍጠፈው ጥፍጥናው ደግሞ ልብ ሰቃይ ልብ አንጠልጣይነቱ ይህን መሳዩን መልክ ሰጥቶታል።

ከላይኛው የሀሳብ ጥልፋችን አንዲቷን ሰበዝ መዘን ስንመለከት፤ አንድ ጥያቄ ውልብ ካለብን ይህን መሳይ ነው፤ መምጣቱንስ ብዙዎች ይመጣሉና "ህሊና" ምን የተለየ ነገር ይዞ መጣ? ጥያቄው ወሳኝና አግባብ ነው። ስለ ድራማው በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ፤ ብዙ አዳዲስ ነገሮች እንዳሉበት የሳልቃን ፊልም ፕሮዳክሽን ገልጿል። ነገር ግን ቀደም ሲል በነበረው የድራማው ሂደት ከሲኒማቶግራፊ የቦታ መረጣና ቀረጻው አንስቶ ድራማውን በኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ መንደር ውስጥ ከፍ ባለ ደረጃ እንዲቀመጥ ለማስቻል መደረግ ያለበትን ሁሉ ከማድረግ አልተቆጠብንም። ተመልካቹም እንዳይጎረብጠው ብቻም ሳይሆን እየወደደው በተመስጦ አይኑን ሳይነቅል የሚያየው ድራማ አድርገው ስለማዘጋጀታቸውም ከጋዜጠኞች ከቀረቡላቸው ጥያቄዎች አስታከው ገልጸውታል። ከሙያዊ ጉዳዮች አንጻር፤ "በትንሹ ሎኬሽን ላይ እንኳን ያለምንም መገደብ ተንፍሰን የሰራንበት ነው" በማለት ከዚህ ቀደም በሀገራችን ፊልሞችም ሆኑ ድራማዎች ላይ በተደጋጋሚ ይነሱ የነበሩ ትችቶች አሉና በዋናነት ይህን ሰንኮፍ ለመቅረፍ ከእስክሪፕት ጀምሮ ሁሉንም ነገሮች በጥንቃቄ ስለማዘጋጀታቸው ዳይሬክተሩ ይናገራል።

እስከዛሬ ከነበረው ልምድ አንጻር ከሙያዊ የጥራት ምልከታ አንጻር ፊልሞቻችን ከድራማው የተሻሉ ናቸው። በፊልሙ ላይ የብዙ ዓመታት ልምድና እውቀት ያለው ሳልቃን በዚህ መልክ ወደ ድራማው በመግባቱ ምናልባትም የተሻሉ ነገሮችን እንድናይ ያደርገናል። አዘጋጆቹ የ"ህሊና" ድራማን የሠሩነው፤ ቀደም ሲል ለድራማዎች ይደረግ በነበረው አይነት ሳይሆን ለፊልሞች ይደረግ በነበረው መልኩ ነው ሲሉ አንድም ከዚሁ ነው። ምን የተለየ ነገር ይዞ መጣ? የሚለው ጥያቄ በተከታታይ ድራማ ውስጥ በአንድ ጀንበር የሚመለስ አይደለም። ምክንያቱም፤ እንደ ፊልምና ቲያትር አስቀድሞ መጀመሪያና መጨረሻው ተመጥኖ የሚደቆስ አይደለምና በጅምር ላይ ያልታሰቡና ያልታዩ ብዙ አዳዲስ ነገሮችን በመሀሉ ልንመለከት እንችላለን።

ታዲያ የ"ህሊና"ን ምናባዊ አፈር ፈጭተው፤ ጭቃውን አቡክተው፤ ከዚያም ነብስ ዘርተው መልክና ደምግባቱን ያበጁ እነማን ናቸው፤ ከምትለው ዳገት ላይም ጥቂት እንሸራተት። ጽንስ ሳይኖር ውልደት የለም፤ የመነሻ ሀሳቡ በራሱ በፕሮዲዩሰሩ ዮሴፍ ካሳ ሲሆን በድርሰት ደረጃ ተለውሶና ልሞ የተድቦለቦለው ደግሞ በዋና ደራሲው ዳንኤል ሰይድና በረዳቷ በአመለወርቅ መዘምር ነው። በረከት ወረደ/ማያ ብዙ ፊልሞችን ዳይሬክተር በማድረግ ምናልባቱም አሉ ከምንላቸው አንደኛው ነው።

የ"ህሊናን" ምናባዊ ትዕይንት በገጸ ባህሪያቱ ነብስ እየዘራ መልክና ደግሞ ግባታቸው ትክክለኛውን የማንነት ቅርጽ ይዞ እንዲሄድ ከፊት ሆኖ ይመራዋል። ሳልቃን ፊልም ፕሮዳክሽንም እንዲሁ የፊልሙ ዓለም ደጀን ነው። ከዚህ ዓለም ወጣ ብሎ ለመጀመሪያ ጊዜ በድራማ የባቡር ሃዲድ ውስጥ ገብቷል። እነማንስ በመሪ ተዋናይነት ይሳተፉበታል? እንደ ኪነ ጥበብ ለዛ ቢስ ጥያቄ ቢሆንም፤ እንደ አንዳንዱ ተመልካች ግን ጥያቄው ወሳኝነት አለው። ምክንያቱም ጸሀፊውን አይተው መጽሀፉን፤ ፖስቸሩን ተመልክተው ፊልሙን...የሚሉት ያልወጣ ውስጣዊ ብሂል አለና ነው።

የሠሯቸው ፊልምና ድራማዎች ብዙ ቢሆኑም፤ በ"ሞጋቾች" ተከታታይ ድራማ ደምቆ የወጣው እንግዳሰው ሀብቴ/ቴዲ እና በ"ኪያዬ" ፊልም እንደ እንጉዳይ የበቀለው ቸርነት ፍቃዱ ጥምረታቸው የጓደኛማችነት አሊያም የወንድምነት ሳይሆን የአባትና የልጅ ሆኖ ተገኝቷል። አባት ግን ህሊናው ገፍትሮ ከስፍራው ላይ ሌላ ፈንጂዎችን ቀብሮበታል። ከራስ አልፎ ማህበረሰባዊ ማንነትን የሚያደባይ ፈንጂ ነው።

በተለያዩ ዘውጎች የሚምዘገዘገው ህሊና አንደኛው በፍቅር ህይወት ሰማይ ላይ ይበራል። ከዚህ ቀደም በሙዚቃው የምናውቀው ድምጻ መረዋው መሳይ ተፈራ በዋና ገጸ ባህሪዋ በህሊና ህይወት ውስጥ ተሸጉጧል። ከትወናው በተጨማሪም በማጀቢያው ሙዚቃው ውስጥ "የፍቅር ወጥመድ ነው መላ ሁሉ ገላሽ፤ ምክንያት አጣሁኝ በምን ሰበብ ልጥላሽ..." ሲል የሚንተከተከው የድምጹ ቅላጼ በ"ህሊና" ነፋሻማ አየር ላይ ይረብባል። በሌላኛው ጎን ደግሞ የፍቅር ሊቁ ቸርነት ፍቃዱ የተላበሰው ገጸ ሰው እንባ የሚያዘራለት የፍቅር ወጥመድ ውስጥ ወድቆ ካልጠበቀው የህይወት ዘመን አጋጣሚና ከሌላ ማንነት ጋር ተፋጧል። ፍናን ህድሩ የ"ህሊና" የማንነት ቀሚስ ለብሳ የብዙ ታሪኮች የፀሐይ መውጫና የጀንበር መጥለቂያ ናት።

የጥበብ ሥራዎች ውስጥ ከታሪኩ ጋር መሳ ለመሳ ቆመው ከሚሄዱ ነገሮች አንደኛው መቼቱ ነው። እንግዲህ "ህሊና" ከአዲስ አበባ ተነስቶ "አንተ ባለጋሪ ቶሎ ቶሎ ንዳ..." ሲል ከናዝሬት አዳማ ላይ ደርሷል። መቼ? ለሚለው እራሱ ድራማው ይነግረናል። የት? ለሚለው ግን ከአዲስ አበባ ተነስቶ ናዝሬትን ከጫፍ እስከ ጫፍ ለማካለል ተነስቷል።

ሌላኛው ጉዳይ ድራማው፤ የመጀመሪያ ዙር ግብሩን አጠናቆ ተመልካቹ ዘንድ ለመድረስ እግሩ አጥሯል። በዚሁ ጉዞው ውስጥ እንደ አንድ ተከታታይ ድራማ ሳይሆን የተለየ የገንዘብና ሙያዊ ጉልበት ፈሶበታል የሚሉት አዘጋጆቹ፤ እንደ ጅምር 16 ያህል ክፍሎች የተሰናዱ መሆናቸውን በመጠቆም፤ ለዚህ ብቻ 10 ሚሊየን ብር ወጪ ተደርጎበታል ብለዋል። እውቁ ተዋናይ እንግዳ ሰው ሀብቴ "ከዚህ ቀደም ብዙ ድራማዎች ላይ ተሳትፈናል፤ ነገር ግን የነበረው ልምድ እንዲህ ለፊልሞች እንደሚደረገው አይነት አልነበረም። "ህሊና" ከቅደም ዝግጅቱ ጀምሮ ልዩ ነው። ድራማው ለማስተላለፍ ከሚፈልገው መልእክት አንጻር ብቻ፤ ፕሮዲዩሰሩ አንዳችም ስለ ወጪና ትርፉ ሳይጨነቅ፤ ስለ ኪነ ጥበቡ መደረግ የነበረባቸውን ነገሮች ሁሉ ያለ ስስት አድርጓል" በማለት ምስጋናውንም ቸሮታል።

"ህሊና" በስተመጨረሻ ማረፊያው ከሀገሬ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሆኗል። እንደሚታወቀው በርከት ያሉ ጣቢያዎች አሉና፤ ፕሮዲዩሰሮቹ እንዴትስ ፊታቸውን ወደዚያ ለማዞር መረጡ የሚለው ሀሳብ ከጋዜጠኞች በጥያቄ መልክ ቀርቦላቸውም ነበር። ምላሹም ይሄው ነው፤ "ሀገሬን ስንመርጥ፤ የሰጡን የገንዘብ አሊያም የጥቅማጥቅም ጉዳይ ከሌሎቹ የተሻለ ስለሆነ ላይሆን ይችላል። ለሙያውና ለጥበብ ባለሙያው ያላቸው ክብር፤ እስከዛሬ ድረስም መስዋዕትነት ልንለው በምንችለው መልኩ ለኢንዱስትሪው ለማበርከት የከፈሉትን ዋጋ በማየት ሀገሬን ትቶ ወደየትም ለመሄድ አላስቻለንም" የሚል ነበር።

"ህሊና" ሐሙስ ሚያዚያ 3፤ በዛሬው ዕለት በሀይሌ ግራንድ ሆቴል ውስጥ ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ፤ ወደ ማህበረሰቡ ለመሄድ ካባውን ለብሶ ይመረቃል፤ ጥበብም ጸአዳውን ጋቢዋን ደርባ በክብር ትመርቃለች። የምርቃት ሥነ ሥርዓቱ በራሱ በሀገሬ ቲቪ በቀጥታ ስርጭትም እንደሚኖረው አስታውቀዋል። በኪነ ጥበብ ሠረገላ ታጅቦ በዕለተ ሰንበት፤ ዘወትር እሁድ እሁድ ከምሽቱ 12 ሰዓት ጀምሮ በሀገሬ ቴሌቪዥን ይታያል።

አዘጋጆቹ ስለ ድራማውም ሆነ አጠቃላይ ይዘቱ ብዙ ብለውናል። እኛም ሰምተን ጥቂትም አይተን ይህችን ብለናል። እንግዲህ እኚህን ሁሉ በአንድ የእይታ ፌስታል አሊያም ዘንቢል ውስጥ አድርጎ በግራም ሆነ በቀኝ መያዙ የናንተው ነው። ሚዛኑም በማየት ነውና ፍርዱም ለተመልካች ይሁን።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የብዙዎች ተስፋ የሆነው የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት

**እዮሩስ ተስፋዬ**

ሻምበል አሳዬ ጥላሁን ትውልድና እድገታቸው በጅማ ከተማ ነው:: በሀገር መከላከያ ሠራዊት በውትድርና ሀገራቸውን ለሃያ ዓመት አገልግለዋል:: ከሁለት ዓመት በፊት በሰሜኑ ክፍል በነበረው ጦርነት ሁለት እግራቸው ላይ ጉዳት ደርሶባቸው ነበር:: በሕይወታቸው ይገጥመኛል ብለው ያላሰቡት ነገር ስለገጠማቸው ሕይወት ፊቷን ያዞረችባቸው መስሎ ተሰማቸው::

በአንድ በኩል ሕይወታቸው መትረፉም የፈጠረባቸው የማይደብቁት የደስታ ስሜት ነበራቸው:: አካል ጉዳተኝነትን ያልተለማመዱት ሻምበል አሳዬ ብዙ ምስቅልቅሎች ገጥሟቸዋል:: በደረሰባቸው የሥነ ልቦና ጉዳት ከቤት ለመውጣት ፍላጎታቸው ትንሽ ነበር:: ሰዎችን ለማግኘትም ፈቃደኛ አልነበሩም:: በገጠማቸው ችግር የአንዳንድ ሰዎችን አስተሳሰብ በሚገባ የመታዘብ ዕድል አጋጥሟቸዋል::

ዛሬ ላይ ሻምበል አሳዬ በመንግሥት በኩል ባገኙት የአካል ድጋፍ አገልግሎት ተስፋቸው ለምልሟል:: ራሳቸውንም ‹‹እኔ ዕድለኛ ነኝ::›› በማለት ይገልጻሉ:: ትናንት እርሳቸውን ሲታገሏቸው የነበሩ ክፉ ሃሳቦች ሁሉ እንደ ጉም በነው ጠፍተዋል:: በተስፋ ተሞልተው ነገን ሠርተው መኖር እንደሚችሉም በሚገባ አምነዋል:: እርሳቸው ያገኙት ድጋፍ ለሌሎች በስፋት እንዲዳረስ ይፈልጋሉ:: ‹‹የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት›› ተቋም ለሌሎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ድጋፍ እንዲያገኙ እስከታችኛው የመንግሥት መዋቅር እና በመላው ሀገሪቱ ተስፋፍቶ ማየትን ይሻሉ::

ሻምበል አሳዬ ካነሱት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ብዙ ነገሮችን ታዝበዋል:: አካል ጉዳት ከገጠማቸው በኋላ ወደ ተለያዩ ተቋማት ለተለያዩ ጉዳዮች ሲያመሩ ተቋሞቹ ምቹ እንዳልሆኑ አይተዋል:: የሕዝብ ትራንስፖርት ለመጠቀም መንገዶች ምቹ እንዳልሆኑና ለአካል ጉዳተኞች አመቺ ሆነው መሥራት እንዳለባቸው ያመለክታሉ:: ጤናማ ሰው በሁሉም ሰው ዘንድ ተፈላጊ



ታሪኩ ታደሰ (ዶ/ር)

ቢሆንም በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሰው ጫና ከበድ ይላል የሚሉት ሻምበል አሳዬ፤ ከዚህ እንፃር ለሁሉም አካል ጉዳተኞች  አስፈላጊው ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ይጠቁማሉ::

ትናንት በውትድርና ሀገራቸውን ያገለገሉት ሻምበል አሳዬ ኑሯቸውን የሚገፉት መንግሥት በሚከፍላቸው የጡረታ ክፍያ ነው:: ካላቸው ሻምበልነት ማዕረግ አኳያ ‹‹አንቱ›› ተብለው ተገለፁ እንጂ በመካከለኛ ዕድሜ ያሉ ናቸውና ሥራ የመሥራት አቅሙም ሆነ ፍላጎታቸው ከፍተኛ እንደሆነ ይገልጻሉ:: መንግሥትም ለእርሳቸውና እንደርሳቸው ጉዳት ለገጠማቸው ዜጎች ሥራ የሚሠሩበት ሁኔታ እንዲያመቻችላቸው ይጠይቃሉ::

የኢትዮጵያ አካል ድጋፍ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ  ታሪኩ ታደሰ (ዶ/ር) እንደሚናገሩት እንደ ሻምበል አሳዬ ያሉትን ጨምሮ በተለያዩ ምክንያቶች ድጋፍ ለሚሹ ሁሉ አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ የሰው ሠራሽ አካላት እና አጋዥ ቴክኖሎጂዎችን ማምረት፣ መጠገን እና ማቅረብ ብሎም ሌሎች የተሐድሶ አገልግሎት ለኅብረተሰቡ ለመስጠት ዓላማ አንግቦ እየሠራ ይገኛል:: በተጨማሪም ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር በሰው ሠራሽ እና በአካል ድጋፍ አገልግሎት የአጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠና መስጠት እና ጥናትና ምርምር በማድረግ በቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ አገልግሎት መስጠት ከዓላማዎቹ መካከል ይጠቀሳል::

ተቋሙ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል የአካል ተሐድሶ ሕክምና፤ የፕሮስቴቲክ እና ኦርቶቲክ ተሐድሶ ሕክምና  አገልግሎት፣ የፊዚዮ ቴራፒ፣ ኦኮፔሽናል ቴራፒ ተሐድሶ ሕክምና አገልግሎት፣ የፊዚዮ ቴራፒ መለማመጃ ምርቶች እና ሌሎችም ይጠቀሳሉ:: በአጋዥ ቴክኖሎጂ ምርትና መገጣጠም ደግሞ በቴርሞ ፕላስቲክ ሥራ ክፍል የሚሰጡ አገልግሎቶች፤ የአርቴፊሻል ግብዓት (ኮምፖነንት) ምርት፣ የክራንች እጄታ ምርት፤ የዊልቸር ግብዓት ምርት (ባላንስ ቦርድ፣ ዊል ባር፣ ላደር፣ ፊንገር እና  ሌሎችም ተጠቃሽ ናቸው::

ከአዕምሮ ተሐድሶ ሕክምና አገልግሎት ጋር በተያያዘም ገፈርሳ አካባቢ በሚገኘው የአዕምሮ ማገገሚያ ሕክምና አገልግሎት በተመላላሽ እና በአስተኝቶ ሕክምና፣ የአርት ቴራፒ አገልግሎት፣ የሻማ (የጥልፍ) ሥራ አገልግሎት፣ የማኅበራዊ፣ የሥነ ልቦና ድጋፍና ክትትል አገልግሎት፣ የሱስ ሕክምና አገልግሎት በተመላላሽ እና በአስተኝቶ ሕክምና ይሰጣል:: ለጊዜው ሦስት መቶ  አልጋ ያለው ሲሆን፤ ታካሚዎች ወይም በሱስ የተጠቁ ዜጎችን ሦስት እና ከዛ ወራት በላይ ሆኗቸው አገግመው እንዲመለሱ  እየሠራ ይገኛል::

ዋና ሥራ አስፈፃሚው እንደሚያብራሩት ተቋሙ አሁን ላይ በሁለት ቦታዎች ላይ ተገድቦ ይሥራ እንጂ ለወደፊት ግን በመመሪያው መሠረት ሁሉንም የማገገሚያ አገልግሎት ለመስጠት እቅድ አለው:: የሰው ልጅ የተለያየ ድጋፍ ይሻል:: በተፈጥሮ ምክንያት ምንም ዓይነት ድጋፍ ባይሻ እንኳን በዕድሜ መግፋት ብቻ የአካል ድጋፍ ፈላጊ ሆኖ ይታያል:: በዚህ መነሻነት ተቋሙ የተለያዩ የአካል ድጋፍ መሣሪያዎችን እንዲሁም ማሽኖችን እና ጥሬ እቃዎችን ከውጭ በማስመጣት እየሠራ ይገኛል:: ከዚህ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ ያሉትን ግብዓቶችን በመጠቀምም አገልግሎቱን ይሰጣል:: ይሁን እንጂ ከውጭ የሚመጡ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ካልተተኩ ኪሳራ ሊያጋጥም ይችላል::

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ አልነበረም ባይባልም በግለሰቦችም ይሁን በአንዳንድ ድርጅቶች አማካኝነት በተለያየ መንገድ አገልግሎቱ ይሠጥ ነበር:: ነገር ግን ቀጣይነት አልነበረውም:: የኢትዮጵያ የአካል ድጋፍ አገልግሎትም እንደ አዲስ በመቋቋም የአካል ድጋፍ አገልግሎት ከዚህ ቀደም ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን በመገንዘብ ዛሬ አበረታች የሚባሉ ጅምሮች አሉ:: ተቋሙም ከኢትዮጵያ አልፎ ምሥራቅ አፍሪካን የማገልገል ሃሳብ አለው:: ሆኖም ያደጉት ሀገራት የደረሱበት ደረጃ ለመድረስ ብዙ መሥራትን ይጠይቃል:: ድጋፎችን ከውጭ ሀገራት ከመጠበቅ ይልቅ በሀገር ውስጥ ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት መሥራት ይገባል::

በኢትዮጵያ አካል ድጋፍ የሚሹ ሰዎች ቁጥር ሃያ ሚሊዮን እንደሆነ የዓለም የጤና ድርጅት መረጃ ያትታል:: ይህ ቁጥር ከሁለት ዓመት በፊት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ከተከሰተው ጦርነት በፊት የነበረ እንደመሆኑ በሰው ሠራሽ አደጋዎች፣በግጭቶች፣ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች እና ከዕድሜ መግፋት ጋር በተያያዘ ቁጥሩ ከዚህም ሊልቅ ይችላል:: በአሁን ወቅት ተቋሙ በቀን ከ40 በላይ ድጋፍ የሚሹ አካል ጉዳተኞችን በመቀበል ላይ ቢገኝም ሥራው ጊዜ፣ ትኩረት፣ ግብዓት እና የበጀት አቅም የሚፈልግ ነው:: ካለው ድጋፍ ፈላጊ ቁጥር አንጻር ልዩ ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሠራ ይገባል::

የተቋሙ ዓላማ ከኢትዮጵያ አልፎ ጎረቤት አገራትን ጭምር ማገልገል እንደመሆኑ መጠን በቀጣይ ቅርንጫፎችን በተለያዩ ክልሎች ላይ በማስፋፋት፣ በትምህርት እና በምርምር ከመሥራት ባሻገር ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል ::

# ዓለም አቀፍ

## አውሮፕላን አብራሪዎችና የእንቅልፍ ጉዳይ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በዚህ ዓመት ኤ320 ኤርባስ አውሮፕላን 153 መንገደኞች እና የአውሮፕላኑን ሠራተኞች አሳፍሮ ከኢንዶኔዢያዋ መዲና ጃካርታ ሱላዌሲ ከተማ መብረር ጀመረ።

ዋናው አብራሪ ረዳት አብራሪውን ትንሽ ልተኛ ስለሆነ ኃላፊነቱን ውሰድ አለው። ረዳት አብራሪውም ተስማማ። ነገር ግን የሆነው ይህ አይደለም።

የኢንዶኔዢያ ብሔራዊ የትራንስፖርት ኮሚቴ በቅርቡ ባወጣው ሪፖርቱ አውሮፕላኑ ለ28 ደቂቃ ያህል ፓይለት አልባ ሆኖ ቆይቷል ብሏል። ሁለቱም አብራሪዎች በአንድ ላይ ተኝተው ነበር።

ክስተቱ ሀገራዊ ጥያቄዎችን ያስከተለ እንዲሁም በንግድ በረራዎች ላይ ያለውን የፓይለቶች ከፍተኛ የድካም ችግር አጉልቶ ያሳየ ሆኗል።

“ከጥቂት ዓመታት በፊት በሙከራ ላይ ያሉ ወታደራዊ ፓይለቶቻችን አዲስ ተልዕኮ ሲያጠናቀቁ ድካም መከላከያ የተባለው ቡና በቂ አይደለም ሲሉ ቅሬታቸውን ገልጸው ነበር” ሌተናል ኮሎኔል ያራ ዊንጌላር ጃግት ብለዋል።

አክለውም “በበራው ወቅት ነቅተው እንዲቆዩ የሚረዳቸው ሌላ ነገር እየፈለጉ ነበር” ይላሉ።

ችግሩን ለመከላከል የጦር አውሮፕላን አብራሪዎች አነቃቂ መድኃኒት የሚወስዱባቸው የተለያዩ ሀገራት አሉ። የንግድ አውሮፕላን አብራሪዎች የሥራ ፈረቃ ርዝማኔያቸው ከወታደራዊ አብራሪዎች የበለጠ ቁጥጥር ይደረግበታል።

ሆኖም ከፍተኛ ድካምን ተቋቁመው በዓመት 1 ሺህ ሰዓታት በደመና ላይ ሊያሳልፉ ይችላሉ። ባለፈው ዓመት በአውሮፓ ያሉ 6 ሺህ 900 አብራሪዎችን



ባሳተፈ አንድ ጥናት መሠረት 72.9 በመቶዎቹ የሚሆኑ ፈረቃቸውን ከጨረሱ በኋላም ከድካማቸው ለማገገም በቂ እረፍት እንደሌላቸው ይሰማቸዋል።

ሦስት አራተኛ የሚሆኑት ፓይለቶች ደግሞ በሥራ ላይ ሆነው እንቅልፍ ሸለብ አድርጓቸው እንደነበር ገልጸዋል። ይህን ለመከላከል ታዲያ በርካታ ፓይለቶች ሞዳፊኒል የተሰኘ አበረታች መድኃኒት እንደሚወስዱ በጥናት መረጋገጡን ቢቢሲ አስነብቧል።

በሮያል ኔዘርላንድስ አየር ኃይል አባላት የሆኑ በጎ ፈቃደኞች ለ17 ሰዓታት ያህል እንዳይተኙ ከተደረገ በኋላ ሞዳፊኒል፣ ካፌይን (ቡና) ወይም ምንም ውጤት የማያመጣ ነገር (ፕላሴቦ) እንዲወስዱ ተደረገ። ንቃታቸው እና የእንቅልፍ ሁኔታቸው ሲገመገምም ካፌይን እና ሞዳፊኒል ውጤታማ መሆኑ ቢደረስበትም ሞዳፊኒል ረዘም ላለ ጊዜ በመቆየት የበለጠ ውጤታማ መሆኑን ሙከራው አሳይቷል።

ሌሊቱን ሙሉ ሳይተኙ ቀርተው ሞዳፊኒል ከወሰዱ በኋላ ሳይተኙ ሌላ ቀንም እንደገና መሥራት እንደሚችሉም ተሰምቷቸው እንደነበርም ይገልጻሉ።

ሌተናል ኮሎኔል ያራ ዊንግላር ጃግት፤ ሞዳፊኒል የተሰኙ አበረታች መድኃኒቶች ከፓይለቶች ይልቅ ረጅም ሰዓት ለሚሠሩ እንደ ድንገተኛ እንክብካቤ ወይም የእሳት አደጋ ሠራተኞች ላሉ ሌሎች ሙያዎች ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል ይላሉ።

“በእነዚህ ሙያዎች ላይ ሠራተኞች ድካም እየተሰማቸው ቢሆን ምንም ስህተት የሌለበት ፍጹም የሆነ ተግባር ማከናወን ይጠበቅባቸዋል” ሲሉ በኔዘርላንድስ የመከላከያ ሚኒስቴር የኤሮስፔስ የሕክምና ክፍል ኃላፊ የሆኑት ሌተናል ኮሎኔል ያራ ዊንጌላር ጃግት ያስረዳሉ።

አንድ ጥናት እንዳመለከተው ሌሊቱን ሙሉ የህክምና አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ዶክተሮች ተግባራቸውን በተሻለ ሁኔታ ማከናወናቸውን አሳይቷል።

ነገር ግን “አብራሪዎች ሌሊቱን ሙሉ ተጉዘው እንዲወስዱን ነው የምንፈልገው? ወይስ አብራሪዎችም ሰዎች መሆናቸውን እና የራሳቸው ውስንነት እንዳላቸው መቀበል? ሁሉም ሰው እንቅልፍ እንደሚያስፈልገው እነሱም እንዲሁ እረፍት ያስፈልጋቸዋል የሚሉ ነገሮችን ልናጤን ይገባል” ይላሉ ሌተናል ኮሎኔሏ።

ሞዳፊሊን አበረታች መድኃኒቶችን የወሰዱ እነዚህ የሕክምና ባለሙያዎች በዕቅድ ተግባሮቻቸውን በማከናወን፣ በማስታወስ ችሎታቸው፣ ችግሮችን በመፍታት ረገድ እንዲሁም በጥንቃቄ በመወሰን የበለጠ ውጤታማ ነበሩ ተብሏል። ነገር ግን እንደ ወታደራዊ አብራሪዎች የሕክምና ባለሙያዎችም እነዚህን አበረታች መድኃኒቶች እንዲጠቀሙ ጫና ሊደረግባቸው ይችላል የሚሉ የሥነ ምግባር ጥያቄዎችም ይነሳሉ።

ያም ሆነ ይህ ግን ፓይለቶች በቂ እረፍት አድርገው በተገቢው ሁኔታ ሥራቸውን መሥራት እንዳለባቸው አብዛኛዎቹ መንገደኞች ይስማማሉ።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# ሐሙስ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ከፅዳት ሰራተኛነት እስከ ወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊነት

**ዓለማየሁ ግዛው**

በጋና በተካሄደው 13ኛ የአፍሪካ ጨዋታዎች ኢትዮጵያ አብዛኛውን ውጤት ያስመዘገበችበት የአትሌቲክስ ውድድር እንደነበር ይታወሳል።በእርምጃ ውድድር አንድ ወርቅና አንድ የብር ሜዳሊያ ማስመዝገብ ተችሏል።ኢትዮጵያ በውጤታማነት በማትታወቅበት የርምጃ ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ ያጠለቀው ደግሞ አትሌት ምስጋናው ዋቁማ ነው።አትሌቱ ወጣት፣ በብዙ ውጣ ውረዶች ለድል የበቃና አሁንም የድል ረሀብ የሚንፀባረቅበት ስፖርተኛ ነው፡፡

አትሌት ምስጋናው ተወልዶ ያደገው በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ወንጪ ወረዳ ሲሆን የእርምጃ ውድድርን የተቀላቀለው በ2013 ዓ.ም ነው።ከዛ በፊት በ 5 እና 10 ሺ ሜትር ርቀቶች ላይ ለመስራት ሞክሯል።በረጅም ርቀት እራሱን ኮከብ አትሌት አድርጎ ህልሙን ለመኖር፣ በመታተር ላይ የነበረው አትሌት በሰዎች ምክር ፊቱን ወደ እርምጃ ውድድር በማዞር ልምምዱን በትጋት ቀጠለ። ባገኘው የሙከራ እድል ዘርፉን ተቀላቅሎም ዛሬ ላይ በውጤት ጎዳና መጓዝ ጀምራል፡፡

በ20 ኪሎ ሜትር የእርምጃ ውድድር ኢትዮጵያን በአፍሪካ ደረጃ በመወከል ወርቅ ያጠለቀው ይህ አትሌት፣ ልምምዶቹን በብዙ መሰናክሎች ውስጥ ሆኖ በማከናወን ያገኘውን እድል በአግባቡ ተጠቅሟል።

በአካዳሚም ይሁን በሌሎች የስልጠና ሂደቶች የማለፍ ዕድሎች ያላገኘው አትሌት ምስጋናው በትውልድ ስፍራው በሚኖርበት ወቅት በሚማርበት ትምህርት ቤት ለስፖርት በነበረው ፍቅር ከሚያደርገው እንቅስቃሴ በስተቀር ያገኘው የስልጠና እድል የለም።የእንጀራ ነገር አስገድዶት የትውልድ ቀዬውን ለቆ ወደ አዲስ አበባ በመጣበት ወቅት ከኑሮ ጋር በሚያደርገው ግብ ግብ በስፖርት ውስጥ ማለፍ ለሱ የሚታሰብ አልነበረም። አትሌቱ የስፖርቱ ፍቅር በውስጡ ስለነበር ከብዙ ዓመታት በኋላ ወደ ስፖርት ተመልሶ ለድል መብቃቱን ይናገራል።

አሰለፈች መርጊያን የመሳሰሉ ታዋቂ አትሌቶች ከትውልድ ስፍራው መውጣታቸው፣ እንደነሱ ለመሆን በልጅነቱ ህልም ሰንቆ በትጋት ፈተናዎችን እየተጋፈጠ መስራቱን ቀጠለ።ከዘመድ ጋር እየኖረ በሆቴል የመስተንግዶ ስራን ከዛም የጽዳት ስራን እየሰራ ህይወትን ለማሸነፍ ከሚያደርገው ግብ ግብ ጎን ለጎን ልምምዱን እየሰራ ቆይቷል። የመስተንግዶ ስራ ከስልጠናው ጋር ሊጣጣምለት ባለመቻሉ የጽዳት ስራን መስራት ጀመረ።በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የጽዳት ስራውንና ልምምዱን ጎን ለጎን ለአራት ዓመት ከግማሽ ሰርቷል።በድርጅቱ በሳምንት ሶስት ቀን ስራ እና ልምምዱን እንዲሰራ ፍቃድ ቢሰጠውም ያ በቂ ባለመሆኑ ስራውን ትቶ ሙሉ ጊዜውን ለአንድ ዓመት ልምምድ ማድረጉን መረጠ።ለአንድ ዓመት ያለስራና ዘመድ ላይ ጥገኛ ሆኖ ጠንክሮ ልምምዱን በመስራት በአዲስ አበባ ክለቦች ቻምፒዮና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ለሙከራ ወክሎ በመወዳደር ሶስተኛ ሆኖ ማጠናቀቁ ለክለቡ እንዲፈርም አስቻለው።በአንድ ወቅት ውድድር ሊያደርግ ዋዜማው ላይ እያለም ልብ ሰባሪ የእህቱ ህይወት ማለፉን የሰማበት ዕለትና ወንድሙን በካንሰር በሽታ ያጣበት ቅጽበት ፈታኙ ጊዜ እንደነበር ያስታውሳል።

በእርምጃ ውድድር በሀገርና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ክለብ ከተቀላቀለ በኋላ አሰልጣኞች የሰጡት ስልጠና እና



**አትሌት ምስጋናው ዋቁማ፣**

ከልጅነቱ ጀምሮ አብሮት ያደገው የስፖርት ፍቅር በውጤት ለመታጀቡ ዋናው መንስኤ እንደሆነ ያስታውሳል።ፊቱን ወደ እርምጃ በማዞር ክለብ ከገባ በኋላ ጥሩ አሰልጣኝ በማግኘቱ ጠንክሮ እየሰራ የአሸናፊነት ስነልቦናን ተጎናጽፏል።ለዚህ ሁሉ ድልና ውጤታማነቱ አንዲት አሰልጣኝ ስሟ በልዩ ሁኔታ ይጠቀሳል።የእርምጃ አሰልጣኝ አምሳለ ያዕቆብ ወደ እርምጃ ውድድር እንዲገባ አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ ትልቅ ሚና አላት።አሰልጣኙ ሻለቃ ባዬ አሰፋ እንዲሁ በሚሰጡት ስልጠና ጠንክሮ በመስራቱ ውጤታማ እንደሆነም ያስረዳል።

የመጀመሪያ ሀገር አቀፍ ውድድሩን በ2013 ዓ.ም አሰላ በተካሄደው የኢትዮጵያ ወጣቶች ቻምፒዮና በ10 ኪሎ ሜትር የመም ውድድር አንደኛ መውጣት ችሏል።በተመሳሳይ ዓመት በሀዋሳ በተካሄደው የኢትዮጵያ ቻምፒዮና 20 ኪሎ ሜትር እርምጃ ክለቡን ወክሎ በመወዳደር ሁለተኛ ወጥቷል።ከዛ በኋላ በተካሄዱ ሀገር አቀፍ ውድድሮች በሙሉ አንደኝነቱን የነጠቀው የለም።ባካሄዳቸው ውድድሮች 11 የወርቅ፣ 1 ብርና 1 የነሐስ ሜዳሊያዎች አሉት፡፡

ሀገርን መወከል የቻለው በአህጉር አቀፍ ውድድሮች ሲሆን 2014 ዓ.ም ሞሪሺዬስ ላይ በተካሄደው 22ኛ የአፍሪካ ቻምፒዮና ሀገሩን ለመጀመሪያ ጊዜ ወክሎ በመሳተፍ የዲፕሎማ ተሸላሚ መሆን ችሏል።በ2015 ዓ.ም በዛምቢያ በተካሄደው መላው የአፍሪካ ጨዋታዎች ሀገሩን ወክሎ የወርቅ ሜዳሊያን አጥልቋል።ዘንድሮ በጋና በተካሄደው 13ኛው የአፍሪካ ጨዋታዎች እንዲሁ በ20 ኪሎ ሜትር የእርምጃ ውድድር አንደኛ በመውጣት ወርቁን ወስዷል።

ይህ ውድድሩ ለአንድ ተጨማሪ ዓመት በመራዘሙ እና ከ33 ዓመት በፊት ወርቅ መመዝገቡ በመስማቱ የረጅም ጊዜ ዝግጅት በማድረግ ለውጤት እንደበቃ ይናገራል።ኢትዮጵያ በሶስት ወንድና በሶስት ሴት ተወዳዳሪዎች በተወከለችበት ውድድር የኬንያና የአልጄሪያ አትሌቶችን ፉክክር ተቋቁሞ አሸንፏል።ከተፎካካሪዎች መብዛትም በላይ የአየር ንብረቱ አስቸጋሪ መሆኑ ከድል አላስቀረውም፡፡

## ከመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# የኢንተርፕራይዙን አቅም ያሳየ የግንባታ ፕሮጀክት

**ስሜነህ ደስታ**

የመከላከያ ኮንስራክሽን ኢንተርፕራይዝ ደረጃ አንድ ሥራ ተቋራጭ ድርጅት ነው።መጀመሪያ የመከላከያ መሰረተ ልማቶችን ፍላጎት ማሟላት በሚል ዓላማ የተቋቋመ ነው።ከጊዜ ወደ ጊዜ ዓላማውንና ተግባሩን በማስፋት አፈጻጸሙን አሳምሯል።በዚህም በትልልቅ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ላይ ሌሎች ተቋራጮች የማይሞክሩትን ጭምር በግንባታው ዘርፍ በመሳተፍ በአግባቡ ሠርቶ በማጠናቀቅ አስረክቧል።የቴክኖሎጂ አጠቃቀሙንና አፈጻጸሙን በማሳደግ አሁንም ትልልቅ ግንባታዎችን በተለያዩ ፈታኝ በሆኑ አካባቢዎች እያከናወነ ይገኛል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና መሥሪያ ቤትን እና የመከላከያ ሚኒስቴር ዋናው መሥሪያ ቤት ሕንፃ ግንባታን አጠናቆ ማስረከቡ የሚጠቀሱለት ተግባራቶቹ ናቸው።ሠርቶ ካስረከባቸው ሕንጻዎች በተጨማሪ በከተማዋ ውስጥ ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ጋር ውል በማድረግ የግንባታ ሥራ እያከናወነ ይገኛል።

በዛሬው ዓምዳችን የምናስቃኛችሁ ኢንተርፕራይዙ በአዲስ አበባ ከተማ እየገነባ የሚገኘውን ዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ ዲዛይን የተደረገውን የዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትን የጂ+3 ማስፋፊያ የሕንጻ ግንባታ ፕሮጀክት ነው።ፕሮጀክቱ የሚገኘው በመዲናችን ጃንሜዳ በሚባለው አካባቢ በመከላከያ ሰላም ማስከበር ማዕከል ግቢ ውስጥ ሲሆን የግንባታው ፕሮጀክት ተጠባባቂ ሥራ አስኪያጅ ደግሞ ኢንጂነር ደረጀ ኃይለገብርኤል ይባላሉ።

ሥራ አስኪያጁ እንደሚሉት የግንባታው ባለቤት የመከላከያ ሰላም ማስከበር ማዕከል ነው።የማማከር ሥራ የሚሠራው የኢንተርፕራይዙ እህት ድርጅት የመከላከያ ኮንስትራክሽን ዲዛይን ድርጅት ነው።የፕሮጀክቱ አጠቃላይ የውለታ መጠን 229 ሚሊዮን 556 ሺህ 614 ብር ከ42 ሳንቲም ነው።ሕንጻው ያረፈበት ስፋት 1ሺህ 158 ሜትር ስኬዌር ሲሆን፣ እኤአ ሚያዚያ 24 ቀን 2023 የሥራው ውል ተፈርሞ በዚሁ ዕለት የግንባታ ሥራውም ተጀምሯል።ለፕሮጀክቱ የተፈቀደው ጊዜ 550 የካላንደር ቀናት ሆኖ እኤአ ጥቅምት 25 ቀን 2024 የሚጠናቀቅ ይሆናል። የፕሮጀክቱ አጠቃላይ አፈጻጸምም 81 ነጥብ 3 በመቶ ነው።

እንደ ኢንጅነር ደረጀ ገለጻ የሕንጻው ዲዛይን ለየት ባለ ሁኔታ ዓለም አቀፍ መስፈርትን መሰረት ያደረገ ስለሆነ ግንባታውም በዚያው መልኩ እየተከናወነ ይገኛል።ባለሶስት ወለሉ ሕንጻ አብዛኞቹ ክፍሎች በጣም ሰፋፊ እና ለመማር ማስተማር ምቹ ናቸው።የወለሎቹ ከፍታ ስነውበትን ጠብቆና አካቶ በግራና በቀኝ ያሉ ክፍሎች ወደ ላይ እና ወደ ታች ለማየት እንዲመች ታስቦ የተገነባ ነው።

የምድሩ ወለል ሰፊ የሆነ ቦታ ለእንግዳ መቀበያ ማረፊያ የተተወ ቦታ፣ ቢሮ፣ ባህላዊ ቡና ማፍያ፣ ገላ መታጠቢያ፣ መጸዳጃ ቤት እንዲሁም ሌሎችም ይገኙበታል።በአንደኛው ወለል ቢሮ፣ ሰፊ መማሪያ ክፍል፣ ሰፊ ቪዲዮ ኮንፍረንስ ክፍል፣ መጋዘን፣ ገላ መታጠቢያ እንዲሁም መጸዳጃ ቤት አሉት።

በሁለተኛው ወለል ቢሮ፣ ሁለት ሰፋፊ መማሪያ ክፍሎች፣ ቤተመፅሀፍት፣ የድምጽ ማዳመጫ ክፍል፣ የፎቶ ኮፒ ክፍል፣ ሰፊ የውጭ ማንበቢያ ቦታ (ቴራዞ) አሉት።ሶስተኛው ወለል ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ሰገነት ያለው ሲሆን በግራ በኩል ያለው ባለ 12 ሜትሩ ከፍታ ወለል 232 ነጥብ 41 ሜትር ስኬዌር የሸፈነ ነው።በቀኝ በኩል ያለው ባለ 13 ነጥብ 5 ሜትር ከፍታ ያለው ወለል ደግሞ 703 ነጥብ 13 ሜትር ስኬዌር ስፋት የሸፈነ ነው።

የሕንጻው ስትራክቸራልና ሌሎች ሥራዎች ሙሉ ለሙሉ ጥራታቸውን ጠብቀው ተጠናቀዋል።ቀሪ ሥራዎች የሙብራትና የመጸዳጃ ቤት የገጠማ ሥራ እንዲሁም የጣራ የውሃ ስርገት፣ የመጸዳጃ ቤት የሴራሚክ ገጠማ እና የውስጥና የውጭ የቀለም ቅብ ሥራዎች ናቸው።እነዚህንም ለማጠናቀቅ ኢንተርፕራይዙ በከፍተኛ ኃላፊት እየሠራ ይገኛል።እኛም በግንባታው ቦታ ተገኝተን እንደተመለከትነው የግንባታው አፈጻጸም ወደ ማጠቃለያው የደረሰ መሆኑን ለመታዘብ ችለናል።

በሕንጻው ሥራ አካል ላይ የተካተቱ የሥራ አይነቶች የእሳት



**እየተጠናቀቀ ያለው ሕንጻ**

አደጋ ጠቋሚ መሳሪያ (Fire alarm System) ፣ ኤልክትሮ ሜካኒካልና ኦዲዮ ቪዥዋል ሲስተም አሉት።ከዘመናዊ የትምህርት አሰጣጥ ጋር የተያያዙና የትምህርት አሰጣጥን ለማሳለጥ የሚረዱ ዲጂታል ሲስተሞች MATV እና CCTV ተዘጋጅቶላቸዋል።ከዚህ በተጨማሪ ለአካል ጉዳተኞች ብቻ የተዘጋጀ፣ ራሳቸው እየተቆጣጠሩ ከሚፈልጉበት ወለል የሚያደርሳቸው አሳንሰር ተዘጋጅቷል፤ ለተመረጡ ክፍሎች ከክፍሉ ሠራተኛ ውጪ እንዳይገባ የሚከለክል በር (Access control door) ሲስተም ይገጠምላቸዋል።

የፕሮጀክቱ ለምድር ወለል እና ለደረጃ ሥራ የሚያገለግል ግራናይት የሚባለውን ቁስ በምርት እጥረት በበቂ ደረጃ ማቅረብ አለመቻሉ ተጠቃሽ ተግዳሮት ሆኗል።በእርግጥ ችግሩ የሚቃለሉበት መንገድ ስለተለየ መፍትሄ ተገኝቶለታል።ይህ ተግዳሮት ይኑር እንጂ ፕሮጀክቱ መልካም አጋጣሚዎችም አሉት።አሠሪው አካል በቅርበት ስላለ ጠዋትና ማታ በየእለቱ ፕሮጀክቱን ይከታተላል።

እንዲሁም በየአስራምስት ቀኑ ከግንባታው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ግምገማ ስለሚካሄድ በቀጣይ ሥራዎች ላይ አቅጣጫ ይቀመጣል።ይህ አካሄድ ፕሮጀክቱን ለማፋጠንና ከተያዘለት ጊዜ በፊት ለማጠናቀቅ ትልቅ እገዛ እንደሚያደርግ ሥራ አስኪያጁ ያስረዳሉ።

እንደ ኢንጅነር ደረጀ ገለጻ፣ ይህ ዓለም አቀፍ መስፈርትን የሚያሟላው የግንባታ ፕሮጀክት ውለታ ከተያዘለት ጊዜ 80% ሳይደርስ ይጠናቀቃል። ለዚህም የኢንተርፕራይዙ ሠራተኞች የሚያሳዩት የሥራ ተነሳሽነትና ትጋት ዋና መተማመኛቸው እንደሆነ ጠቅሰዋል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ